# ልሳነ ህዝብ

## ድምፅ ለተነፈጉት የቆመ ልሳን

ቅፅ3 ቁጥር 04 ግንቦት 2/2016


## በዚህ ዕትም


1. ትክክለኛው የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ
2. ያባዲብሉ ግጥሞች
   ክፍል ፪
3. የህወሓት ተስፋፊነት
4. ውሸት ቢደጋግም
5. ትውስታ
6. አይ ስብሃት ነጋ

ቃለ ምልልስ

7. ከቀሲስ ታደሰ አጠና ሃይሉ ጋር

ግጥሞች

እንዲሁም ሌሎች ዘገባዎች


### የሳምንቱ ምርጥ ግጥሞች

**ዘመናይ ማርዬ**

ዘመናይ ማርዬ
ዘመናይ ማርዬ
ውሸትሽን ችዬ
ማጭበርበርሽን ችየ
ሰላም ስለፈለግኩ
ሞኝ ነው ተብዬ
ላመታት ታገስኩሽ
ሳትቱዪኝ አልተውኩሽ
ዘመን ሲያልፍ በሮ
መንፈሴ ተሰብሮ
ጧት ማታ እሮሮ
ብልጣ ብልጧ አራዳ
ስሜቴ ሲጎዳ
ስገልጽ ቅሬታዬ
ያገር ትምክህተኛ
ጉረኛ ተብዬ
በዘመናይ ብትር
የህሊና ስምበር
ያቆሰለኝ ስራሽ
ሞክሪው በተራሽ
በቃኝ ቋቅ ብሎኛል
ውሸት ሰልችቶኛል
ትምክህተኛም በዪኝ
እንደ ዲያብሎስ ጥዪኝ
ግን ዞር በይ ከኔ
እራስሽ ተቀጪ
በራስሽ ኩነኔ
ይባልልሽ መጥኔ
ዘመናይ ወገኔ
ዘመናይ ወያኔ
አባ ዲብሉ - ከጮሪሳ



**የኛ ባንዲራ**

ጨውም ቋጠሩብሽ
ብዙም አወሩብሽ
አጣጣሉሽ ከቶ
በየካምፓቸው ጥግ
አረጉሽ ቡትቶ
ትርጉምሽ ሳያቁ
ከንቱ ተሳለቁ
የኋላ የኋላ
ማን አላቸው መላ
አሉሽ ባንዲራችን
ትዝብት ከልባችን
ከልሳነ ህዝብ

# ትክክለኛው የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ

## ለፍትህ ተሚጋኞች የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የፍትህ ጥያቄ፡ ለጠባቦቹ ደግሞ ከግርግር ለማትረፍ መልካም አጋጣሚ ይመስላል።

**ከልሳነ ህዝብ ዘጋቢ**

የሰላምና የዲሞክራሲ ጥያቄ የኛ ብቻ ሳይሆን የበርካታ ጭቁን ህዝቦች ጥያቄ ነው። ባገራችን የወያኔ ስርዓት ያዘመተው የዘር ፖለቲካ የአንዱን ህዝብ ፍትሃዊ ጥያቄ የሌላው እንዳይመስለውና ይልቅስ አንዱ ሲነሳ ሌላኛው የሚጎዳ እንዲመሰለው በያንዳንዱ ዜጋ ውስጥ የተከሉት መርዘኛ ዕፅ መኖሩ ከታወቀ ሰነባብቷል።

በተለይም የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ ተገቢና ትክክለኛ ቢሆንም እንኳ ወያኔ በሚያሰራጨው የጥላቻ ወሬ ምክንያት በርካታ ዜጎች የኦሮሞ መጠናከር ለአማራው ወይም ለትግሬው ወይም ለደቡቡ መዳከም ምክንያት እንደሆነ አድርገው እንዲያሰቡ ከተደረጉ ሰነባብተዋል።

ጥቂት ጠባብ አስተሳሰብ ያላቸው የኦሮሞ ብሄር ተወላጆች ሌላው ህዝብ በኦሮሞ ህዝብ ጫንቃ ላይ የተቀመጠ እስኪመስላቸው ድረስ የኦሮሞ ህዝብ እንደሌሎች ወንድሞቹ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ለፍትህና ለዕኩልነት የሚያደርገውን ትግል በመጠለፍ የመገንጠልን ጥያቄ ሲያራምዱ ማየት ከተለመደ ሰነባብቷል።

በመጀመሪያ ለነዚህ ጠባቦችና አርቀው ማሰብ ለማይችሉት ቦታ በመስጠት መፃፍ አድካሚና ደባሪ በመሆኑ ስለመልካሙና ብዙው የብሄሩ አባላት መናገር ተገቢ ነው።

የኦሮሞ ህዝብ እንደሁሉም ህዝብ የሃገራችንን አንድነት ተከብሮና ሁሉም ዜጎች የሃገራቸውን ሃብት እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስርዓት እንዲፈጠርና በዚሁ ስዓት ውስጥም የበዪ ተመልካች ከመሆን ነፃ ወጥተው ከሁሉም ህዝቦች ጋር በእኩልነትና በሰላም መኖር ይፈልጋሉ፡ በዚህም ምክንያት የመበት ጥያቄአቸውን በሰላማዊ መንገድ ለማቅረብ ባገኙት መድረከ ሁሉ ድምፃቸወን በማሰማት ላይ ናቸው።

የኦሮሞ ህዝብ ቢያነሳውም ጥያቄው የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለም።

አማራን ጨምሮ ማንም ሆዝብ በማንም ጫንቃ ላይ አልተቀመጠም። በየጊዜው ወደ ስልጣን የመጡ ዘራፊዎች በህዝቡ ጫንቃ ላይ ሲቀመጡ ጥቂት የማይባሉ የስርዓቱ ጋሻጃግሬዎች ደግሞ የዝርፊያ ተግባራቸውን ያከናውናሉ። ወያኔ ወደ ስልጣን ሲመጣ ምስኪንና ለህዝብ ቆርቋሪ በመምሰል ነበር። በኋላ ግን ስልጣኑን በማደላደል ህዝቦች ባንድነት እንዳይነሱም በብሄሮችና ብሄረሰቦች መካከል የስነ ልቦና ጦርነት በመከፈትና ለዘመናት የሚዘልቅ መጠራጠር በመፍጠር ያገራችን ህዝቦች የተባበረ ድምፅ እንዳይኖራቸው አድርጓል።

በዚህ አደገኛ ድርጊቱ ለጊዜው የተሳካለት የመሰለው ወያኔ የአማራ ህዝብ ለመብቱ ሲነሳ ኦሮሞውን አማራ መጣብህ እንደበፊቱ ሊገዛህ ሊጨፈልቅህ ነው በማለት ኦሮሞው ለመብቱ ሲነሳም እንደዚሁ የኦሮሞው መጠናከር ለአማራ አደገኛ አስመስሎ በማቅረብ ህዝቡን ሲያለያይና ከቻለም ሲያጋጭ ቆይቷል።

መልካሙ ነገር ምንድነው ቢባል ህዝቡ ይህንን ርካሽ የ19ኛ ክፍለ ዘመን የአውሮፓውያን የከፋፍለህ ግዛ አካሄድ ዋጋ እንደሌለው መረዳቱ ነው። ካሁን በኋላ ማንም ሰው በማንነቱ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነቱ የማንም ዜጋ ፍትሃዊ ጥያቄ በጋራ በመማንሳት ለተግባራዊነቱ ባንድ ላይ የሚታገልበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ትክክለኛው የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ የመላው ኢትዮጵያውያን ጥያቄ ነው። የኦሮሞ ህዝብ መብቱና ነፃነቱ እንዳይከበር የሚፈልግ ሰላማዊ ሰው የለም፡ ከወያኔ መሪዎችና ከጋሻጃግሬዎቹ በስተቀር። አማረኛ ተናጋሪ ሰዎች ስልጣን ሲይዙ በጅምላ የህዝቡን የባህሪይ ነፀብራቅ ተደርገው መወሰድ የለባቸውም። የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ሰዎች ስለጣን ላይ ስለወጡ መላው የትግራይ ህዝቦ ተጠቃሚ አልሆነም፡፡

ባሁኑ ጊዜ ነፃነት የናፈቀው ቁጥር አንድ ህዝብ ቢኖር የትግራይ ህዝብ ነው። ለመብቱ መታገል እንዳይችል በስለላና በተለያዩ ዘዴዎች ወያኔ አፍኖ ስለየያዛቸው ለጊዜው የተዳከሙ ቢመስሉም ቀኑ ሲደርስ ግን ምን እንደሚያደርጉ ይታያል።

የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ የአማራውም የሰፊው የትግራይ ህዝብም የሁሉም ብሄር በሄረሰቦችም ስሜትና ፍላጎት ያካተተ ተገቢ ጥያቄ ነው።

**አባ ዲብሉ—ከጮሪሳ**

እንዳባኩላሳ
እንዳቡሳ ኬሳ
መንፈሴ እየሳሳ
ገላዬ እየከሳ
የዛሬውን ዕውነት
በነገ ተስፋነት
ጭጋግ ወሮት ቤቴ
ከማዶ ማየቴ
ቅዠት ወይስ ጤና
ራዕይ የታለና
ሃታኡ ሃታኡ
ከማለት በስተቀር
ከባብ አናት ሆኖ
አጉል መመናቀር
ዝንጀሮ'ንኳ ያውቃል
ሃታኡ በማለት
ጊዜን ይጠብቃል
የኔም ወኔ እንደሁ
አልተሸናም ከቶ
ይጠብቃል ሰክኖ
ትግስተኛ ሆኖ
ትግስት ሲበዛ
ተዳፍኖ እሳቱ
ገሞራ ፈንድቶ
አይቀርም መውጣቱ
ጊዜ እንጂ ኣባ ጅሎ
ያላወቀ መስሎ
በራሱ ላይ ቆጥሮ
ያሰማል እሮሮ
የማይቀር ቀጠሮ
እንዲለይ በወቅቱ
እንዲለይ ዘንድሮ።

አባ ዲብሉ—ከጮሪሳ

# በብሔርተኝነት ስም ታሪክንና የኢትዮጵዊነትን መንፈስ ማጣጣል ተቀባይነት የለውም!!

ከ http://welkait.com/?p=1494 የተወሰደ
(በፍቅር ለይኩን)

በአንድ ወቅት በደቡብ አፍሪካዊቷ ከተማ በኬፐታውን የሚኖር አንድ በንግድ ሥራ የሚተዳደር ኢትዮጵያዊ ጎልማሳ አንድ አሳዛኝ ገጠመኙን እንዲህ አጫውቶኝ ነበር፡፡ ይህን ታሪኩን ያካፈለኝ ኢትዮጵያዊ ጎልማሳ የሥራ ቦታው ላይ ከአንድ ከኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ጋር በተነሳ ጠብ በተፈጠረ ግጭት የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ የሆነው ጓደኛውን አንድ የፊቱን ጥርሱን በቦክስ ያወልቀዋል፡፡ የጥርሱን መውለቅ የሰሙ የዚህ ሰው ጓደኞችም ተሰባስበው ይህን ሰው ካልገደልን በማለት ሲጋበዙ ነገሩ በሰላም ያልቅ ዘንድ አንዳንድ የሚያውቋቸው ሰዎች ለሽምግልና ጣልቃ ይገባሉ፡፡ በሽምግልና ድርድር ላይ እያሉም የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ የሆነው ጓደኛውን ጥርስ ያወለቀው ሰው የአያቱ ስም የኦሮሞ ስም ሆኖ ይገኛል፡፡ እነዛም በእንዴት ተደፍረን፣ ይህን ሰው ካልገደልን በማለት ሲዝቱ የነበሩ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችም፣ ይኸ ሰው ለካ ወገናችን ነው በማለት ለበቀል ያነሱትን ሰይፋቸውን ወደ ሰገባው ይመልሳሉ፡፡ ሐሳባቸውን በመቀየር ጉዳዩ በሰላም ተቋጭቶ፣ በሃያ ሺሕ የደቡብ አፍሪካ ራንድ ካሳ ክፍያ እንዲጠናቀቅ ተስማምተው እርቅ ማውረዳቸውንና አያቴ ስም የኦሮሞ ስም በመሆኑ ከጉድ ወጣሁ ሲል በግርምት መንፈስ ሆኖ ገጠመኙን አጫወተኝ፡፡ ቀጣዩን በገጽ 8 ይመልከቱ



ፍትህ ከአፈሙዝ ?



የተማሪ ሬሳ ማየቱ ያብቃ



ይህ ሰቆቃ መቼ ያብቃ?

የሀሊና እስረኛው አብርሃም ደስታ






# ኦሮሚያ የመላው ኢትዮጵያዊ መላው ኢትዮጵያም የሁሉም ኦሮሞ ናት! -አበበ ቶላ

## አቤ ቶኪቻው
## ከጃዋር ሃሳብ የማልስማማበት እና የምስማማበትን ስለመለየት፤

የኛ ሀገር ፖለቲካ የቡዳ ፖለቲካ ነው እንዳሉት ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና አሁንም ድጋሚ ፖለቲካችንን ቡዳ ሊበላው ነው መሰል ጣት መቀሳሰር እና እነ እንትና እነ እንትና መባባል ልንጀምር ይመስላል... ምናባቱ እንግዲህ ካልደፈረሰ አይጠራም...

ጃዋር ሰሞኑን ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በዋሽንግተን ዲሲ ካደረጉት ንግግር በኋላ በአራት ጉድዮች ላይ አስተያየት ሰጥቷል። ካነሳቸው ሃሳቦች ውስጥ በተወሰነ ደረጃ የምስማማባቸው ሃሳቦች ቢኖሩኝም በርካታ የማልስማማባቸው ሃሳቦችም አሉ። ከሁሉ ከሁሉ ግን በትልቁ የማልስማማበት፤ ኦሮሞ በሙሉ ተመሳሳይ ነው ብሎ ሁሉንም ኦሮሞዎች በአንድ ቅርጫት ውስጥ ለማስቀመጥ የሚሞክረው ነገር ሁልጊዜም በጣም የሚያበሳጨኝ ነው። (እነደሱ አባባል እርሱ በሚለው የማይስማማ ኦሮሞ ኦሮሞ አይደለም (ሲያናድድ!))

እኛ ኦሮሞዎች ሰዎች ነን። ምንም እንኳ የሰው ልጆች በሙሉ በፍጥረታቸው አንድ ናቸው ቢባልም፤ በአስተሳሰብ እና በአመለካከት ግን አንድ አይነት መሆን አይችሉም። ሁሉም ሰው የየራሱ አመለካከት እንዳለው ሁሉ፤ ኦሮሞዎችም የየራሳችን አመለካከት አለን። እኛ በፋብሪካ የተመረትን ሮቦቶች አይደለንም። የተለያየ አመለካከት የተለያየ አስተሳሰብ፣ የተለያየ የምፍትሄ አቅጣጫ፣ የተለያየ ምኞት እና ፍላጎት ያለን ሰዎች ነን። ይሄ ሰው በመሆናችን የተሰጠንም ጸጋ ነው። ጃዋር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፤ "ከለዘብተኛ ኦሮሞዎች ጋር አብረን እየሰራን ነው" ማለቱን ተከትሎ በኦሮሞ ውስጥ ለዘብተኛ አክራሪ የለም ብሎ ይሞግተናል። ሞልቶ! በሁሉም ማህበረሰብ ውስጥ በአንድ ጉዳይ ላይ አክራሪ እና ለዘብተኛ እንዳለው ሁሉ በኦሮሞ ማህበረሰብ ውስጥም ይሄ አለ። ወደፊትም ይኖራል።

ለምሳሌ ያክልም፤ ራሱ ከጃዋር እና የመሳሰሉት ኦሮሚያ የኦሮሞ ናት ሲሉን እየሰማን ነው። በነገራችን ላይ የ 'የ' እና የ 'ለ' ነገር በትርጉሙ ላይ ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም። ኦሮሚያ ለኦሮሞ ናት ተባለም ኦሮሚያ የኦሮሞ ናት ተባለም ምንም የፍቺ ልዩነት የላቸውም። (ወዳጃችን ጃዋር ኦሮሚያ ለኦሮሞ ናት አላልኩም ኦሮሚያ የኦሮሞ ናት ነው ያልኩት ሲል አይቼ ባውጠነጥን ባውጠነጥን ምንም ልዩነት አላየሁበትም።) የሆነው ሆኖ ጃዋር እንደሚያስበው ይሄ አስተሳሰብ የሁሉም ኦሮሞዎች አስተሳሰብ ነው። በኦሮሚያ የተነሳው ተቃውሞም ዋና ሃሳብ ይሄ ነው ይለናል።

እኛ ጃዋር ኦሮሞ አይደለም ብለን አንከራከርም። ነገር ግን እርሱ ብቻ ሳይሆን እኛም ኦሮሞዎች ነን። እንደኛ አስተሳሰብ ኦሮሚያ የመላው ኢትዮጵያዊ መላው ኢትዮጵያም የኦሮሞ ናት። እንኳንስ ኦሮሚያ እና ብሪታኒያ እና አሜሪካንን የመሳሰሉት ሀገሮች እንኳን የብርትሾች እና የአሜሪካኖች አይደሉም፤ የሁላችንም ናቸው እንጂ! (ምንም እንኳ እንደ ዶናልድ ትራምፕ አይነት ቀውሶች ይሄ አሳብ ቅዥት ቢመስላቸውም አሁን አለም ባለችበት ደረጃ ግን ማንም ሰው የሀገሪቱን ህግ እና ደንብ አክብሮ እስከኖረ ድረስ ሁሉም ሀገር የሁሉም ነው። በዛ መሰረት ነው ጃዋርም ሆነ እኔ በአሜሪካ እና እንግሊዝ የምንኖረው!)


በኦሮሚያ ክልል የተነሳው ተቃውሞ ዋና ማጠንጠኛ ኦሮሞ ዘመዶቻችን አንድም በገዛ ወገኖቻቸው፤ (በኦህዴድ አባላት) አንድም ከፌደራል በሚሄዱት እነ አባይ ጸሃዬ የሚደርስባቸው ስር የሰደደ በደል ሞልቶ ስለፈሰሰ ነው፤ እንጂ ኦሮሚያ ለኦሮሞ ትሁን በሚል አይደለም። እንደዚ የሚሉ ቢኖሩም እንኳ በኔ አስተሳሰብ ስህተት ውስጥ እየገቡ ነው። ማንም ሰው በአግባቡ እና በደንቡ መሰረት እስከተንቀሳቀሰ ድረስ (በእግር ኳስ ቋንቋ ፌር ፕሌይ እስከተጫወተ) ሁሉም ሃገር የርሱ ነው። ኦሮሚያን ጨምሮ። ብቻ ገበሬዎችን ያለአግባብ አያፈናቅል። ብቻ ገበሬውን በገዛ መሬቱ ላይ ከአምራችነት ወደ ዘበኛነት አይቀይር እንጂ!

አሁን ኢህአዴግ እየፈጸመ ያለው ዘረፋ በኦሮሚያ ላይ ነውር ነው! በትግራይም ላይ ሲፈጸም ብልግና ነው! በአማራ ክልልም ሲደረግ ጸያፍ ነው።

ይልቅስ ጃዋር በብሄር ስለመደራጀት ያነሳው ነገር ላይ እስማማለሁ። ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ይሄ የኔ አመለካከት ነው ብለው በነገሩን መሰረት የብሄር ወይም ዘውጌ ፖለቲካዊ ስብስብ አይመስጣቸውም ብቻ ሳይሆን አፍራሽ ነው ሲሉም ኮንነውታል። በርግጥ "እባብን ያየ በልጥ ይደነግጣል" እንዲሉ አሁን አሁን እየሆነ እንዳለው ነገር የብሄር አደረጃጀቶች የሚያስፈራ ነገር አላቸው። ቢሆንም ግን አፍራሽ ናቸው ብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ ከባድ ነው። ሰዎች በመሰላቸው መልኩ የመደራቸት እና የመታገል መብታቸው በጽኑ ሊከበር ይገባል። በሰለጠኑት ሃገራት በብሄር የተደራጁ ፓርቲዎች ለዴሞክራሲ ግንባታ አፍራሽ ሚና ሲጫወቱ አላየንም። እንደ ምሳሌም ስኮቲሽ ናሽናል ፓርቲ በ ዩናይትድ ኪንግደም ፖለቲካ ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ማየት ይቻላል። እኛም ሃገር ቢሆን ፖለቲካችን አፍራሽ ሚና የሚኖረው ከአያያዛችን እንጂ ከአደረጃጀታችን አይመስለኝም። (እንደውም ከቤተሰብ ጉባኤ አንስቶ ብብሄር መደራጀት ተፈጥሯዊ ነው ብዬ አስባለሁ.... አፍራሽ የሚሆነው ከኔ ብሄር በላይ ላሳር ማለት ሲጀመር ነው! እሱን የሚገራ ሀገር አቀፍ ህግ መኖር ይኖርበታል!)

በኢሳት ቴሌቪዥን የኦሮምኛ ቋንቋ ዝግጅቶች መጀመራቸውን አስመልክቶ የኦሮሞን ህዝብ ትግል ለማዳከም ነው የሚለን ጃዋር ከላይ እንዳነሳሁት በኢሳት ቴሌቪዥን ላይ በአዘጋጅነት የሚሰሩትን ኦሮሞዎች ስለ ኦሮሞ ጉዳይ የማያስቡ ራሱን ደግሞ ከማንም በላይ ለኦሮሞ አሳቢ የማድረግ አዝማሚያ ነው ያየሁበት... ይሄኔ ይቺ ሰውዬ ቀስ ብላ እኔንም ለኦሮሞ አታስብም ትለኝ ይሆናል እኮ ብዬ ስቄ ትቼዋለሁ!

እያልኩ ልጻፍ ልተወው... በማለት እያሰብኩ ነው....



ልሳነ ህዝብ የብዙሃን ድምፅ ነው

## የህወሓት ተስፋፊነት በኢትዮጵያ ዓላማው:- ታላቋን ትግራይ መመሥረት! – ገብረመድህን አርአያ (ፐርዝ፣ አውስትራሊያ)

**በሰሜን በጌምድር (ጎንደር) ወልቃይት ፀገዴ፣ ፀለምት በአማራው ላይ ተስፋፊው ተሓህት/ህወሓት የፈጸመው የዘር ማጽዳት ወንጀል**

ይህ ታሪካዊ መረጃ በተቀነባበረ መልኩ የሚጀምረው ገና ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ (ተሓህት) ሲፈጠር ጀምሮ አስቀድሞ ለማጥፋት ያነጣጠረው በአማራው ህዝብ ላይ እንደሆነ በማስገንዘብ ነው።

ከዚህ በመነሳት የተሓህት ፕሮግራም ገና ከ1967 ጀምሮ የረቀቀው በዲማ ኮንፈረንስ በየካቲት ወር 1968 ከ150 ያነሱ የተሓህት ታጋዮችን በማሰባሰብ ሕጋዊ ሆነ ተብሎ ቢነገርም፣ ሁሉም ታጋዮች ግን አልተቀበሉትም። በመጥፎ መልኩ የተዘጋጀውና አማራውን በማውገዝና ጠላት ብሎ የፈረጀ ነው። በኢትዮጵያና በህዝቧ፣ 1ኛ፣ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት አውዳሚ፣ 2ኛ፣ አንድነቱን ጠብቆ ለዘመናት አብሮ የኖረውን የኢትዮጵያ ህዝብ በጎሳ በዘር ለመበታተን ተደምሮና ተቀንሶ የተቀነባበረ አደገኛ ፕሮግራም በማለት አውግዘውት ነበር። **ከነዚህካወገዙት መካከል ለምሳሌለመጥቀስ፤ አስገደገብረሥላሴ፣ ካህሳይ በርሄ (ዶ/ር ግንጽል)፣ ተሾመ ጉዶ፣ ሲሆኑ እነዚህ በህይወት ያሉ ሲሆን፣ እቁባዝጊ በየነ፣አሰፋገብረዋእድ፣አጽብሃ ዳኘው፣ ዘርኡ ገሰሰ (ኢጋአዚ) ገሰሰው አየለ፣ ዶ/ር አታክልት ቀጸላ፣ ዘወንጀል በየነ፣ መሃረተክሌ ወዘተ እነዚህፕሮግራሙን በጠነከረ አቋም ስለተቃወሙ የተገደሉናቸው።**

ተሓህት የፕሮግራም ዝግጅቱን ንድፈ ሃሳብ የጀመረው ገና በረሃ ሳይወጣ ማገብት ተብሎ በሚጠራበት ከ1966 ጀምሮ ነው። ይህንን ፕሮግራም በሃላፊነት ያዘጋጀው አረጋዊ በርሄ ሲሆን፣ ጥር 1967 ለወታደራዊ ስልጠና ኤርትራ፣ ስህል ወርደው ፕሮግራሙን በማጠናከር የተሰማሩት የትጥቅ ትግሉ መሪዎች አረጋዊ በርሄ፤ በዋና ሃላፊነት፣ ግደይ ዘርአጽዮን፣ አስፍሃ ሃጎስ፣ በህመም የሞተ፣ ዘርኡ ገሰሰ፣ በወያኔ የተገደለ፣ ሥዩም መስፍን፣ ሃይሉ /ነጠበ/ መንገሻ ሲሆኑ ብዙ የጎደለው እንዳለ ተስማምተው በይደር ወደ ደደቢት ተዘዋወረ።

የካቲት 11፣ 1967 ታጋዮቹ ደደቢት በረሃ እንደገቡና የትጥቅ ትግሉ እንደተጀመረ፣ ግንባር ቀደም ተግባራቸው ሶስት ነጥቦች ላይ ነበር ትኩረት ይሰጠው።

1ኛ፣ የድርጅቱን ስም ማውጣት፣

2ኛ፣ ለወደፊቱ ለምትመሰረተው የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የግዛት ስፋት ከውጭ ሃገር፣ ሱዳን በሚገኘው መልኩ ማዘጋጀት፤

3ኛ፣ ፕሮግራሙን ለመጨረሻው ዝግጅቱ ታማኝ ታጋዮችን በማሰባሰብ ለሚከተሉት ሰዎች፣ ማለትም፣ **አረጋዊ በርሄ፣ሊቀመንበር፣ ሥዩምመስፍን፣ አባይ ፀሃየ፣ ስብሃት ነጋ፣ መለስዜናዊ፣ አውአሎም ወልዱ፣ ስየ አብርሃ፣ ግደይ ዘርአጽዮን**ወዘተ ሃላፊነቱ ተሰጠ።

**ለዚህ መሰናዶ ከበጌምድር ጠቅላይ ግዛት፣ ፀገዴ፣ ፀለምት፣ ሁመራ፣ ወልቃይት እንዲሁም ከወሎ ጠ/ግዛት፣ ራያና ቆቦ፣ወልድያ፣ አላማጣእስከ ላይኛው ሃሸንጌ ሃይቅ ድረስበማጠቃለል የትግራይ መሬት ነው ተብሎ በመወሰን የፕሮግራሙንአቋም ደመደመ።**

ይህ ፕሮግራም ለመጀመሪያ ጊዜ በእጅ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ ወደ 30 ገጽ የሚሆን ተባዝቶ በመጽሓፍ መልክ ተጠርዞ በብዛት ተያዘ። **በሃላፊነትየጻፉት አረጋዊ በርሄ፣ ስብሃት ነጋ፣ ሥዩምመስፍን፣ መለስ ዜናዊ፣ አባይ ፀሃየ ናቸው።** በየቦታው እንዲሰራጭም ተደረገ።

ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ኢትዮጵያን ለመበታተን፣ ሕዝቧን በዘርና በጎሳ የከፋፈለ፣ አማራውን ደመኛ ጠላት ብሎ ያወገዘ ሆኖ የመጣና እነሆ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት የሆነ አስተሳሰብ ነበር።

አማራ የትግራይ ህዝብ ደመኛ ጠላት ነው፣ ከሚለው

ቀጥሎም **ለብዙ ዓመታት ነፃ ሃገር ትግራይ ነፃነቷ ተገፎ በአማራው (ኢትዮጵያ) ቅኝአገዛዝ ወድቃለች፣** በማለት **ብዙይ ተነትናል። በአጼ ዮሃንስ ዘመነ መንግሥት ሃይሏ በርትቶ በአካባቢዋየነበሩትን ነገሥታት በቁጥጥር ስርአውላ ነበር። ይሁን እንጂ አፄ ዮሃንስ ከሞቱ በኋላ በዳግማዊ ምኒልክአማካኝነትትግራይ በሸዋው ማእከላዊ ግዛት ስር ወደቀች። ከዚህ ጊዜበኋላ ነው አማራው የመሳፍንት ቡድን እና ተከታዮቹየትግራይን ነፃነት ገፈው የህዝቧን አንድነት ያናጉት።በግልጽና ስውር በሆነ ዘዴዎች (ሸዋዊ ዘይቤዎች) የትግራይ ህዝብበድንቁርና፣ በበሽታ፣ በረሃብ አዘቅት ውስጥ እንዲሰምጥ ያደረጉት እያለ ይቀጥላል።**

ከላይ የተጠቀሰውና ሌላውን ጨምሮ ተሓህት የትግራይ ህዝብ ጠላት አማራ ነው፣ ነፃ ሃገር የነበረቸው ትግራይ ሃገርህ በአማራ (ኢትዮጵያ) ቅኝ ግዛት ሆና አንተ ለከፋ መከራ ተረግህ በማለት አመራሩ በሙሉና የተሓህት ታጋዮች ወደ ህዝቡ ተበታትነው ፖለቲካቸውን አስተማሩት። ማንኛውም የትግራይ ህብረተሰብ ይህ የምትናገሩት ሁሉ ፈጽሞ ከእውነት የራቀና የራሳችሁ የፈጠራ ፖለቲካ ነው። አማራ ለትግራይ ህዝብ ጠላቱ አይደለም፣ ወንድሙና እህቱ እንጂ። ሁላችንም ተቃቅፈን በጋብቻ ተሳስረን በፍቅርና በሰላም የምንንሮር የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች ነን። ከትወልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣውን ፍቅርና ወንድማማችነትን እህታማችነት አታፍርሱብን። አማራ (ኢትዮጵያ) ትግራይን በቅኝ ግዛት ስር አድርጋለች የምትሉት ከየት ያገኛችሁት እንደሆነ እኛ አናውቅም። ትግራይ ዱሮም አሁንም የኢትዮጵያ የታሪክ ማእከል ናት በማለት የትግራይ ህዝብ ከገጠር እስከ ከተማ ተቃውሞ አደረሰባቸው። በዚህም ምክንያት የገጠርና የከተማ ኗሪው በቀን እና በሌሊት እየተለቀመ በሽብርተኞች ቡድን ተገደለ፣ ቤቱ ፈረሰ፣ ህፃናት በየቦታው ወድቀው ቀሩ። ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት ከፋሽስቱ ጣሊያን ጋር የተዋጉ የትግራይ ኢትዮጵያዊ አርበኞች በወያኔ ትሓህት ከየቤታቸው እየተለቀሙ ሃለዋ ወያኔ ገብተው በጥይት እየተረሸኑ መስዋእትነት ከፈሉ።

ይህ በዚህ እንዳለ

**በ1969 የተሓህት መሪዎች ስብሃት ነጋ፣ አረጋዊ በርሄ፣ አባይ ፀሃየ፣ መለስ ዜናዊ፣ ሥዩም መስፈን፣ስየ አብርሃ፣አውአሎም ወልዱ ተሰባስበው በትግራይውስጥ የሚኖረው አማራ፣ ኦሮሞና ሌላውም ከትግራይ ይውጡ፣ትግራይ ለትግራይ ህዝብ ብቻ ናትየሚል አዋጅ አስተላለፉ።** ይህንን ሃሳብ ያልደገፉት **ግደይ ዘርአጽዮን እና ዶ/ርአታክልት ቀጸላ** ብቻ ነበሩ።

በዚህ የዘረኝነት አጥር ውስጥ የገባው የተሓህት አመራር ከ1969 መጨረሻ በፕሮግራሙ ያካተተው **የትግራይ መሬት ብሎያስቀመጠውወልቃይት፣ ፀገዴ፣ ፀለምት፣ ሁመራ ቃፍታላይ ማነጣጠር ጀመረ።** በተቻለ መጠንም በፍጥነት ተቆጣጥረን በትግራይ ውስጥ ገብተው በተሓህት አመረር ስር መተዳደር አለባቸው የሚል እቅድ ያዘ። ከዚህ ቀደም ብሎ**በአርከበእቁባይ** የተዘጋጀ ካርታ **ከበጌምድር ጠ/ግዛት ከላይየተጠቀሱትን ቦታዎች፣ ከወሎ ጠ/ግዛት ራያና ቆቦ፣ አላማጣ፣ወልዲያ፣ አፍላ ደራ** ለምት መሰረተው **አዲሲቷ ዲሞክራቲክሪፑብሊክ ትግራይሲ**ካተቱ፣ በምእራብ በኩል **ደግሞወልቃይት፣ ሁመራ ፀለምት፣ ፀገዴ ተጨምረው ትግራይ ከሱዳን ጠረፍ ጋር እንደትገናኝ፣ በደቡብ በኩልደግሞወደውሃ ምላሽትግራይ እንድትሰፋ ሲወስን፣ እነዚህ ቦታዎች ሁሉ ለምና ሃብታም መሬቶች ናቸው። ይህንን ውጥንለማሳካትበወልቃይት ፀገዴ ተሓህት ህዝቡን እያፈነ ማጥቃት ጀመረ።**

**<u>የወያኔ/ህወሓት/ተሓህት መሰረታዊ የታሪክ ወንጀል</u>**

የወላቅይት ፀገዴ፣ ፀለምት፣ ሁመራ ኢትዮጵያ ከተፈጠረች ጀምሮ ለብዙ ሺህ ዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ታሪካዊ ቦታዎች የበጌምድር (ጎንደር) ግዛት መሬት ነው። ታሪክም የሚያረጋግጠው ይህ ነው።። በምንም ተአምር ከትግራይ ግዛት ጋር ግንኙነት የለውም። የሚገናኙበት ኢትዮጵያውያን እና ኢትዮጵያዊነት ነው። በጌምድርም ሆነ ትግራይ የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች ናቸው። በሃይማኖትና በጋብቻ ተያይዘዋል። ይህ ደግሞ በሁለቱ ህዝብ ማካከል ብቻ ሳይሆን በመላው ኢትዮጵያ ውስጥም ያለ ነው። ኦሮሞው ከትግሬ፤ ትግሬው ከአማራ፣ አፋሩ ከጋምቤላው፣ ጉራጌው ከሌላው ዘር ጋር ወዘተ የተደባለቀ ህዝብ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ በደም የተቆራኘና አንድ ህዝብ ነው።

አመቺ ጊዜ እስኪያገኝ በመጠባበቅ የቆየው የተሓህት አመራር በየካቲት መጨረሻ በ1968 በድርጅቱ የተሰባሰቡት ታጋዮች ዲማ በተባለው በኢጋሜ አውራጃ ውስጥ የዲማ ኮንፈረንስ በመባል የሚታወቅ ኮንፈረንስ በማካሄድ ከ150 የማይበልጡ ታጋዮች **በአረጋዊ በርሄ** ሊቀመንበርነት በሚመራ ስብሰባ ፕሮግራሙ ቀርቦ እንዲጸድቅ ቢጠይቅም ታጋዩ አልተቀበለውም። ይሁንና፣ ሊቀመንበሩ ጸድቋል ብሎ የድርጅቱ የፖሊሲ አቋም ሆኖ እስከመጨረሻው ቀጥሏል።

**<u>የተሓህት የሰሜን በጌምድር የወረራ ዝግጅት</u>**

ተሓህት ወደ ሰሜን በጌምድር/ጎንደር በቀጥታ ሃይሉን አሰባስቦ አልገባም። ምክንያቱም፡

በመጀመሪያ ጊዜና ሁኔታውን ማስተከካል ፈለገ፤ ኢህአፓ በአካባቢው በስፋት ይንቀሳቀስ ስለነበር በአቅምና በትጥቅ ጥራት ህወሓት ዝቅተኛ ስለሆነ፣ ኢህአፓዎቹ ይመቱናል፣ ያጠቁናል የሚል ስጋት ስለአደረበት፣

የወልቃይት ፀገዴ ፀለምት ህዝብ አይቀበለኝም ብሎ በማመኑ፣ አቅሙን እስኪያጠናክር መዘግየቱን እንደ አማራጭ ወሰደ።

ቢሆንም ግን፣ ተሓህት በድብቅ በ1969 መጨረሻ ወደ ፀገዴና ፀለምት መሽሎክሎኩን ቀጠለ። በዚህ ጊዜ ደጀና ውስጥ ሽሬላ ተብላ በምትታወቀው ትንሽ ከተማ የተሓህት ታጋዮች ቅዳሜ ቀን ህዝቡን ሲያንገላቱ በነበሩበት ወቅት ማንነቱ ባልታወቀ ቡድን ሁለቱን የተሓህት ታጋዮች በገበያው መሃከል ገደሏቸው። በታህሳስ 1972 በሻእቢያና በጀብሃ፣ በወያኔና በኢህአፓ መካከል በተነሳው ጦርነት በኢህአፓ በሰነዘረው ጥቃት ተበታትነው ሱዳን ገቡ። በወልቃይት ፀገዴ ፀለምት የኢህአፓን ሠራዊት በበላይነት ሲመሩት የነበሩት **ታምራት ላይኔ፣በረከት ስምኦን፣ አዲሱ ለገሰ፣ ተፈራ ዋለዋ፣ ታደሰቅንጥሾ** ወዘተ አስቀድመው ለወያኔ ህወሓት እጃቸውን ስለሰጡ፣ እየመሩም የኢህአፓን ሠራዊት እንዲጠቃ አደረጉ። በጥቃቱም ብዙዎቹ ተገደሉ፣ ተማረኩ፤ የተማረኩትም ተረሸኑ።

ለዚህ ተጠያቂዎቹ **ስብሃት ነጋና አባይ ፀሃየ** ናቸው።

ይህ ጊዜ ወያኔ ህወሓት ፍላጎቱ የተሳካበት ወቅት ነበር። አሁን ያለው የህወሓት አመራር በ1971 የካቲት 5 ቀን የተመረጡት፤ **ስብሃት ነጋ፣የድርጅቱ ሊቀመንበር፤ አረጋዊ በርሄ፣ወታደራዊ አዛዥ፤ አባይ ፀሃየ፤ ግደይ ዘርአጽዮን፤ ስዩምመስፈን፤ መለስ ዜናዊ፤ አውአሎም ወልዱ፤አርከበ እቁባይ፤ ዘርአይ አስገዶም፤ ተወልደ ወ/ማርያም፤ ገብሩ አስራት፤ስየአብርሃ፤ ጽድቃን ገ/ተንሳይ፤ ዶክተር አታክልት ቀጸላ፣ በወያኔየተገደለ፤ አስፍሃ ሃጎስ፣** ታሞ የሞተ ናቸው። የህወሓት ከፍተኛ አመራር የነበሩና ሁሉን ትእዛዝ የሚሰጡት ደግሞ፣**ስብሃት ነጋ፤ መለስ ዜናዊ፤አረጋዊ በርሄ፤ አባይ ፀሃየ፤ ስዩምመስፍን፤ ግደይ ዘርአጽዮን** ናቸው። በወልቃይት ፀገዴ ጥቃቱን ያቀነባበሩት አመራሮች፤ **ስየ አብርሃ፤አርከበእቁባይ፤ጻድቃን ገ/ተንሳይ፤ ዘርአይ አስገዶም፤ አውአሎም ወልዱ ናቸው።** እነዚህ በሰሜን በጌምድር፣ ወልቃይት ፀገዴ ትእዛዝ ይጠባበቁ የነበሩ ሲሆኑ፤ ይህንን ሁሉ በበላይነት የመራው**ስብሃት ነጋ** ሲሆን፤ የቅርብ ተባባሪዎቹ ደግሞ**አባይ ፀሃየና አርከበ እቁባይ** ነበሩ።

ከላይ የተጠቀሱት የህወሓት አመራር የሰሜን ጎንደር ኗሪ ሰላማዊ ህዝብ ለማጥቃት የታየው ሁኔታ አመራሩ ዝግጅት ያደረገው ነበር። በሪጅን 1 የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ የነበረው፣ በአባቱ ወልቃይት ፀገዴ፣ በእናቱ ሽሬ የሆነው**መኮንንዘለለው**፣ የተወጠነውን ተልእኮ ይዞ ወልቃይት ፀገዴ ፀለምት እየተዘዋወረ ህዝቡን በመሰብሰብ ይህ መሬት የትግራይ መሬት ስለሆነ እናንተ ከእንግዲህ ወዲህ የሰሜን ጎንደር ዜጎች አይደላችሁም፣ የትግራይ መሬት ስለሆነ እንኖራለን ካላችሁ ትግሬዎች መሆናችሁን አምናችሁ ተቀበሉ፤ የትግራይ ዜጎች አይደለንም፣ ሰሜን በጌምድር የትግራይ አይደለም ካላችሁ ደግሞ የድርጅቱን የህወሓትን ውሳኔ ተጠባባቁ፤ የምታምኑበትን አሁን ተናገሩ በማለት ሲያስጠነቅቅ፣ ከህዝቡ በኩል ያገኘው መልስ ግን አንድ ነበር። የቀረበውን ሃሳብ ከህፃን እስከ አዋቂ፣ የወልቃይት ፀገዴና የፀለምት ህዝብ፣ እኛ የሰሜን በጌምድር (ጎንደር) አማሮች እንጂ ትግሬዎች አይደለንም፣ የታሪካችን ስር መሰረቱ የበጌምድር አማሮች ነን። ይህ ቆመህ የምትናገርበት መሬት ሰሜን በጌምድር ይባላል። ከጥንቱ ታሪካችን ብትነሳም ይህ መሬት ታሪካዊ ነው። ያለፉት የኢትዮጵያ ነገሥታት ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁኗ ሰአት በመንግሥት እውቅና ያገኘ የጎንደር፣ “የበጌምድር” ጠቅላይ ግዛት እየተባለ የሚጠራ ነው።

ቀጣዩን በገፅ 4 ይመልከቱ

ልሳነ ህዝብ

በአፋኙና ጨቋኙ የወያኔ መንግስት ምክንያት የተሸበቡ የኢትዮጵውያን ልሳኖች እንደተዘጉ አይቀሩም። ስለነሱ የሚናገርላቸው፣ አቤት የሚልላቸውና የሚያስተጋባላቸው ልሳን አለ። ይህንንም ልሳን የህዝብ እንጂ የማንንም እንዳልሆነ ላማሳየት ልሳነ ህዝብ በድረ ገፁ በየወሩ የማያወጣው ጋዜጣ ነው።

ልሳነ ህዝብ በፖለቲካ ፓርቲነትም ሆነ በማንኛውም ቀጥተኛ የፖለቲካ መድረክ ላይ የማይሳተፍ ለኢትዮጵያውያን ጥቅም ብቻ የቆመ የዲሞክራሲና የፍትህ መድረክ ነው።

ማንም ሰው አመለካከቱን በነፃነት መግለፅ የተፈጥሮ ልግሱ ነው በማለት የተነሳ መድረክ ነው።

# ከገፅ 3 የዞረ ..... የህወሓት ተስፋፊነት

ዋና ከተማችን ደግሞ ጎንደር ነው። የእናንተም ትግራይ ጠቅላይ ግዛት ይባላል፣ ዋና ከተማው ደግሞ መቀሌ ነው። ስለዚህ ኣናንተ የተሓህት ታግዮች ጉዳዩን ብታስቡበት ጥሩ ነው። ወደ እርስ በርስ ግጭት ያመራል። በተጨማሪም ታሪካዊ የወሰን ክልል አለን፣ እሱም ተከዜ ወንዝ ነው። **የትግራይና በጌምድር የድንበርክልሉ ተከዜ ወን ዝ ነው።** ከጥንት ጀምሮ የሁለቱ ኢትዮጵያውያን የድንበር ወሰን መሆኑን ልናረጋግጥ እንፈልጋለን በማለት በአንድነት ድምፅ ህዝቡ ራሱ አረጋገጠ።

ሁመራን በተመለከተ ወያኔ ተሓህት/ህወሓት የትግራይ ነው ቢልም በወቅቱ እስከ ግንቦት 1983 የኢትዮጵያ ምድር ጦር ሰፈ ጥበቃ ስለነበረው፣ ወያኔ ህወሓት መሬቱን የተቆጣጠረው አዲስ አባባን በያዘበት ጊዜ ነው። ወያኔ ህወሃት በትግል ላይ በነበሩበት ጊዜ 17 ዓመታት ሙሉ ሁመራ አልገባም፣ አልተቆጣጠረም። በአካባቢውም ድርሽ አላለም።

ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መኮንን ዘለለው የህዝቡን አንበገርም ባይነትና የሰሜን በጌምድር አማሮች ነን ባይነት፣ ለወራት የቆየበትን ሪፖርት ለህወሓት አመራር ለስብሃት ነጋና ሌሎችም አቀረበ። **ስብሃት ነጋ በመኮንን ዘለለው**ላይ ወረደበት፣ ወዲያውኑም ከሪጅን 1 የህዝብ ግንኙነት ሃላፊነት አወረደው። በዚህ ክስተት ባይታሰርም የአእምሮ በሽታ ሰለባ በማድረግ አሰቃዩት።

ከዚህ በመቀጠል የተነሳንበትን ታሪካዊ ትንተና በተጨባጭ ለማረጋገጥ የቀድሞውን የሃገራችን ኢትዮጵያን ካርታ በ "ሀ" እንዲሁም ወያኔ ህወሃት ኢትዮጵያን ወሮ ከያዘ በኋላ ያዘጋጀውን ካርታ በ"ለ"፣ የበጌምድር ጠ/ግዛትን እና የትግራይን ጠ/ግዛት የወሰን ክልል ደግሞ በ "ሐ" ና "መ" ላይ በማነጻጸር እንመልከት።

ለሱዳን በህ.ወ.ሓ.ት. የተሸጠው መሬት

"ሀ" በሚለው የኢትዮጵያ ካርታ በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታትና ህዝብ ያመኑበት፣ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታትና በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ተቀባይነት ያለው የኢትዮጵያ ግዛት መልክአ ምድር ካርታ ነው። በኢትዮጵያ በቅደም ተከተል የመጡ መሪዎች እስከ ደርግ ዘመን መንግሥት ይህንኑ ተቀብለውና አምነው ኢትዮጵያና ህዝቧ አንድነቱን ጠብቆ የሃገሪቷን ዳር ድንበር በመጠበቅ ኢትዮጵያን የመሩበት ረጅም ዘመናት ያስቆጠረ ካርታ ነው።

በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ህዝብ የጠቃላይ ግዛቶች የወሰን ድንበር ሳይካልለው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ በፈለገውና በመረጠው ጠ/ግዛት ሄዶ በመንግሥት ሥራ፣ በእርሻ፣ በንግድ፣ በአንጥረኛነት፣ በሸማኔነት ወዘተ በመሥራትና የሃገሪቱን ሕገመንግሥት በመከተል ትዳር መስርቶ፣ ኢትዮጵያዊነትን ከደመ ስጋው ቀላቅሎና ኮርቶ የሚኖር ህዝብ ነው። ኢትዮጵያ በልጆቿ ተከብራ ለዘመናት የቆየች ሃገር ናት። ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚኮራባት ሃገርም ነበረች። ዛሬስ? የሚለውን ጥያቄ እንደሚከተለው እንመለከተዋለን።

**ታሪካዊው የጠ/ግዛቶች የድንበር ክልል**

የኢትዮጵያ ጠ/ግዛቶች ድንበር በ "ሀ" ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ካርታን ብንመለከተው በቂ ግንዛቤ ይሰጠናል። ይህ ደግሞ ለዘመናት ጸንቶ የቆየ ነው። ለዚህም ነው ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር የተቆራኘው።

**የበጌምድር ጠ/ግዛትና የወሎ ጠ/ግዛትን ስንመለከት**

የበጌምድር ጠ/ግዛትና የትግራይ ጠ/ግዛት ድንበርን ያካለለው ታሪካዊው የተከዜ ወንዝ ነው። ተከዜ ወንዝ በምእራብ በኩል በጌምድርን፣ በምስራቅ በኩል ትግራይን ለይቶ በማካለል ለብዙ ዘመናት ጸንቶ የቆየና የኢትዮጵያ ነገሥታትም ያመኑበት ድንበር ነው።

ወልቃይት፣ ፀገዴ፣ ፀለምት፣ ቃፍታ፣ ሁመራ በሰሜን በጌምድር (ጎንደር) ስለሚገኙም ሰሜን በጌምደር (ጎንደር) ተብለው ይጠራሉ። ይህ ደግሞ በተለያዩ የታሪክ መጽሐፍት የሚገኝ እውነት ነው።

የኢትዮጵያ ግዛቶች በወሰን ክልላቸው የሚታወቁት ከጥንት ተያይዞ የመጣ በመሆኑ በትግራይና በጌምድር፣ በትግራይና በወሎ እስከ ደርግ ዘመነ መንግሥት ድረስ ያስነሳው ግጭትም ሆነ ይገባኛል የሚል ጥያቄ ተንስቶም አያውቅም፣ አይታሰብብምም። የትግራይ ህዝብ ሰሜን በጌምድር የትግራይ ነው አላለም። ይህንን ተስፋፊነት የፈጠረው የተሓህት አመራር ነው። ይህ በህ.ወ.ሓ.ት የተፈፀው ሰብዓዊ ሙብት ረገጣም በከፍተኛ የወንጀል ተጠያቂው ወያኔ ነው። ሰሜን ጎንደር፣ አማራ ነው ግዛቱም የጎንደር ነው። በኢትዮጵያ ታሪክም የሚታወቀው ወልቃይት.. ፀገዴ.. ፀለምት.. ሁመራ.. ወ፣ዘ፣ተ የጎንደር ግዛቶች መሆናቸው ነው።

**የድንበርን ቋንቋ በተመለከተ**

በዚህ ዓለም በድንበር የሚገናኙ የተለያዩ ሃገራት አንዱ የአንዱን ቋንቋ ይናገራሉ። ለምሳሌ፤ ቤልጂየምን ብንመለከት፣ ፈረንሳይና፣ ደች፣ ጀርመንኛ የሚናገሩ ሕዝቦ አሏት። ነገር ግን የቤልጂየም ዜጎች እንጂ ቋንቋውን በመናገራቸው የፈረንሳይ፣ ጀርመን ወይም የኔዘርላንድ ዜጎች አይደሉም።

በኢትዮጵያ ውስጥም በድንበር የሚዋሰኑ ጠቅላይ ግዛቶች፣ አፋሩ ትግርኛና አማርኛ ይናገራል፤ ትግራይም አማርኛና ትግርኛ ይናገራል፤ አማራውም ኦሮምኛና ትግርኛ፣ አርጎብኛ፣ ጉራጌኛ ይናገራል። በቋንቋ ድንበርን ለመወሰን ፈጽሞ አይቻልም። ተስፋፊው ተሓህት/ህወሓት ግን የታላቋን የትግራይ ሪፓብሊክ ለመፍጠር፣ የበጌምድር ጠ/ግዛትን እና የወሎ ጠ/ግዛትን ለም መሬቶች ትግርኛ ይናገራሉ በሚል ቁንጽል አስተሳሰብ በጉልበቱ መሬት ነጥቋል። **የሰሜን በጌምድር፣ወልቃይት፤ ፀገዴ፣ ፀለምት ፣ ሁመራ፣ ባህላቸውና ቋንቋቸው አማራ ነው።** ይህም ለብዙ ዘመናት እየዳበረ የመጣ ሲሆን፣ በተከዜ ወንዝ ዳር የሚኖሩ ዜጎች ትግርኛ መናገር ቢችሉም ዋናው ቋንቋቸው አማርኛ ነው። ሙሉው የዘር ሃረጋቸውም አማራ ነው። ስለሆነም እነዚህ ዜጎች የአማራ ሕብረተሰብ አካል ናቸው። ከትግራይ ሕብረተሰብ ጋር የሚያገናኛቸው ኢትዮጵያዊነታቸው ነው። በጋብቻ በመተሳሰር በሰላምና በፍቅር የኖሩ፣ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኮሩ ህዝብ ናቸው። በዚህም ምክንያት የትግራይ ህዝብም በበጌምድርና በወሎ ህወሓት የፈጸመውን ተስፋፊነት አልተቀበሉትም። በእነዚህ ሶስት ጠ/ግዛቶች፣ ማለትም በጌምድር፣ ትግራይና ወሎ የመሬት ይገባኛል የድንበር ክልል ተነስቶ አያውቅም። የሚነሳበት ምክንያትም የለም።

**የሕግ መሰረት**

እነዚህ ከበጌምድር ጠ/ግዛት በተሓህት/ህወሓት የተነጠቁት መሬቶች፣ ወልቃይት፣ ፀገዴ፣ ፀለምት፣ ቃፍታ፣ ሁመራ፣ ከወሎ ጠ/ግዛት ደግሞ ደቡብ ወሎ የተነጠቁት ቦታዎች ሕገወጥ ናቸው። ተስፋፊው ተሓህት በፕሮግራሙ መቅድም በሚለው አርእስት ያካተተው **የትግራይ ቦታዎችናቸው የሚለው የትግራይ ህዝብ ከመጀመሪያው፣ ከ1969 ጀምሮበቁርጠኝነትየተ ቃወመው ነው።** እኛን ከህዝቡ በመነጠል ችግር እንዲፈጠር አታድርጉ፤ የምትሉት መሬት በታሪክም የትግራይ አልነበረም ባለበት ጊዜ ነበር **"ትግራዋይ ሸዋዊ"** የሚል ስም የሰጡት። ህዝብ ያልተቀበለው ተስፋፊነት ደግሞ አምባገነን እና ፋሽስትነት ነው። ስለሆነም በሕግ ተቀባይነት የለውም። ተሓህት/ህወሓት በጉልበት የነጠቃቸው መሬቶች ካለምንም ውጣ ውረድ ወደ ቀድሞ ይዞታቸው ይመለሳሉ። ህዝብ በጠራራ ጸሓይ መሬቱ አይነጠቅም አይፈናቀልም።

**በህዝብ ሬፈሬንደም ይወሰናሉ፣ ለምን?**

በካርታ "ሀ" ላይ የተመለከተውን ታሪካዊ የሚያደርገው፣ በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት ተቀብለውት የጸና ሆኖ ብዙ ዘመናት ያስቆጠረ ስለሆነ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ አምኖበት የተቀበለው፣ በምንም መልኩ የድንበር ግጭትና ኹከት ያልፈጠረ፣ ዜጎች ሁሉ አምነውበትና ኮርተውበት ኢትዮጵያውያዊነታቸውን አጠናክሮና አቅፎ የተጓዘም ስለሆነም ነው።

አንዳንድ የተሓህት/ሀውሓት አመራርና ነባር አባላቱ የድንበሩ ጉዳይ በህዝበ ወሳኔ ይፈታ የሚሉ አሉ። ይህ በተሓህት/ህወሓት የተፈጸመው የመስፋፋት ጉዳይ ሕገወጥ ነው። የሰሜን በጌምድር መሬት፣ የደቡብ ወሎ መሬት ለድርድር ሳይቀርቡ በቀጥታ ወደ ቀድሞ ግዛታቸው ይመለሳሉ። ለህዝበ ውሳኔ ይቅረብ ማለት ፌዝና ቀልድም ጭምር ነው። ስለሆነም ህዝበ ውሳኔ ሕገወጥ ነው። **ፀገዴ፣ ወልቃይት፣ ፀለምት፣ ሁመራየበጌምድር (የጎንደር) ግዛት ናቸው። በወሎም፣ ወልዲያ፣ አፍላደራ፣ ራያና ቆቦ፣ አላማጣ የወሎ ጠ/ግዛት ናቸው።** የወያኔ ህወሓት አመረራርና አባላቱም ጭምር ይህንን አምነው መቀበል ግዴታቸው ነው።

**የደረሰው የዘር ማጥፋት ወንጀል**

ተሓህት/ህወሓት ሲፈጠር ተስፋፊነትን የፖሊሲው አቋም አድርጎ የተነሳ ድረጅት ነው። 5ኛ ፕሮግራሙን እንመልከት። ተስፋፊነት ደግሞ ፋሽስት፣ አምባገነን፣ ጨካኝ፣ ምህረት የለሽነው። ተፈጥሯዊው ባህሪውም ስለሆነ በዚሁ ነው የሚያድገው።

ተሓህት/ህወሓት ታህሳስ 1972 በቀጥታ የዘመተው ወደ ሰሜን በጌምድር ነበር። ዘመቻው ሰላማዊ ኢትዮጵያውያን የአማራ ዜጎችን ለማጥፋት የወጣ እቅድ ነው። በትግራይ ውስጥም አማራ ደመኛ ጠላትህ ነው ሲሉት፣ አማራ ለትግራይ ጠላት አይደለም፣ ወንድማችን ነው፣ በጋብቻና በዘር ደማችን የተቀላቀለ ኢትዮጵያዊ ነን በማለት በቆራጥነት አቋሙን የገለጸ ህዝብ ነው። "የትግራይ የሸዋ" በሚል ከገጠሩ ጀምሮ እስክ ከተሞች የግድያ እልቂት የሚፈጸምበት ጊዜም ነበር። የትግራይ ህዝብ አማራ ወንድሜ፣ እህቴ፣ ልጆቹ ልጆቼ፣ ሁላችንም የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች ነን በማለቱ በስንት ሺህ የሚቆጠር ህዝብ በህወሓት 06 ሓለዋ ወያነ እየገባ በጥይት ተደብድቦ ከባድ መስዋእትነት የከፈለ የአማራው አጋር ኢትዮጵያዊ ነው።

ቀጣዩን በገፅ 5 ይመልከቱ

## ከገፅ 4 የዞረ ..... የህወሓት ተስፋፊነት

ወያኔ ህወሓት ወደ ሰሜን በጌምድር ሲዘምት ዋናው አስተባባሪ ሆኖ እልቂቱ እንዲፈጸም ያስተባበረው የድርጅቱ ሊቀመንበር ስብሃት ነጋ ነበር። ከስብሃት ነጋ ጋር በመተባባር በተግባር የዘር እልቂት እንዲፈጽሙ የተመደቡት የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ደግሞ፣ **አርከበ እቁባይ፣ ስዩምመስፈን፣ ዘርአይ አስገዶም፣ ስየ አብርሃ** ናቸው። በእልቂቱ የታሳተፉ ተዋጊ ሃይሎች የተመሩት ደግሞ፣ **በሳሞራ የኑስ፣ ተከስተ እስጢፋኖስ፣ታደሰ ወረደ፣ መኮንን አሊሱም** ሲሆኑ፤ **ክርቢት** ተብለው የሚታወቁት ሽብርተኛ ጋንታ የተመሩት ደግሞ፤ **በሻሸይ በላይ፣አሰፋ ማሞ፣ ጸጋይቆማጥ፣ መሃሪ፣ ዳሳ ጉግሳ** ነበሩ። አምስተኛ ክርቢት ደግሞ የተመራው በአርከበ እቁባይ ሲሆን፣ ስምሪታቸው በፀገዴ፣ ወልቃይት፣ ፀለምት ነበር። እዚህ የሚኖረው ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን ነው። እኛ በታሪክ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣን አማሮች ነን በማለታቸው፣ በቀንና በሌሊት እሳተ ነበልባል ወረደባቸው። በስብሃት ነጋ በሚመራው የህወሓት ሰራዊት ከያሉበት እየተለቀሙ በጥይት እየተደበደቡ አለቁ። ሃብት ንብረታቸው፣ እንቁላል፣ ዶሮ፣ የጋማ ከብት፣ ያፈሩት ንብረት ሁሉ በህወሓት እየተዘረፈ ወደ ትግራይ እየመጣ የሰራዊቱ ቀለብ ሆነ። ቤት ፈረሰ፣ ወላጆች፣ ህፃናትን ጨመሮ በህወሓት አለቁ። ቤተሰቦች እየተሰበሰቡ እቤት ወስጥ እየታጎሩ አርከበ እቁባይ በሚመራው ክርቢት እሳት እየተለቀቀባቸው በእሳት አጋይተው ጨረሷቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ፤ **በብስራት አማረ** የሚመራው ጨካኝና አረመኔ ሰራዊት፣ የቡድኑ አባላት፤ **አሰፋ ጉሬዛ፣ ሃይሉ በርሄ፣ልኡል በርሄ፣ ዘርአይ ይህደጎ፣ ካህሳይ ቆራጽ፣ ዘውዱ፣ገብረዮሃን** ለህወሓት የስለላ ሥራ ወልቃይት ፀገዴ ተሰማርተው ነበር። በፀለምት በኩል ደግሞ **በዘአማኑኤልለገሰ** የሚመራና ተጠሪነቱ ለብስራት አማረ የሆነ ቡድን ተሰማርቶ ነበር። የቡድኑ አባላት፣ **አደም፣ ታደሰ 06፣ ታደሰ መሰረት፣ ተስፋየ አፅብሃ(አፍርሰው)፣ መሃመድ፣ ፍሬ ጎይትኦም (ሴት)** ነበሩ። ይህ በዚህ እንዳለ፣ ሃለዋ ወያኔ እያስገቡ መግደል ስለሚመቻቸው፣ ለወልቃይት ፀገዴ፣ ፀለምት አመቺ የሆኑ ሃለዋ ወያኔ ተከፈቱ። እነሱም፣

ፍየል ውሃ ፀገዴ፣ በክንፈ ገ/መድህን የሚመራ፣

ባኽላ ሳሞረ፣ የፀገዴ ዳር፣ በሙሉጌታ ወዛም (ማይዶ አስከን) ዛሬ በአሜሪካ የሚኖር፣

ሱር ለፀለምት አቅራቢያ፣ በአበበ ተክለሃይማኖት የሚመራ (የአየር ሃይል አዛዥ ጄነራል ነበር)

የወልቃይት ፀገዴ ፀለምት ህዝብ በነብስራት፣ አማራው በቀንና በሌሊት እየታፈነ በሶስቱ ሃለዋ ወያኔ እየገባ በአማራው የሰሜን በጌምድር ህዝብ የዘር ማጥፋት ወንጀል ህወሓት በመፈጸም ላይ እንዳለ፣ ቦታው በመጣበቡ ምክንያት ሌላ ሃለዋ ወያነ መጀመሪያ በሃሰን ሹፋ የሚመራ ሃለዋ ወያነ የአማራው ሕይወት ተቀጠፈ፤ በጅምላ ጉድጓዶች እየገቡ በፍየል ውሃ፣ በባኽላ፣ በሱር፣ በገሃነብ፣ በህወሓት ጥይት እየተደበደበ ያለቀው ህዝብ ቤት ይቁጠረው። መሬቷና በአካባቢው ከሞት የተረፈው ምስክርነትይሰጥበታል። ተሓህት/ህወሓት የአማራውን ህዝብ ዘር ማጥፋት የጀመረው ከ1969 መጀመሪያ ቢሆንም በከፋና አሰቃቂ መልኩ የጀመረው በ1972 ታህሳስ ሲሆን ለረጅም አመታት ግድያው ቀጠለ።

ከዚህ የዘር ማጥፋት እልቂት ከደረሰበት የወልቃይት ፀጋዴ ፀለምት ህዝብ አሁን በእድል ከሞት ተርፎ ቤተሰቦቹ ያለቁበት ዜጋ፣ በዛን ጊዜ የህወሓት አመራር ጠላቶቹ እነማን ይሆኑ? የሚል አእምሮውን የሚረብሹ ጥያቄዎች አሉ። ስለሆነም እዚያ የነበሩ የተሓህት/ህወሓት መሪዎች እነሆ ተቀበሉ። ጊዜውም ከ1967 እስከ 1977 ነበር።

ስበሃት ነጋ፣ የህወሓት ሊቀመንበር ፖሊት ቢሮ

አረጋዊ በርሄ፣ ወታደራዊ አዛዥ ፖሊት ቢሮ

ግደይ ዘርአፅዮን፣ የህወሓት ም/ሊቀመንበር ፖሊት ቢሮ፣ ፕሮግራሙን ያልጠበቀ

አባይ ፀሃየ፣ ፖለቲካዊ ጽ/ቤት ፖሊት ቢሮ

ሥዩም መስፈን፣ የውጭ ጉዳይ ሃላፊ ፖሊት ቢሮ

መለስ ዜናዊ፣ የፖለቲካ አዘጋጅ ማ/ኮ

አውአሎም ወበዱ፣ የሪጅን 1-2 ሃላፊ ማ/ኮ

አርከበ እቁባይ፣ ወታደራዊ ማ/ኮ

ስየ አብርሃ፣ ወታደራዊ ማ/ኮ

ዘርአይ አስገዶም፣ ከተማ ግንኙነት ማ/ኮ

ተወልደ ወ/ማርያም፣ የገጠር ግንኙነት ማ/ኮ በህመም ምክንያት ሱዳን የሄደ

ገብሩ አስራት፣ የሪጅን 3 ሃላፊ ማ/ኮ

አስፍሃ ሃጎስ፣ የውጭ ጉዳይ ማ/ኮ

አታክልት ቀፀላ፣ በአመራሩ የተገደለ ማ/ኮ፣ በ1971 የተገደለ

ጻድቃን ግ/ተንሳይ፣ ወታደር ማ/ኮ

ከዚህ የዘር ማጥፋት ወንጀል፣ የአማርኛ ቁንቋ የአማራው ገዢ መደብ ቋንቋ ስለሆነ አብሮ መጥፋት አለበት ተብሎም ከዘመቻው አንዱ ሆነ። ከዚህ በተጨማሪ፣ ክርስትና ሃይማኖት ተከታይ በመሆኑ ኢትዮጵያዊነት የሚለው ስር የሰደደ እምነት አብሮ ይጠፋል ሲሉ ነበር።

**<u>የህወሓት ፋሽስት ቡድን ኢትዮጵያን እንደተቆጣጠረ</u>**

ከዚህ ቀጥዬ የማቀርበው፣ እኔ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ በወቅቱ የነበርኩት አዲስ አበባ ውስጥ ነበር። እነሱ ኢትዮጵያን ወረው ሲቆጣጠሩ ደግሞ ዩጋንዳ፣ ካምፓላ ስለነበርኩ የማቀርበው ሃተታ በትግሉ ወቅት ጓዳኛዬ የነበረ፣ በ1968 በተሓህት አብረን የተሰለፍን ግለሰብ የነገረኝን ነው። ገና ከመነሻው ጀምሮ የጋንታ መሪ፣ የሃይል መሪ፣ የባታልዮን መሪ፣ የብርጌድ መሪ፣ የክፍለ ጦር መሪ፣ እየሆነ የመጣ በትግሉ ታዋቂ የነበረ ታጋይ ነበር። ኢትዮጵያን እንደተቆጣጠሩ፣ የሽግግር መንግሥት ተብሎ ሲቋቋም በጸረ-መለስ ዜናዊና ስብሃት ነጋ ተፈርጄ ህዳር 1984 ተባረርኩ ያለኝ የህወሓት ታጋይ የነበረ ነው። ይህ ግለሰብ ከህወሓት ሰራዊት ብቻውን ሳይሆን በርካቶች መባረራቸውን ነግሮኛል። አሁን የምተዳደረው በግሌ በአነስተኛ ንግድ ነውም ብሎኛል። የተገናኘነው ዩጋንዳ፣ ካምፓላ ለግል ሥራ በመጣ ጊዜ ነበር። ወሩና ዓ.ምን ጭምር እቤቴ እንደገባሁ በማስታወሻ ይዤው ነበር። ህወሓት በኔ ላይ በዙ ችግሮች እየፈጠረብኝ የነበረበት ጊዜ ስለነበር፣ እንኳን ለማነጋገር ለመቆም እንኳን አእምሮዬ ሊቀበልልኝ አልቻለም። እሱም እንደተጠራጠርኩት ስላወቀ፣ እኔን አትጠራጠረኝ፣ በኔ ላይ የፈጸሙብኝን ብነግረህ ታለቅሳልህ ሲለኝ በመጠኑም ቢሆን ተቀበልኩት።

የተገናኘነው ሚያዚያ 1985 ነበር። ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር ምንም ችግር ሳይገጥመን ካለ ምንም ጦርነት ከትግራይ በመኪና ተጭነን አዲስ አበባ መጥተን ነበር። ሃገሪቷ በእጃችን በወደቀችበት ጊዜ በየመንገዱና በየቦታው የሃገሪቷን ሃብትና ንብረት ዘርፈናል። ደርግ ዘራፊ ይመስለኝ ነበር። ነገር ግን አንዲት ብር ሳትነሳ ያገኘነው ባንክ ቤቶች፣ የመንግሥት ግምጃ ቤቶች፣ ያለውን ገንዘብ ጠራርገን ነበር የወሰድነው። አዲስ አበባ ስንገባ ሁለት ክፍለ ጦሮች ባንክና ማንኛውንም የገንዘብ ተቋሞች እንድንጠብቅ ከተመደቡት አንዱ የኔ ክ/ጦር ስለነበር፣ የህወሓት አመራር በቀንና በሌሊት ፖሊት ቢሮ አመራር የበላይ ሆነው የሚቆጣጠሩት ስብሃት ነጋና አዲስ አበባ ስንገባ ለሁለት ቀናት ለንደን የቆየው መለስ ዜናዊ ሆነው ለዘርፊያ ተሰማሩ። **በዝርፊያው የተሰማሩት የፖሊት ቢሮ አባላትም፣ ጻድቃን ገብረተንሳይ፣ አርከበ እቁባይ፣ አውአሎም ወልዱ፣ክንፈገብረመድህን፣ ስየ አብርሃ፣ አበበ ተ/ሃይማኖት፣ አባይ ፀሃየ፣ የማነ ኪዳነ (ጃማይካ) በዋናነት የሃገር ሃብት፣ገንዘብ፣ ወርቅና ልዩ ልዩ ውድቅርሳቅርስ ዘርፈዋል።** የተዘረፈው ሃብትም መለስ ዜናዊ በሚኖርበት ምኒሊክ ቤተ መንግሥት ተከመረ። እኛም ዘርፈናል በማለት የጀመረውን ጨዋታ ቀጠለ። ይህ የትግል ጓደኛዬ በአድዋ አውራጃ ቢወለድም አብዛኛው ቤተሰቦቹ ጎንደርና አዲስ አበባ ይሚኖሩ ናቸው። የትምህርት ደረጃው ከአንደኛ ደረጃ ባይዘልም በኢትዮጵያ ላይ ጥሩ አመለካከት እንዳለው ከፊቱ ይነበባል። ከአጫወተኝ ሁሉ ትኩረት የሰጠሁት፤

1ኛ፣ የህወሓትፖሊት ቢሮ ኢትዮጵያን እንደሚቆጣጠርና እንደሚመራ የአሜሪካና የእንግሊዝ መንግሥታት በእርግጠኝነት ሲናገሩ፣ የኢትዮጵያ ምድር ጦር፣ አየር ሃይል፣ ባህር ሃይል በቀላሉ እንደማይሸነፉ ያውቁ ስለነበር፣ ሁለቱ መንግሥታት ይጨነቁ ስለነበር፣ በርካታ የጦር መሳሪያ ለህወሓትይሰጧቸው ነበር።

2ኛ፣ የህወሓት የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት ተብሎ ኢትዮጵያን ለመምራት ስለማይችል በፍጥነት ስማቸውን እንዲለውጡ ማድረግ። በዚህ መሰረትም የህወሓት ፖሊት ቢሮ፣ **መለስዜናዊ፣ ስብሃት ነጋ፣ አባይ ፀሃየ፣ ሥዩም መስፍን፣ገብሩ አስራት፣ ስየ አብርሃ፣ አለምሰገድ ገ/አምላክ፣ አርከበ እቁባይ፣ ጻድቃን ገ/ተንሳይ፣ አበበ ተክለሃይማኖት፣አውአሎምወልዱ፣ አረጋሽ አዳነ፣ ተወልደ ወ/ማርያም** ህዳር 1982 መቀሌ ከተማ ተሰብስበው የሚፈለገው ስም ለማውጣት አራት ቀን ተዘግተው በጭንቀት ላይ ቆዩ። በመጨረሻም ተወልደ ወ/ማርያምና አለምሰገድ ገ/አምላክ የመጨረሻ አማራጭ ብለው ያቀረቡት ስም፣ "የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር" (ኢህአዴግ) እንዲባል ፖሊት ቢሮ ተቀብሎ አጸደቀው። እንደ ወጥ ማጣፈጫ የሚጠቀሙበት ብአዴን በግንባሩ ውስጥ ከተቀላቀለ ኢህአዴግ አስተማማኝና ተቀባይነት ያለው ስም ይሆናል ተባለ። ውሳኔውን እንግሊዝና አሜሪካም ተቀብለውታል። ብአዴን የተጨመረው አማራ ብሄር ሆኖ፣ "ህዝቦች" የምትለው ቃል ስትሸፍን፣ 'አብዮት' የምትለው ቃል ደግሞ ወያኔን ትሸፍናለች። የህወሓትን የበላይነትንም ታረጋግጣለች።

በሌላ መልኩ ደግሞ፣ **ህዝቦችየሚለው ቃል የኢትዮጵያን ህዝብአንድ ኢትዮጵያ ሳይሆን በዘፈቀደ የተሳባሰበ ነው ለማለትና በዘርና በቋንቋ ከፋፍለውለመግዛትየሚጠቀሙበት፣ለሥልጣናቸው እድሜ ማራዘሚያ የሚያደርጉበት ነው።**

3ኛ፣ ህወሓት በሚከተለው ፖሊሲ መሰረት የአሰብ ወደብ የኢትዮጵያ አለመሆኑ ሻእቢያም የኤርትራ መሬትና ወደብ አይደለም፤ የኢትዮጵያ ነው፣ በማለት ስለአረጋገጡ አሰብን ወደ ኢትዮጵያ አካለለች። እንግሊዝ ሃገር ልካችሁ ካርታችሁን አዘጋጁ የሚል ሃሳብም ቀርቦላቸዋል። ፖሊት ቢሮው በሙሉ ወደ እብደት ወሰዳቸው። **አሰብ የኤርትራ እንጂየኢትዮጵያአይደለም፣ አሰብን አናካትትም በማለት፣ በተለይም ስብሃት ነጋ፣መለስ ዜናዊ፣ ስየ አብርሃ፣ ስዩም መስፍን፣ብርሃን ገ/ክርስቶስ** ወዘተ በጥብቅ በማውገዛቸው የተነሳ እንግሊዝና አሜሪካም ሃሳባቸውን በመቀልበስ ኢትዮጵያን የባህር በር አልባ አደረጓት።

ይህንን ሁሉ የነገረኝ ይህ የቀድሞ ጓደኛዬ በንጹህ ልቦና ቢሆንም፤ እኔ ግን የህወሓትን እርኩስ ተግባር ስለማውቀው እስክንለያይ ድረስ መጠርጠሬ ከፍተኛ ነበር። ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ከማንም የማላገኘው እውነታ በመሆኑ ጥሩ ግንዛቤ ስጥቶኛል። ቀደም ብዬ የማውቀው የወያኔ ህወሓት ፀረ-ሃገርና ፀረ-ህዝብ የመሆኑን እምነቴን አዳብሮልኛል። በተለይ በአማራውና በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሚፈጸምውን ከፍተኛ ግፍ በጽናት አውግዞታል። ይህንን ካልኩ በኋል ወደ ወናው ሃሳቤ ስመለስ፣ ኢትዮጵያን እንደተቆጣጠረ፣ ፋሽስቱ ህወሓት ወያኔ ከሰኔ 1983 ጀምሮ ይፋ ያደረገው የኢትዮጵያ ካርታ ሃገር የሚያፈርስ፣ ህዝብ የሚበትን፣ ደመኛ ጠላትነቱን ያረጋገጠ መሆኑን ሁሉም ኢትዮጵያዊ በትክክል ያውቃል። ሆኖም፣ ሃሳቦቼን በገጽ 5 ስላስቀመጥኩት፣ በትኩረት እንመልከተው።

በ"ለ" ላይ የተመለከተው የኢትዮጵያ ካርታየተዘረዘሩት የህወሓት አመራር ያዘጋጀውና ሆን ተብሎ የተሰራና የተወጠነ ነው። ምክንያቱም፣

1ኛ፣ ካርታው እንደሚያመለክተው፣ የአማራውን ነገድ በታትኖ ዘሩን ለማጥፋት፣ ሰሜን በጌምድር ፀለምት፣ ፀገዴ፣ ወልቃይት፣ ቃፍታ፣ ሁመራ፣ በቀጥታ ወደ ትግራይ ግዛት ሲካለሉ ከወሎ ደግሞ ራያና ቆቦን፣ አላማጣን፣ አፍላ ደራ፣ ወልዲያ፣ እነዚህንም ወደ ትግራይ ግዛት ተካለሉ። ህወሓት ታላቋን ትግራይ በጉልበቱ ነጥቆ ፈጠራት። ወሎ አሁንም ቀድሞ ከነበረው ግዛቷ ከግማሽ በላይ ወደ አፋር ተካለለ። **የቀድሞዋ ጠ/ግዛት ወሎአሁን የለችም። የቀድሞዋ የበጌምድርጠ/ግዛት አሁን የለችም። ጎጃም፣ ሸዋ የሉም።** መተማና ሌሎች ወረዳዎች ወደ ቤኒሻንጉል ተካለዋል። ወያኔ ህወሓት ኢትዮጵያን እንደተቆጣጠረ አማራው ተበታትኖ መኖሪያ አልባ ሆነ። ከተወለደበት፣ ካደገበት ቀዬ ተባረረ። ከርታታና ማደሪያ የሌለው ሆኖ ለረሃብ፣ ለበሽታና ለብዙ ችግር ተዳረገ። የአማራው ህዝብ የሚኖርባት ክልል ከአንድ አውራጃ ያነሰች ሆነች። 2ኛ፣ ይህ የህወሓት የካርታ ክልል ኢትዮጵያዊነንት ፍጽሞ የሚያጠፋ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን አንድ ህዝብ ሆኖ በአንድነቱና በኢትዮጵያዊነቱ እንዳልኖረ ሁሉ፣ የህወሓት አመራር ይህን እውነታ በመጻረር ሃገርን በጎሳ፣ በቋንቋ ከፋፍለውታል። የቀድሞው የወያኔ ግፈኛው ፋሽስት መሪ የነበረው መለስ ዜናዊ በጻፈው <u>"TPLF's Strategies for Establishing its Hegemony and Perpetuating its Rule"</u> በሚለው ጽሁፍ የህወሓትን ዓላማ፣ ማለትም ሁሉንም የሃገሪቷን ጉዳይ በመቆጣጠር በቀጣይነት መግዛት ነው፣ በማለት አስቀምጦታል። ይሄንን ከገቡ ለማድረስ፣ ተቃዋሚ ሃይሎችን ማጥፋት፣ ነፃ ሚዲያን በማጥፋት የህወሓት ልሳናትን ማሳደግ፣ የህወሓት ደጋፊዎችን የሥራ እድል መስጠት፣ ቁልፍ የፕሮፓጋንዳ መሥሪያ ቤቶችን፣ ማለትም፣ ትምህርት ቤቶችን፣ የሃይማኖት ተቋማትን፣ የብዙሃን መገናኛዎችን፣ ጋዜጣ፣ መጽሔት፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን ወዘተ በመቆጣጠር የህወሓት አገልጋይ ማድረግ በማለት ጽፏል።

ቀጣዩ በገፅ 6 ይመልከቱ

## ከገፅ 5 የዞረ ..... የህወሓት ተስፋፊነት

በዋናናት ያስቀመጣቸው ደግሞ፣ ሃይማኖት ከአድሃሪው ህብረተሰብ ጋር የተቆራኙ ስለሆነ ያ መቋረጥ እንዳለበት ጽፏል። መለስ ዜናዊ አድሃሪ ህብረተሰብ የሚለው፣ ሙስሊሙን፣ ክርስቲያኑን፣ ወዘተ ነው። አስከትሎም፣ አድሃሪ፣ የለውጥና የእድገት ተቃዋሚ የሚላቸው ደግሞ መላውን ኢትዮጵያዊ ሲያንቋሽሽ ነው።

3ኛ፣ ያለፈው የአማራው ትምክህተኛ አገዛዝ ኢትዮጵያዊነት ዘልቆ የተዋሃደውና ከደመ ነፍሱ ጋር የተሳሰረ ነው። ይህንን ከህዝቡ ስነአእምሮ ነቅለን ለመጣል፣ በዘር፣ በጎሳ፣ በቋንቋ ማደራጀትና በዚህ ዓላማ የሚመሩ ድርጅቶችን መፈጠር ይላል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀስኳቸው የህወሓት መርሆዎች ገና ትግሉ እንደተጀመረ በኢህአፓ ላይ የፈጸመውን ወንጀል ማስታወስ ይበቃል። ኢህአፓ በኢትዮጵያዊነቱ ያመነና የተደራጀ፣ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ፣ ማለትም አፋን፣ አማራውን፣ ትግሬውን፣ ኦሮሞውን፣ ጉራጌውን፣ ኦጋዴኑን፣ ጋምቤላውን ወዘተ ያቀፈ፣ በዘር፣ በቋንቋ የማያማን ድርጅት ነበር፤ ለዚህም ነው በህወሓት የተደመሰሰው። በሃይማኖቶች ላይ እየተፈጸመ ያለው ግፍም ህወሓት ገና በትግሉ ጊዜ እስልምና እና ክርስትናን ለማጣፋት ታጥቆ የተነሳ እንደነበርና አሁንም በተግባር እያሳየው ያለ ጉድይ ነው።

ህወሓት ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተነሳውም ገና ከትግሉ መነሻ ጀምሮ ነው። እንደዋናው ዓላማው አድርጎ የተጠቀመበት ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት አስቀድመን አማራውን ማጥፋት ብሎ ከ1969 መጀመሪያ ጀምሮ ነበር። አማራውን ከትግራይ ውጡ በማለት የግፍ ግድያ የተፈጸመባቸው በዚህ ምክንያት ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ህወሓት የአማራን ዘር ማጥፋቱን ቀጠለበት፣ አሁንም አላቋረጠም።

የካርታው ዓላማ ህወሓት በዘር፣ በጎሳና በቋንቋ የከፋፈለው፣ የህወሓት መሪዎችን የግዛት እድሜአቸውን ለማራዘም ነው። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ የመግባቢያ ቋንቋ እንዳይኖር ለማድረግ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ አማርኛ የህዝብ መግባቢያ ቋንቋ በመሆኑ ይህንን በማጥፋት ኢትዮጵያዊነቱን እና አንድነቱን ለማጥፋት የሸረበው ተንኮል ነው። አዲሱን ትውልድ በጥቅማ ጥቅም በመያዝ ሊያዘናጋ ቢሞክርም፣ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ከዱሮው በበለጠ አማርኛ ቋንቋን በንግግርና በሥነጽሑፍ አስፋፍቶ በኢትዮጵያ ውስጥና ውጪንም ጨምሮ ኢትዮጵያዊነቱን በማጠናከርና በማቀፍ በበለጠ እድገት እየተራመደ ነው።

የወያኔ ህወሓት መሪዎች እቅድ ከሸፎ የኢትዮጵያ ህዝብ ይበልጥ ኢትዮጵያዊንቱን በማጠናከር ተከፋፍለን አንገዛም በማለት ሁሉም በሃይማኖቱ፣ ሙስሊሙ፣ ካቶሊኩ፣ ፕሮቴስታንቱ፣ አርቶዶክሱ አንድነት ፈጥረው የህወሓት ፋሽስቱን መሪዎች መፈናፈኛ ያሳጣቸው ጊዜ አድርገውታል። ከዚህም የተነሳ የመለስ ዜናዊ ጽሑፍ ውድቅ ሆኖ ቀረ። (ይህንን የመለስ ዜናዊን ጽሑፍ ያገኘሁት፣ Solidarity Movement for a New Ethiopia (SMNE) ድረገጽ ሲሆን፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቢያነበው የህወሓት ወያኔን ዓላማ ለማወቅ ያስችለዋል። አርእስቱ፣ "TPLF's Strategies for Establishing its Hegemony and Perpetuating its Rule" ነው።

**<u>በህወሓት አመራር የተፈጸመ የዘር ማጥፋት ወንጀል</u>**

ወደ ዘር ማጥፋት ከማቅናታችን በፊት ህወሓት ማን ነው የሚለውን በአጭሩ እንመልከት፤

1ኛ፣ ተሓህት/ህወሓት ከመጀመሪያ ጀምሮ ቅጥረኛ ነፈሰ ገዳይ ሆኖ የተፈጠረ፣ የባእዳንን ተልእኮ ለማስፈጸም የተደራጀ ድርጅት ነው። ጥቁር የአፍሪካ ናዚ።

2ኛ፣ ተሓህት/ህወሓት ተስፋፊ ድርጅት ነው። ታላቋን የትግራይ መንግሥት ለመመስረት ከበጌምድር ጠ/ግዛትና ከወሎ ጠ/ግዛት በህገወጥ መንገድ የነጠቀውን ቦታዎች እንመልከት፣

3ኛ፣ ተሓህት/ህወሓት ጠባብ፣ ዘረኛ፣ ፀረ-የኢትዮጵያ ሉአላዊነትና ፀረ-የኢትዮጵያ ህዝብ የሆነና በባእዳን የተፈጠረ ድርጅት ነው፣

4ኛ፣ ተሓህት/ህወሓት ሽበርተኛ ድርጅት ነው። ከ1969 ጀምሮ በጠራራ ፀሃይና በሌሊት ፈዳያን ብሎ ባሰለጠናቸውና በብስራት አማረ በመመራት ህዝብ ፈጁ፤

5ኛ፣ ተሓህት/ህወሓት ፀረ-ዲሞክራሲ፣ ጸረ-ሃይማኖት፣ ፀረ-ሕዝብ ሆኖ የተፈጠረ ድርጅት ነው። ይህ የማፊያ ድርጅት ኢትዮጵያን ለ24 ዓመታት እየገዛ ያለ ድርጅት ነው።

6ኛ፣ ተሓህት/ህወሓት የሰው ሃብት ቀማኛና የሃገር ታሪካዊ ቅርሶችን፣ የሃገር ሃብትን ዘራፊ ድርጅት ነው። ከዚህም አልፎ፣ ህዝብ እያፈናቀለ ኢትዮጵያን ለባለሃብት ባእዳን ሃገሮች በመሸጥ የተሰማራ ድርጅት ነው።

ይህ የባእዳን ቅጥረኛ ደርጅት ብዙ የከፋ ባህሪ ያለው ድርጅት ነው። ኢትዮጵያ ለዘመናት ብዙ ነገሥታትን ያሳለፈች፣ ዝነኛና ባለታሪክ ሃገር ናት። እንደ ወያኔ ህወሓት የመሰለ በታሪኳ አጋጥሟት አያውቅም። በ845 በዮዲት ጉዲት፣ በ15ኛው ክፍለ ዘመን በግራኝ መሃመድ አጥፊ ወራሪ ቢገጥማትም፤ ህወሓትን የመሰለ አረመኔና ፋሽስት፣ ኢትዮጵያን እና ህዝቧን ለማጥፋት የተሰማራ፣ ተወዳዳሪ የሌለው እኩይ ድርጅት ህወሓት ብቻ ነው።

**<u>የህወሓት የዘር ማጥፋት ዓላማና ተግባር</u>**

ህወሓት በአማራው ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀልን ስራዬ ብሎ የተያያዘው ከ1969 ጀምሮ ነው። በትግራይ ሰላማዊ ዜጎችና ታጋዮችንም በተመሳሳይ ሁኔታ ጎን ለጎን ማካሄዱን ቀጠለበት። ማሰቃየትና መግደል የተጀመረው በዚሁ ወቅት ነበር። ህወሓት በአሁኑ ወቅት ከሚጠቀምባቸው የዘር ማጣፍት ወንጀሎች መካከል ጥቂቶቹን እንመልከት፤

1ኛ፣ በየክልሉ በወያኔ ሰራዊትና ካድሬዎች ዜጎችን በግልጽ በመትረየስና በነብስ ወከፍ ጠመንጃ መጨፍጨፍ፣

2ኛ፣ ቤት ውስጥ አሰባስቦ በሩን በመዝጋት በእሳት ማጋየት፣

3ኛ፣ አፍኖ በመሰወር፣

4ኛ፣ ብርሃን እና ነፋስ በማይገባበት የጉድጓድ እስር ቤቶች ወስጥ በማጎርና በማጨናነቅ በተላላፊ በሽታ እንዲያልቁ ማድረግ። ዓይነ ስውር እንዲሆኑና አእምሮአቸውን በመሳት እንዲያብዱ ማድረግ፣

5ኛ፣ ኦሮሞ፣ አማራ ወዘተ በመሆኑ ብቻ ያለምንም ፍርድ ወህኒ ቤት ተሰቃይቶ እንዲሞት ማድረግ፣ ከዘመድ አዝማድ በማራቅ በሌላ ክልል ወስዶ ማሰር፣

6ኛ፣ በዘጠኙ ክልሎች በወያኔ የተቋቋሙት እስር ቤቶች ውስጥ ያሉ ታሳሪዎች ሲታመሙ ህክምና ማግኘት ስለማይፈቀድላቸው፣ ብዙ ታሳሪዎች በዚህ ምክንያት በበሽታ እንዲያልቁ ማድረግ፣

7ኛ፣ በፈዋሽ መድሃኒት ስም ጽንስ የሚያስወርድና የሚያመክን መድሃኒት በመስጠት ዘር ማጥፋት፣

8ኛ፣ የህወሓት መሪዎች እንደ ትልቅ ፖሊሲ አድርገው የያዙት ድርጊት፣ ወጣት ሴቶችና ወንዶች ሃገር ጥለው እንዲሰደዱ በማድረግ ሃገሪቱን የወደፊት ተረካቢ በማሳጣት የሥልጣን ጊዜአቸው እንዲራዘም ማድረግ፣

9ኛ፣ መሬት ነጠቃ፣ ህወሓት (ወያነ) ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ፣ በእድገትና ሰላም ስም ሕዝቡን በግዴታ ከተወለደበትና ከሚኖርበት ቀየው እያፈናቀለ ለባእድ ሃገሮች ለምና ሰፋፊ መሬቶችን በርካሽ በሊዝ በመስጠት ደሪውን ህዝብ፣ ለረሃብ፣ ለችግርና ለስደት መዳረግ። ይህ ግፈኛና ፋሽስት መንግሥት በኢትዮጵያ ህዝብላይ የፈጸመውና በመፈጸም ላይ የሚገኘው ግፍ ተቆጥሮ የሚያልቅ አይደለም።

**<u>የኦሮሞ ህዝብ በፋሽስቱ ገዢ ህወሓት የደረሰበት ግፍና ሰቆቃ</u>**

የኦሮሞ ህዝብ ትልቁ የኢትዮጵያ ነገድ ነው። የኦሮሞ ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ በሙሉ ልቡ የሚያምን እና የሚኮራ ዜጋ ነው። እናት ሃገሩን ኢትዮጵያን ከተለያዩ የጠላት ወራሪዎች በመከላከል ለብዙ ዘመናት ከኢትዮጵያዊ ወገኖቹ ጋር በመሰለፍ ደሙን ያፈሰሰና አጥንቱን የከሰከሰ ጀግና ህዝብ ነው። የኦሮሞ ህዝብ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ጠብቆ ለትውልድ ያስተለለፈ ህዝብ ነው። ልጆቹም በኢትዮጵያ በተለያዩ ወታደራዊ ክፍሎች ውስጥ፣ በውጭ ሃገር ከፍተኛ ትምህርት ተምረው፣ በአየር ሃይል፣ በምድር ጦር፣ በባህር ሃይል፣ በፖሊስ ወስጥ ተሰማርተው ሃገራቸውን ያገለገሉና የወገን ኩራትና አለኝታ የሆኑ ናቸው። ለአብነት ጥቂቶቹን ብንጠቅስ፣ ጄነራል ጃገማ ኬሎ፣ ጄነራል ሙሉጌታ ቡሊ፣ ጄነራል ደምሴ ቡልቶ፣ ጄነራል ረጋሣ ጂማ፣ ጄነራል ዋቅጅራ ሳርዳ፣ ጄነራል ገብረክርስቶስ ቡሊ፣ ጄነራል አስራት ብሩ፣ ጄነራል ቀልቤሳ ቤካ፣ ጄነራል አበበ ገመዳ የመሳሰሉትን ማንሳት ይበቃል። የኦሮሞ ህዝብ በተለያዩ የትመህርት መስክ ተሰማርተው በቀሰሙት እውቀትና ብቃት እናት ሃገራቸው ኢትዮጵያን ያገለገሉና በማገለጋል ላይ የሚገኙ ዜጎች ናቸው። የህወሓት መሪዎች ዛሬ የኦሮሞን ህዝብ ሽብርተኛ ብሎታል። ሽብርተኛው ግን ራሱ ህወሓት ነው። ህወሓት ኢትዮጵያን ወሮ ከተቆጣጠር ከ1984 መጀመሪያ አንስቶ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ይህ ነው የማይባል በርካታ ጥቃት ፈጽሞበታል። ግድያ ፈጽሞበታል፣ ሰቆቃ በመፈጸም አፍኖ አጥፍቶታል፣ ከየሥራው አፈናቅሎታል፣ ወንድ ሴት ሳይለይ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚማሩትን ወጣት ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው አባርሯል፣ በወታደርነት፣ በፖሊስ ወዘተ ተሰማርተው የሚያገለግሉትን የኦሮሞ ተወላጆች ከሥራ በማባረር ለችግር ዳርጓቸዋል፣ ከመሬቱ ተፈናቅሎ መሬቱን በእድገትና በልማት ስም ለውጭ ባእዳን አገሮች ሸጦበታል። ኢትዮጵያዊው የኦሮሞ ህዝብ አሁንም በህወሓት እየተሰቃየና እየተገደለ ነው።




ህወሓት የኦሮሞ ህዝብ በሙሉ የኦነግ ደጋፊና አፍቃሪ ነው በማለት በተለያዩ ቦታዎች በሺህ የሚቆጠሩ የኦሮሞና የሌሎች ነገድ ሰዎች የወያኔን እስር ቤቶች አጨናንቀውታል። እንዲሁም ማንም በማያውቃቸው **ድብቅ ወህኒ ቤቶች፣ ማለትም፣ ገሃንነብ (ቃሌማ)፣ ፍየል ውሃ የመሳሰሉ፣ በወልቃይት ፀገዴ የሚገኙና ከመሬት በታች ሁለት ሜትር ጥልቀት ባላቸው እስር ቤቶች በማጎር ያሰቃያቸዋል።** በአጠቃላይ እስር ቤቶች በሞላ በኦሮሞ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን ተጣበዋል። በወህኒ ቤቶች ካለ ፍርድና ፍትህ የሚማቅቀው የኦሮሞ ህዝብ ቁጥሩ ለማወቅ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ እስር ቤት ያልገባውም ኦሮሞም የህወሓት እስረኛ ነው።

**<u>አማራው</u>**

ወያኔ ተሓህት/ህወሓት ሲፈጠር ጀምሮ ኢትዮጵያዊውን የአማራ ህዝብ ለማጥፋት ያቀደ ነው። ይህንንም በፕሮግራሙ ላይ በግልጽ አስቀምጦታል። ተሓህት/ህወሓት ለውጭ ጠላት የሚውለውን 'ጠላት' የሚል ቋንቋ በአማራው ኢትዮጵያዊ ላይ መጠቀሙ የሃገርና የወገን ከሃዲዎች መሆናቸውን በግልጽ ያመለክታል። ወያኔ ተሓህት/ህወሓት አማራው ጠላቴ ነው በማለት ዘሩን ለማጥፋት የተነሳው ከ1969 ጀምሮ ሲሆን፣ አሁንም በአማራው ላይ መጠነ ሰፊ የሆነ ጥቃት እየፈጸመበት ይገኛል።

ተስፋፊው ህወሓት በ1967 ይዞት ወደ ደደቢት በረሃ በወረደው ፕሮግራሙ ላይ፣ ሰሜን በጌምድርን በሙሉ፣ ወልቃይት ፀገዴን፣ ሁመራን፣ ፀለምትን ወደ ትግራይ ለማቀላቀል መሬቱ ከአማራ መጽዳት አለበት በማለት በታህሳስ 1972 ገልጾታል። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት፣ በሰሜን በጌምድር ጾታን ሳይለይ፣ ከህጻናት እስከ ሽማግሌ ሰቆቃ ተፈጽሞባቸዋል። እቤት ወስጥ እየታጎሩ በእሳት ጋይተዋል። ወያኔ ህወሓት በተለያየ ዘዴ አማራ የተባለውን እያደነ የዘር ማጥፋት ድርጊት ፈጽሞበታል። ነፍሳቸውን ያተረፉት ለስደት ሲዳረጉ፣ የቀሩት ጥቂቶቹ ደግሞ ከቤት ንብርታቸው እንዳይፈናቀሉ በመፍራት የሚደርስባቸውን ስቃይ እየተቀበሉ እየኖሩ ነው።

ወያኔ ህወሓት ኢትዮጵያን ወሮ ከተቆጣጠረ 'ለ' ተብሎ እንደተመለከው ካርታ አይነት በማዘጋጀት ሆን ብሎ አማራውን በዘዴ ለማጥፋት ያቀደ ክልል የሚል ስምና ካርታ አዘጋጅቶ አማራውን በዚሁ አጠፋዋለሁ በማለት። ይህንንም ለማሳካት ከበጌምድር፣ ከወሎ፣ ከጎጃም ለም መሬቶችን እየመረጠ ወደ ትግራይ አካሏል። በነዚህ ለም መሬቶች ላይ ሲኖር የነበረው የአማራው ህዝብ አብዛኛው ተገድሏል፤ ቀሪውም ተሰዷል። ያማራው ሕዝብ በቀጥታና ዘዴ በተላበሰ መንገድ በወያኔ ህወሓት የግፍ እልቂት ተፈጽሞበታል። አለመታደል ሆነ እንጂ አማራ እኮ የኢትዮጵያ ጋሻ መታ ነው። ከ7ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የእናት ሀገሩ ኢትዮጵያ ዳር ድንበር ከወራሪ ጠላት እየተከላከል የመጣ ባለታሪክ ህዝብ ነው።

ቀጣዩን በገፅ 7 ይመልከቱ

# ከገፅ 6 የዞረ .....

## የህወሓት ተስፋፊነት

ወደ ሌላ ሃሳብ ከመግባታችን በፊት፣ ኢትዮጵያውያን በብሄር ብሄረሰቦች በመተባበር ለረጅም ዘመናት አብሮ የኖረና በዳበረ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ትስስር የቆየ ህዝብ ነው። አሁንም ወያኔ የሚፈልገውን መንገድ አንከተልም በማለት የተጠናከረ ህብረት ፈጥሮ በሙሉ ልቦና እና ኢትዮጵያዊነት ተሰባስበው እየተራመዱ ነው። እምቢ ለወያኔ አልገዛም እምቢ ለወያኔ የእድሜ መግዣ አልሆንም አማራ ነኝ አማራነቴም የሚነጥቀኝ ሀይል የለም። የሙብት ገዴታየም በህዝባዊ አመፅ አከብራሉ የኦሮሞ ህዝብም እንደዚሁ፡ ሌላው ኢትዮጵያዊ ህዝብም እንደዚሁ ተነስተዋ ግለቱ እየጨመረ። የወያኔ ህ.ወ.ሓ.ት ስርአት በዚች አመት ከርሰ መቃብሩ መግባቱ እይቀሬ ነው። ህዝብ ሀያል ነው፤ ህዝብ ከተነሳ የሚመልሰው ሀይል በዚች አለም የለም። የኢትዮጵያ ህዝብ አሁን የትቀጣጠለው ህዝባዊ አመፅ ሀገር አቀፍ ሆኖ ዳሩን እናድርሰው ነፃነታች እናስመልስ። ህ.ወ.ሓ.ት የመሰለ ክፉ ጠለት የለም።

**ጋምቤላ**

የጋምቤላ ኢትዮጵያዊ ዜጋም ልክ በአማራውና በኦሮሞው ህዝብ ላይ የሚደርሰው ዓይነት ሰቆቃ፣ እስራት፣ ግድያ፣ አፈና በወያኔ ህወሓት እየተፈጸመበት ዘሩ እንዲጠፋ እየተደረገ ነው። በአማራው ላይ የተፈጸመው በመድሃኒት ስም በግድ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጠው የማምከኛ መድሃኒትም ለጋምምቤላ ሕዝብ እየተሰጠ ዘሩ እየጠፋ ነው። በህወሓት የሚመራው ሽብርተኛ ስርዓት በጋምቤላው አኝዋክ ህዝብ ላይ **በጄነራል ጻጋዬ የሚመራው 43ኛው ክፍለ ጦር** በቀን ከ425 በላይ ገበሬዎችን፣ ሴቶችን እና ህጻናትን ገድሏል፣ ቤታቸው ተቃጥሏል፣ የተረፈውም ተሰዷል።

ይህ ሳይበቃው፣ የህወሓት ሽበርተኛ ስርዓት የጋምቤላ ህዝብ በእርሻ ላይ ተሰማርቶ የሚኖረውን ገበሬ የሚጠቀምበትን መሬት ለባእዳን ባለሃብቶች በመስጠት ለችግርና መከራ ዳርጓቸዋል። ዛሬ፣ የጋምቤላ ህዝብ በደረሰበት የዘር ማጥፋት ምክንያት ህልውናው የተመናመነ ሆኗል።

**ኦጋዴን**

ወያኔው የህወሃት ፋሽስት መሪዎች በኦጋዴን ህዝብ ላይም ሰፊ የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጽመዋል። ይህ ኢትዮጵያዊው ህዝብ የኦነግ አባል ነህ በሚል ሰንካላ ምክንያት በቀን እና በሌሊት እያደነ መጠን የሌለው ግድያ በመፈጸም ዘሩን አጥፍቷል። እቤት ውስጥ አሰባስቦ ቤቱን በመቆለፍ በህይወት እያሉ በላያቸው ላይ እሳት በመለኮስ በእሳት ጋይተው እንዲሞቱ አድርጓል። በሌላው ዘር ላይ እንደተፈጸመው አይነትም ከመሬታቸው እንዲፈናቀሉና እንዲሰደዱ አስገድዷቸዋል። አስገድዶ የማምከኛ መርፌና ኪኒን በመስጠት ዘሩ እንዲጠፋ አድርጓል። በየቦታው በማይታወቁና በሚታወቁ የወያኔ ህወሓት ወህኒ ቤቶች በበሽታ፣ በረሃብ ቤተሰባቸው በማያውቀበት ሁኔታ ታስሮ ዘሩ እያለቀ ነው።

**አፋር**

የአፋር ኢትዮጵያዊው ዜጋም ከላይ በተጠቀሰው ዓይነት በህወሓት የዘር ማጥፋት ደርሶባታል። ከመሬቱ ተፈናቅሎ በገዛ ሃገረ ስደተኛና ባይተዋር ተደርጓል።

**ትግራይ**

የትግራይ ህዝብ ገና ወያኔ ሲፈጠር ይዞት የመጣውን ፕሮግራም አልቀበልም በማለት፣ አማራው ደመኛ ጠላትህ ነው ሲባል፣ አማራው ወንድሜና እህቴ፣ ደሜና ስጋዬ ነው፣ አማራው ለትግራይ ህዝብ ጠላት አይደለም፣ እናንተ የወያኔ መሪዎች የምታወሩትና ከወገናችን ለማቃረን የሸረባችሁት ዘዴ ነው እንጂ፣ ሁለቱ ህዝቦች ለብዙ ዘመን በፍቅር፣ በሰላም ተጋብቶና በደም ተቆራኝቶ የኖረ ህዝብ ነው። አማራ የትግራይ ህዝብ ጠላት ሳይሆን ወንድምና እህት እንዲሁም ወገንና መመኪያ ነው። ትግራይ የኢትዮጵያ አካል እንጂ ነፃ ሃገር ነበረች የምትሉትን ተረታችሁን አንቀበለውም በማለቱ ከባድ መሰዋእትነት የከፈለ፣ ወገኔን አትንኩ በማለቱ "የትግራይ ሸዋ" የተባለ ህዝብ ነው። በዚህም ምክንያት በወያኔ ተሓህት/ህወሓት ከፍተኛ ጥቃት ደርሶባታል፣ ተገድሏል፣ ንብረቱ ተወርሶ ለከፋ ችግር ተዳርጓል።

በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ለደረሰው ለዚህ ሁሉ ጥቃት ተጠያቂዎቹ እነማን ናቸው? በኢትዮጵያ የዘር ማጥፋት ወንጀል በአማራው፣ በኦሮሞው፣ በጋምቤላው፣ በኦጋዴኑ፣ በአፋሩ፣ ወዘተ ላይ ተፈጽሟል። ከተወለደበት ካደገበት መሬት ተፈናቅሏል፤ በመድሃኒት እንዳይዋለዱና እንዳይባዙ ተደርገዋል፣ ንጹሃን ወገኖች በጅምላ ተገድለዋል፤ እንዚህ ሁሉ ከዘር ማጥፋት ድርጊት ያላነሱ ተግባሮች ናቸው። እስከ አሁን በወያኔ ህወሓት አመራር የተገደለው ኢትዮጵያዊ ቁጥር ከ9 ሚሊዮን በላይ እንደደረሰና ቁጥሩ በማደግ ላይ እንድሆነ ጥቆማዎች ያመለክታሉ። ከ34 ሚሊዮን በላይ ደግሞ ከመሬታቸውና ከትውልድ ቦታቸው ተፈናቅለው መኖሪያ አልባ በመሆን ለስደት፣ ለረሃብ፣ ለበሽታና ለሞት፣ ተዳርገዋል። ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) ነው። በእኩይ ተግባራቸው ታሪክ ሊረሳቸውና ሊፋረዳቸው የሚገባቸውን እንደሚከተለው አስቀምጣለሁ፤

**መለስ ዜናዊ፣ ቢሞትም የሰራው የወንጄል ድርጊት ተጠያቂ ያደርገዋል፣ አዜብ መስፍን፣ ስብሃት ነጋ፣ ሥዩም መስፍን፣ አባይ ፀሃየ፣ ስየ አብርሃ፣ አውአሎም ወልዱ፣ ገብሩ አስራት፣ ፃድቃን ገብረተንሳይ፣ አበበ ተ/ሃይማኖት፣ ሳሞራ የኑስ፣ ሃየሎም አርአያ፣ ብስራት አማረ፣ አርከበ እቁባይ፣ ፀጋይ በርሄ፣ ደብረጽዮን ገ/ሚካኤል፣ ቴዎድሮስ ሃጎስ፣ ቴድሮስ አድሃኖም፣ አባዲ ዘሞ፣ አረጋሽ አዳነ፣ ተወልደ ወ/ማርያን፣ ጌታቸው አሰፋ፣ ክንፈ ገብረመድህን፣ ገብረአብ ባርኖባስ፣ ዘርአይ አስገዶም፣ የማነ ኪዳነ ጃማይካ፣ ብርሃን ገብረክርስቶስ፣ ሙሉጌታ አለምሰገድ፣ ቢተው በላይ፣ አባይ ወልዱ፣ በየነ ምክሩ፣ አዲስዓለም ባሌማ፣ ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ፣ ታደሰ መሰረት በዋናነት ተጠያቂዎች ናቸው። በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በነዚህ ግለሰቦች ላይ እርምጃ መወሰድ አለበት።**

በተጨማሪ የኢትዮጵያ ህዝብ ሊፋረዳቸው የሚገቡ፤

ከ1967 ጀምሮ እስከ ዛሬ ያለው የማ/ኮሚቴ አባላት በሙሉ፣

ከላይ እስከታች ያሉት የደህንነት አባላት፣

በማእካላዊ ወህኒ ቤት ያገለገሉና የሚያገለግሉ በሙሉ፣

የህዝብ ግንኙነት ካድሬዎች በሙሉ፣

በዘራቸው ምክንያት የተሾሙት የህወሓት ጄነራሎች በሙሉ።

**የብአዴን ሥራ አስፈጻሚ የነበሩና የሆኑ፣**

**ደመቀ መኮንን፣ ገዱ አንዳርጋቸው፣ በረከት ስምኦን፣ አየለ ጎበዜ፣ ዓለምነው መኮንን፣ ብናልፍ አንዱዓለም፣ አህመድ አብተው፣ ተፈራ ደርቤው፣ አምባቸው መኮንን፣** በተጨማሪም የማ/ኮሚቴው አባላት በሙሉ።

**የኦህዴድ ሥራ አስፈጻሚ የነበሩና የሆኑ፣**

**አባዱላ ገመዳ፣ ሶፍያን መሃመድ፣ በዙ ዋቅቢያካ፣ አስቴር ማሞ፣ ወርቅነህ ገበየሁ፣ ሙክታር ከዲር፣ ዲሪባ ኩማ፣ አከይል አዚዝ መሃመድ፣ ኡመር ሁሴን፣ አለማየሁ ቶምሳ፣ ኩማ ደመቅሳ፣ ግርማ ብሩ፣** እነዚህና ጠቅላላው የማ/ኮሚቴው።

**የደቡብ ህዝብ ሥራ አስፈጻሚ የነበሩና የሆኑ፣**

**ሃይለማርያም ደሳለኝ፣ ሽፈራው ሽጉጤ፣ ሬድዋን ሁሴን፣ መኩሪያ ሃይሉ፣ ሲራጅ ፈጌሳ፣ ሽፈራው ተ/ሃይማኖት፣ አለማየሁ አሰፋ፣ ደሴ ዳልከ፣**እነዚህና ጠቅላላው የማ/ኮሚቴው።

ከላይ ከተጠቀሱት ባልተናነሰ ሁኔታ በዘር ማጥፋት መጠየቅ ያለባቸው፤ የትግራይ ክልል፣ የአማራ ክልል፣ የአፋር ክልል፣ የሶማሊ ክልል፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ የጋምቤላ ክልል፣ የደቡብ ክልል፣ የሃረሪ ክልል፣ የኦሮሚያ ክልል፣ የአዲስ አባባ አስተዳደር፣ የድሬደዋ አስተዳደርም ተጠያቂዎች ናቸው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የቅጥረኛ ቅጥረኛ ሆነው በማገልገል፤ የህወሓት ተባባሪ በመሆን የኢትዮጵያን ሉአላዊንት አፍርሰዋል፤ በዘር ማጥፋት ድርጊት ተካፋይ ሆነዋል፣ ኢትዮጵያውያንን ከመሬታቸው በማፈናቀልና በመግደል እንዲሁም ንብረታቸውን በመንጠቅ ከፍተኛ ግፍ ፈጽመዋል፤ ከወያኔ በመተባባር የማምከኛ መድሃኒት እየወጉ ዘር በማጥፋት ድርጊት ተሰማርተዋል፤ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን መንግሥት እንዲሸጥ በማድረግ ተባብረዋል፤ በየክልላቸው ድብቅ እስርቤቶችን በመሥራት ተቃዋሚዎችን እና ንጹሃን ዜጎችን ያለፍርድ አስረዋል፤ የኢትዮጵያን ህዝብ ሰብአዊ መብቱን በመንፈግ ለግፍና መከራ ዳርገውታል።

**ውድ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ!!!** ከትግራይ የመጣውና አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ፋሺስቱ ህወሓት ሃገራችንን ተቆጣጥሮ በቅኝግዛት መዳፍ ውስጥ ካደረጋት እነሆ ዛሬ 24 ዓመታት አልፈዋል። በነዚህ ዓምታት ውስጥ ኢትዮጵያ የባህር በር አልባ ሃገር ሆናለች፣ ለም መሬቷ ከሁመራ እስከ ሞያሌ ያለው የድንበር ሃገራችን ለሱዳን በምልጃ ለወያኔ ጥቅም እየተሰጠ ነው፣ህዝብ ሊፈናቀል ነው፣ ከሃገሩ ከተወለደበት ካደገበት ተፈናቅሎ የት ሊገባ ነው? ይህ የአማራ ጉዳይ ብቻ አይደለም፣ ሁሉንምየኢትዮጵያ ዜጋ የሚመለከት ነው፣ የኢትዮጵያዜጋ በሙሉ ካለአንዳች ልዩነት በአንድነት በመነሳትየሚፈለገውን የህይወት መስዋእትነት ከፍሎ፣ ኢትዮጵያ ሃገራችንን የመሬት ወረራ እናድን። ታሪካዊ መሬት፣ ለም መሬት አሳልፈን ለሱዳን ወራሪ መንግስት በወያኔ የባንዳ ስርአትኢትዮጵያበሱዳን አትወረርም። በየቦታው ያሉት ለም መሬቶች ለባእዳን ሃገሮች እየተቸበቸቡ ነው፣ በዚህም ምክንያት የሃገራችን ህዝብ መሬትና ሃገር አልባ በመሆን፣ ለረሃብ፣ ለእርዛት፣ ለበሽታና ለሞት ተዳርጓል፣ ግፉና በደሉ አሁንም ተጠናክሮ ቀጥሏል። ስለዚህ፣ ረሃብና በሽታ በየጊዜው እየተፈራረቁብህ እስከመቼ በባርነት ትኖራለህ? ነፃነትህ ያለችው በእጅህ ላይ ስለሆች እምቢ ለወያኔ፣ አሁንስ በቃኝ ብለህ ተነሳ፣ አሁን የተጀመረውን ህዝባዊ አመጽበሀይልና በግለት አጠናክር። የህዝብን ቁጣ ምንም ዓይነት ሃይል ስለማይቋቋመው ሆ ብለህ በመነሳት ሃይልህን በማሳየት ሃገራችን ኢትዮጵያን ነፃ አውጣ። የወያኔ ባርነት፣ ግድያ፣ ረሃብ፤ ስደትና ተመጽዋችነት ይብቃህ። ከኢትዮጵያዊ ዜግነትህ አልባ ሆነህ የባንዳ ልጆችና ባንዳዎች አገርህን እየዘረፉ፣ የኢትዮጵያን ሉእላዊነት እያፈረሱና እየሸጡ እያየህ እስከመቸነው ዝምታው? አሁንስ በቃ። ፋሽስቱን ወያኔ የተዘረጋውን ክንዳችንን እናሳርፍበት።

## የገነፈለ የህዝብ ቁጣ የሚገታው የለም



## ሆድ ይፍጀው

"የሆዴን በሆዴ"
አዝማሪ እንዳለው፤
ትርፍ ከመናገር
ይሻላል "ሆድ ይፍጀው"...
ታዛቢው ህሊና
ሁሉን እያየ ነው።

ከገፅ 1 የቀጠለ

# …… በብሔርተኝነት ስም

ይህ ሰው እስከዛች ቀን ድረስ ስለ አያቱ ኦሮሞነትም ሆነ ስለመጣበት ብሔር ወይም ጎሳና ማንነት በቅጡ አስቦ ወይም ትዝ ብሎት እንደማያውቅና ይህ ገጠመኙ ግን ከሚኮራበት ከኢትዮጵያዊነት ማንነቱ ባሻገርም ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ስለሰፏት ሕዝቦቿ ታሪክ፣ ባህል፣ ማንነትና ቅርስ ለማጥናት የማንቂያ ደወል ሆነኝ ሲል ነግሮኛል፡፡ በነገራችን ላይ ይህ ሰው በተለያዩ ጊዜያት ወደ ደቡብ አፍሪካ በስደት የገቡና ኖሮአቸውን በዛው ያደረጉ የኦሮሞ ተወላጆች ለደቡብ አፍሪካ መንግሥት የፖለቲካ ጥገኝነት ጥያቄ በሚያቀርቡበት ወቅት የተፈጠረውን እሰጥ አገባም እንዲህ ጨምሮ ተርኮልኛል፡፡

የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ሆኑ ስደተኞች ለፖለቲካ ጥገኝነት ብቁ የሚያደርጋቸውን ቅፅ በሚሞሉበት አጋጣሚ አብዛኛው የኦሮሞ ተወላጆች ዜግነት ወይም አገር በሚለው ክፍት ቦታ ላይ ‹‹ኦሮሚያ›› በማለት በመሙላታቸው የደቡብ አፍሪካ ‹‹ሆም አፌር ቢሮ›› የሥራ ባልደረቦች እኛ ‹‹ኦሮሚያ›› የሚባል አገር አናውቅም በማለታቸው በተነሳ ክርክር፣ እነዚህ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ የሆኑ የፖለቲካ ጥገኝነት ፈላጊዎች፣ ‹‹ኦሮሚያ በቀድሞዋ አቢሲኒያ በአሁኗ ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ስር ምትማቅቅ አገር ናት፡፡›› በማለት በማስረዳት ዜግነት በሚለው ክፍት ቦታ ላይ ‹‹ኦሮሚያ›› የሚለው ማንነታቸው እንዲሞላላቸው ቢጠይቁም ተቀባይነት በማጣታቸው እየጎመዘዛቸው ቢሆንም የማያምኑበትን የኢትዮጵያዊ ዜግነት በክፍት ቦታው ላይ ይሞሉ እንደነበር ይህ ሰው ጨምሮ ነግሮኛል፡፡

ይህንና ይህን የመሳሰሉ ብሔርን ማእከል ያደረጉ አሳዛኝ ገጠመኞች በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ አገር ተደጋግመው የሚከሰቱ መሆናቸው ደጋግምን ያየነውና የሰማነው እውነታ ነው፡፡ በአውሮፓ፣ በአሜሪካ፣ በአውስትራሊያና በደቡብ አፍሪካ ዛሬ ዛሬ በትግሬ፣ በአማራ፣ በኦሮሞ … ወዘተ ስምና ማንነት የራሳቸውን ወሰን ወስነውና አጥር ከልልው የሚኖሩና ይህና ያ ብሔር በእኔና በዚህ ብሔር ላይ ታሪክ ይቅር የማይለው በደል፣ ግፍና ጭቆና አድርሶብናል በሚል የየራሳቸውን የጭቆና ታሪክና የተጋድሎ ገድል ጽፈውና አጽፈው ያሉ፣ ከዚህም የተነሳ ደግሞ ለበቀል የሚፈላለጉና በጎሪጥ የሚተያዩ ሕዝቦች ኢትዮጵያ በምትባለው ምድር ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው፡፡

ይህን ከላይ በመግቢያችን የገለጽኩትን አሳዛኝ ገጠመኝ ወይም ታሪክ ለዚህ ጹሑፍ መግቢያ ይሆነኝ ዘንድ የመረጥኩት ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ ስለ ኢትዮጵያዊነትና ኦሮሙማ (ኦሮሞ ናሽናሊዝም) በተመለከተ ‹‹በገዳ ዶት ኮም›› እና በሌሎች በተለያዩ ድረ ገጾች ሰፋ ያለ ውይይትና ክርክር ተደርጎ ነበር፡፡ በዚህ ከስምንት የማያንሱ ማእከላቸውን አውሮፓና አሜሪካ ያደረጉ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና የኦሮሞ ምሁራን ባደረጉት ውይይትና ክርክር ከተሳተፉት ፖለቲከኞችና የኦሮሞ ምሁራን መካከል ዶ/ር በያን አሶቦና ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ይኸው የኢትዮጵያዊነትና የኦሮሙማ ሙግትም የፓል ቶክ ዋና የመወያያ ርዕስ ሆኖ ነበር፡፡ ይህ ውይይትና ክርክር ገና ሳይበርድና ሳይቋጭ ነበር በዛው ሰሞን ወጣቱ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁርና ተንታኝ ጃዋር ሙሐመድ ከአልጀዚራ የቴሌቪዥን ጣቢያ ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ ለዓመታት በዘለቀው የኦሮሞ ጥያቄ፣ የነፃነት ትግል ታሪክ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ትንታኔ የሰጠው፡፡ ጃዋር I am First Oromo. Ethiopia is imposed on me የሚለው አቋሙን ግልጽ ካደረገ በኋላ የኦሮሞን ታሪክና የኦሮሞን የዓመታት ጥያቄ በተመለከተ የፖለቲካ ተንታኙን የጃዋርን ትንታኔና አቋም በመቃወምም ይሁን በመደገፍ የተለያዩ ሐሳቦች መንሸራሸር ጀመሩ፣ አሁንም ድረስም እየተንሸራሸሩ ነው፡፡

ባለፉት ሰሞናትም በተለያዩ በይነ መረቦችና በማኅበራዊ ድረ ገጾች ላይም የጃዋርን ሐሳብ ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች በየበኩላቸው አቋማቸውን ለመግለጽ ሞክረዋል፡፡ አንዳንዶችም ስድብ ቀረሽ በሚመስል ጨዋነትና ቅንነት በጎደለው መንፈስ ጃዋር ባነሳው ሐሳብ ላይ የውይይት መድረኩን የሚያጠለሹና የሚበርዙ እሳቤዎችን ከስድብ፣ ከዛቻና ከማስፈራሪያ ጭምር ሲያዘንቡም ታዝበናል፡፡ ከዚህ ውጪ ደግሞ ሰብአዊ ፍቅር፣ ጨዋነትና ቅንነት በተሞላበት መንፈስ ከኦሮሞም ይሁን ከሌላ ብሔር ተወላጆች ዘንድ፣ ሚዛናዊ የሆነ፣ ከጭፍን ጥላቻና ከበቀል ስሜት በጸዳ መንፈስ ሐሳባቸውንና አቋማቸው የገለጹም ጥቂት ጸሐፊዎችና ተንታኞችም ብቅ ብቅ ብለው ነበር፡፡

እኔም በዚሁ ሰሞነኛ በሆነው የኦሮሞ ሕዝብን ታሪክና ጥያቄ በተመለከተ ለኦሮሞ ሕዝብ ነፃነትና መብት ቆመናል በሚሉ አንዳንድ የኦሮሞ ምሁራንና ፖለቲከኞች ዘንድ በኦሮሙማ (በኦሮሞ ናሽናሊዝም)፣ በኢትዮጵያ ታሪክና በኢትዮጵያዊነት ላይ በሚያነሷቸው አንኳር ሐሳቦችና በሚያራመዱት አቋሞቻቸው ዙሪያ ላይ ጥቂት የመወያያ ሐሳቦችን ለማጫር ወደድኩ፡፡

በእርግጥ ይህ ለውይይት ማጫሪያ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ አጭር ጽሑፍ የኦሮሞ ተወላጅ ምሁራንና ፖለቲከኞችን፣ አሊያም ደግሞ በኦሮሞ ሕዝብ ስም ተቋቋመው እየተንቀሳቀሱ ያሉ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ታሪክና በኢትዮጵያዊነት ላይ ያላቸውን አቋማቸውንና ለኦሮሞ ሕዝብ አለን ስለሚሉት የትግል አቅጣጫዎቻቸውን ለመተንተን፣ ለመተቸትና ለመገምገም አይደለም አነሳሱ፡፡ ይህን ለማድረግ እንሞክር ቢባል እንኳን በእነዚህ ጥቂት ገጾች ለመሞከር የሚታሰብ አይሆንም፡፡

ለዚህም እንደ ዋና ሆነው ከሚነሱት ዐበይት ምክንያቶች መካከል ደግሞ በኦሮሞ ሕዝብ ስም እየተንቀሳቀሱ ያሉ በዓላማም በአቋምም የተለያዩ ፓርቲዎች መኖራቸው፡፡ እንዲሁም እነዚሁ ፓርቲዎችም የኦሮሞን ሕዝብን ታሪክና ጥያቄ በተመለከተ የሚያራምዷቸው አቋሞችና ጥያቄዎች ‹‹ከባርነት ወይም ነፃነት›› ወይም ደግሞ ‹‹ከአቢሲኒያ/ከዛሬዋ ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ነፃ የመውጣት ጥያቄ ነው፡፡›› ከሚለው ፖለቲካዊ አቋም አንስቶ በተለያዩ የኦሮሞ ተወላጅ ምሁራንና ፖለቲከኞች ዘንድ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች ባሉ የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ፣ ባህል፣ እምነትና ቅርስ አኳያ ያሉት አመለካከቶችና ትንታኔዎች መንገዳቸው የየቅል መሆኑን ነገርዬውን ቀላል አያደርገውም ብዬ ስለምገምት ነው፡፡

ለአብነትም ያህል የኦሮሞን ብሔርተኝነት በእጅጉ ያራምዱና ‹‹የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄ የነጻነት ጥያቄ ነው፡፡›› ሲሉ የነበሩ አንዳንድ የኦሮሞ ምሁራንና ፖለቲከኞች በጊዜ ሂደት ኦሮሞ በኢትዮጵያ በቆዳ ስፋት ትልቁና የሕዝቡም ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ውስጥ ግዙፍ ሆነ ቦታ ሊሰጠው ይገባል፣ የኦሮሚፋም በኢትዮጵያ የፌዴራል መንግሥት ፖለቲካ አሥተዳደር ውስጥ የፌዴራል መንግሥቱ ቋንቋ መሆን የሚችልበት መንገድ ሊታሰብበት ይገባዋል፣ የሚሉ የተለሳለሱ አቋሞችን የሚያራምዱ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ፖለቲከኞችም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ብቅ ብቅ ማለታቸውንም ታዝበናል፡፡

ስለሆነም በዚህ ጽሑፍ የኦሮሞን ታሪክ፣ ባህል፣ ማንነት፣ የኦሮሞን የመብት ጥያቄና ትግል ተመለከተ በፊትም ሆነ በተለይም ደግሞ ከሰሞኑን የፖለቲካ ተንታኙ ጃዋር ሙሐመድ ባነሳው የኢትዮጵያዊነትና የኦሮሙማ አንኳር እሳቤዎች ላይ ተመርኩዤ ጥቂት ነገሮችን ለማለት ወደድኩ፡፡

እንደሚታወቀው ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት ውስጥ የእከሌ ብሔር ወይም ጎሳ በዚህኛው ብሔር ወይም ጎሳ ላይ ለፈጸመው በደልና ጭቆና በሚል ያልተወራረዱና ጊዜ እየጠበቁ ቦግ እልም የሚሉ ምሬቶችን፣ ቁጣዎችንና የበቀል ሰይፎችን በተለያዩ የአገራችን ክልሎች መከሰታቸውን ታዝበናል፡፡ ይህን እኩይ የሆነ የበቀል ሒሳብ በማወራረድ የተጠመዱ አንዳንድ ፓርቲዎች፣ ፖለቲከኞችና ግለሰቦችም ሆን ብለውና ያልተገባ ፖለቲካዊ ትርፍ ለማግበስበስ ሲባል እውነታን በማጣመም በሚጻፏቸውና በሚያጽፏቸው የተዛቡ የታሪክ ድርሳናትና ገድሎቻቸው፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ትናንትና ያልነበረ ዛሬም የሌለ ቅዠት ወይም ሕልም ነው እስኪባል ድረስ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በርካታ ትንታኔዎቻቸውን ሰምተናል፣ የዳጎሱ ጥናታዊ ጽሑፎቻቸውንም አስነብበውናል፡፡

በዚህ እነዚሁ የብሔር ፖለቲካ ጽንፈኞች፣ በቀልን ሰባኪዎች፣ የብሔራዊ መግባባትና እርቅ ተቀዋሚዎች በተጻፉ የተዛቡ ታሪኮችና ያልተወራረዱ የበቀል ሒሳቦች ከፉ ስብከት የተነሣም ለዘመናት ተዋደውና ተከባብረው፣ በጋብቻና በአምቻ ተሳስረው፣ እኔ ትብስ አንተ ትብስ ብለው የኖሩ ሕዝቦች የተሳሰሩበትን የአንድነት ድርና ማግ ለመበጠስ ሲባል የተደረጉ አያሌ ዘመቻዎችንም በዘመናችን በሐዘንና በግርምት ሆነን አስተውለናል፡፡

ዛሬም ድረስ ለኦሮሞ ሕዝብ መፍትሔው የእኔ የፖለቲካ አቅጣጫ ነው የሚሉ በርካታ የኦሮሞ ምሁራን፣ ፖለቲከኞችና ፓርቲዎች በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሆነው ለኦሮሞ ሕዝብ ይጠቅማል በሚሉት መንገድ የራሳቸውን አቋም በማራመድ ይጻፋሉ፣ ይወያያሉ፣ ይከራከራሉ፣ ይሟገታሉም፡፡

ይሁን እንጂ እስካሁኗ ቅጽበት ለኦሮሞ ሕዝብ ነፃነት፣ መብትና ጥቅም ቆመናል በሚሉት በበርካታ የኦሮሞ ፖለቲከኞች፣ ምሁራንንም ሆነ ፓርቲዎች ዘንድ ቢያንስ ባለፉት ሁለት ዐሥርተ ዓመታት የኦሮሞን ሕዝብ ታሪክና ጥያቄ በማስተጋባትና በመፍትሔ አቅጣጫዎችም ዙሪያ በሚያራምዱት አቋማቸው እርስ በርሳቸው የተለያዩና የተከፋፈሉ መሆናቸውን በተለያዩ አጋጣሚዎች ዐይተናል፡፡ በዋነኝነት የኦሮሞ ሕዝብን ጥያቄ ለመፍታት ከእኔ ወዲያ ለአሳር በማለት ሲምል ሲገዝት የነበረው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) በዕድሜ የሚያክለውና የሚስተካከለው ባይኖርም ዛሬም ድረስ በተለያዩ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ውስብስብ ችግሮች ተተብትቦ እየዳከረ ያለ ፓርቲ መሆኑን የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

በተጨማሪም ባለፉት ዓመታት በፓርቲው አመራሮቹ መካከል በተፈጠረ ልዩነትና ውዝግብ የፓርቲው ህልውና አበቃለት እስኪባል ድረስ የነበረውና አሁንም በያዝ ለቀቅ በፓርቲው ውስጥ የሚነሱት ወጀብና ዐውሎ ንፋሶች ዛሬም ድረስ ገና መፍትሔና መቋጫ ያገኙ አይመስሉም፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው፣ ነፃነትን የማወጅ፣ ሉዓላዊነትን የማስከበር፣ የማንነት፣ የታሪክና ፖለቲካ ጥያቄ ነው፣ በማለት ጽንፈኛ አቋሙን በሚያራምደው ኦነግና ደጋፊዎቹ ዘንድ ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በሸዋው ንጉሥ በምኒልክ ሰይፍ ተቀጥቅጦ በአማራ ታሪክና ማንነት ላይ የተገነባ ነው የሚለው መከራከሪያቸው አሁንም ድረስ በአቋም ደረጃ በግልጽ የሚንጸባረቅ ነው፡፡

ወጣቱ የፖለቲካ ምሁርና ተንታኝ ጃዋር ሙሐመድም ይህንኑ ሐሳብ በመድገም እንዲህ ብሎአል፡- ‹‹ … ኢትዮጵያን የመሠረታት የሦስትዮሽ ጦርነት ግብግብ ነው፡፡ በአማራው፣ በኦሮሞው፣ በትግሬው ግብግብ ውስጥ ወደ መጨረሻ ላይ በአመራር ስር የበላይነቱን የያዘው አማራው ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ አሁን የምናያት ኢትዮጵያ ማንነቷ በአማራ ባሕላዊ ሥርጭትና በአማራ ፖለቲካ የተገነባች ነች፡፡ … የኢትዮጵያ አገራዊ ማንነት የምንለውም የአማራ ባህላዊ ማንነት ነው፡፡›› ሲል ከኢትዮጵያ ታላቅ ሥልጣኔ፣ ታሪክና ከኢትዮጵያዊነት መንፈስ ወይም ማንነት ጋር የሚጣረስ ድምዳሜን ሰጥቶአል፡፡

ይህ ዓይነቱ ትንታኔ የኢትዮጵያን ታሪክ በአግባቡ ያለመረዳት ቀውስ ወይም ደግሞ ሆን ብሎ የታሪክ እውነታን የማዛባት ዘመቻ ነው የሚመስለው፡፡ ኢትዮጵያ የምትባለው ምድርና ሕዝቦቿ ትናንትና ከመቶ ዓመት በፊት ምኒልክና ተከታዮቹ በኃይልና በሰይፍ በሚፈልጓት ቅርፅና ይዘት ቀጥቅጠው የፈጠሯት እንጂ የሚለው መከራከሪያ ሐሳብ በምንም መንገድ ውኃ ሊያነሳ የሚችል ሐሳብ አይመስለኝም፡፡ ይህ ዓይነቱ አመለካከት ከሺሕ ዓመታት በፊት ጀምሮ በገናና ሥልጣኔዋና ታሪኳ በዓለም መድረክ ስሟ ገኖ የወጣውን፣ ከአፍሪካ አልፎ በሰሜን አሜሪካና በካረቢያን በባርነትና በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ተይዘው ሲማቅቁ ለነበሩ ሕዝቦች የነፃነት ምድር፣ የጥቁር ሕዝቦች ተስፋ ‹‹የጥቁር ሕዝቦች የከነዓን ምድር›› በሚል በሰቀቀንና በናፍቆት ሲያስቧትና ሲዘክሯት የኖረችውን ኢትዮጵያን ህልውና የመካድ ያህል የሚቆጠር ይመስለኛል፡፡

ኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት መንፈስ የነፃነት ተምሳሌት፣ የአንድነትና የፍቅር ኪዳን ሆኖ በብዙዎች ልብ ውስጥ ሲንቀለቀልና ለዘመናት ሲያበራ የኖረ እውነት መሆኑን መካድ አንችልም፡፡ ከአፍሪካ እስከ አሜሪካ፣ ካረቢያና ጃማይካ ይህ ኢትዮጵያዊነት መንፈስ በእውቁ የነፃነት ታጋይ በእነ ማርከስ ጋርቬይ፣ በሬጌው ንጉሥ በእነ ቦብ ማርሌይ፣ በእነ ፒተር ቶሽ፣ በአፍሪካውያኑ የነፃነት አባቶች፣ በእነ ጆሞ ኬንያታ፣ በንኩርማ፣ በማንዴላና በበርካታ የነፃነት ታጋዮች ዘንድ የሞራልና ወኔ ስንቅ ሆኖ ያገለገለ፣ ክቡር ታሪክ፣ ሕያው አሻራና ቅርስ መሆኑን መዘንጋት ከታሪክ ሐቅ ጋር መጣላት ነው የሚሆነው፡፡

ቀሪውን በገጽ 9 ይመልከቱ

ከገጽ 8 የዞረ

# ....... በብሔርተኝነት ስም

በተጨማሪም ለዚህችው በሺሕ ዘመናት ገናና ሥልጣኔዋ፣ ነፃነቷ፣ ታሪኳና ሉዓላዊነቷ ሲሉ በዐድዋ ጦር ግንባር ከወራሪው የአውሮጳ ኃይል ጋር አንገት ለአንገት ተናንቀው ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ለሕዝቦቿም ነፃነት ዋጋ የከፈሉትን የኦሮሞ ተወላጆቹን የእነ ባልቻ አባ ነፍሶን፣ የእነ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪን፣ የእነ ራስ አበበ አረጋይን፣ አውሮጳ ምድር ድረስ ዘልቆ በሮማ አደባባይ የኢትዮጵያውያንን አይበገሬነትና ለነፃነታቸው ቀናኢ ሕዝብ መሆናቸውን ያሳየውን የአብዲሳ አጋንና የበርካታ እልፍ የሚሆኑ የኦሮሞ ልጆችን ለሰው ልጆች ነፃነት የፈሰሰ ደምና መሥዋዕትነት ማራከስ ነው የሚሆነው፡፡
ከሰሞኑን የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩና አንጋፋው ፖለቲከኛ ፕ/ር መረራ ጉዲና፡- ‹‹የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምስቅልቅል ጉዞና የሕይወቴ ትዝታዎች፡- ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ እስከ ኢህአዴግ›› በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፋቸውም በዓድዋው ጦርነት ከየትኛውም ሕዝብ ይልቅ የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑ ጦር አዝማቾችና ጀግኖች ታላቅ መሥዋዕትነት መክፈላቸውን በመግለጽ የዓድዋ ድል የምኒልክን ቅኝ ግዛት ዘመቻ ያጠናከረ ዓውደ ግንባር ነው የሚለውን ሐሳብ አጣጥለው በመከራከር ጽፈዋል፡፡
በተጨማሪም ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ታላቅነትና አይበገሬነት በኦሎምፒክ መድረክ ከፍ ያደረጉ አበበ በቂላ፣ ዋሚ ቢራቱ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ብርሃኔ አደሬ፣ ጌጤ ዋሚ፣ ጥሩነሽ ዲባባ፣ ፋጡማ ሮባ፣ ደራርቱ ቱሉ ... እነዚህ ሁሉ በሮጡበት መድረክ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ብሔርና ሃይማኖት ሳይለዩ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ አብረው ሮጠዋል፣ ስለ ኢትዮጵያ ክብርና ድልም አብረው አምጠዋል፣ ተጨንቀዋል፡፡ በባርሴሎና ኦሎምፒክ መድረክ አበባችን ደራርቱ ቱሉ በአሥር ሺሕ ሜትር የመጀመሪያቱ አፍሪካዊት ሴት ወርቅ ሜዳሊስት በሆነችበት ድሏ የአገሯ ብሔራዊ መዝሙርና ሰንደቅ ዓላማ በስፔን ሰማይ ላይ ሲናኝና ከፍ ብሎ ሲታይ በጉንጯ ላይ ኮለል ብሎ የፈሰሰውን ዕንባዋን የታዘብን ሁሉ፣ በኢትዮጵያዊነት ኩራትና አይበገሬነት መንፈስ አብረናት በደስታ ሲቃ አንብተናል፣ መሬት ስመናል፡፡
ይህን ታሪክ በወርቅ ቀለም የጻፈውን የበርካታ ኦሮሞ ጀግኖችን ገድልና ለኢትዮጵያዊነት የተከፈለ መሥዋዕትነትን ማቃለልና ታሪክን ማዛባት ጤነኛ አካሄድ አይደለም፡፡ በዘመናችን ኦሮሙማን/የኦሮሞን ብሔርተኝነት በእጅጉ የሚሰብኩና የሚያራግቡ ሰዎች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ኦሮሙማን ወይም የኦሮሞ ብሔርተኝነነትን ለመገንባት ሲሉ የኢትዮጵያን የሺሕ ዘመናት ታሪክ፣ ሥልጣኔ፣ ቅርስና የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ ማጣጣልና መንኳሰስ ጤነኛ አካሄድ አይመስለኝም፡፡
ኢትዮጵያዊነት እንደ ኮሶ ተበጥብጦ በግድ እያነገፈገፈን የተጋትነው፣ እየቀፈፈንና እየኮሰኮሰን የተደረበብን ማንነት ብለው ለሚከራከሩ ሰዎች በእርግጥም በግድ ሳይወዱ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ተቀበሉ ብሎ ማስገደድ እንደማይቻል አሳምሬ አውቃለሁ፡፡ ኢትዮጵያዊ ለመሆን ያለመፈለግ መብታቸውንም በግሌ አከብራለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ታሪክን በማዛባት ጥቁር ሕዝቦች፣ መላው አፍሪካና በአጠቃላይ ነፃነትን አፍቃሪ የሆኑ ሕዝቦች ልብ ውስጥ ትልቅ ዋጋና ክብር ያለውን የኢትዮጵያዊነትን መንፈስ ማራከስ፣ በኢትዮጵያና በሕዝቦቿን ታሪክ፣ ቅርስና ማንነት ላይ መዘባበት ጤነኛ አካሄድ እንዳልሆነ አሁንም በድጋሚ አስረግጬ ለመናገር እወዳለሁ፡፡

# ትውስታ

## ከእስክንድር ነጋ

ጠ/ሚ/ሩ ቃለምልልስ እየሰጡ ነው... ቅዳሜ መጋቢት 3/2003 ...በዚያን ሰሞን ሞላ ብሎ የነበረው ሰውነታቸው አሁን ከሳ ብሏል... ውይ! ውይ! ውይ!... እኔን! ግን... ግን... ከትላንት ወዲያ ቱኒዚያ፣ ትላንት ግብፅ፣ ዛሬ ደግሞ ሊቢያ እየተፈራረቁባቸው ከሳ ማለትማ ይነሳቸው እንዴ?... «ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል» እንጂ፣ የሰሞኑ የመለስ የስጋት ኑሮ «ውስጡን ለቄስ» እንደተባለው ነው... የስቃይ ኑሮ... አሳዛኝ ኑሮ... እኔን!

የወትሮው «መፈክር አውራጁ» መለስ ዛሬ ቀዝቀዝ ብለዋል፡፡ ስለኢኮኖሚው ተጠይቀው ሲመልሱ ሃሳባቸው ሌላ ቦታ ይመስላል፡፡ ዋናዎቹን ጥያቄዎች እየጠበቁ ይመስላሉ... የቱን ጥያቄዎች?... ከእንጥፍጣፊዎቹ በኋላ የሚመጡትን... ህዝባዊ ተቃውሞ በኢትዮጵያ ይቀሰቀሳል ብለው አልሰጉም ወይ? (ያው መስጋታቸው ቢታወቅም...) ህዝባዊ ተቃውሞ ቢነሳ፣ ሠራዊቱ እንዲተኩስ ትዕዛዝ ይሰጣሉ ወይ?... የግብፅና የቱኒዚያ ሠራዊቶች በህዝባቸው ላይ አንተኩስም ማለታቸውን እንዴት ይመለከቱታል?... ህዝባዊ ተቃውሞ ቢነሳ፣ ሥልጣንዎን በፈቃድዎ ይለቃሉ ወይ?... አውራው የዴሞክራሲ እንቅፋት መለስ ዜናዊ ናቸው የሚባለውን እንዴት ይመለከቱታል?... ኧረ ስንቱ ! ኧረ ስንቱ !... እነዚህ ጋዜጠኞች አንጀታችንን ሊያርሱት ነው... ሶፋዬ ላይ ተመቻቸኹ... ዛሬ ጉድ ሊፈላ ነው!!
እንጥፍጣፊ ጥያቄዎቹ ግዜ እየፈጁ ነው... ሃ... ሃ... ሃ... ሃ... ሃ... አዘጋኹ... አሰልቺ ጥያቄዎች፣ አሰልቺ መልሶች... በእጄ የያዝኹትን መፅሃፍ ማገላበጥ ጀመርኹ... ደቂቃዎች አለፉ...

ሴቷ ጋዜጠኛ ጀመረችው... ደስ አይልም?... ወንዶቹ ደግሞ ይቀጥላሉ... አለሳልሳ ነው ጥያቄውን ያቀረበችው... እነዚህ ጋዜጠኞች ተነጋግረው መሆን አለበት... ቀስ ብለው ጀምረው፣ ሳይታሰብ ሊያፍረጠርጡት መሆን አለበት... «በሰሜን አፍሪካ ሕዝባዊ ተቃውሞ ያስነሱት ክስተቶች በኢትዮጵያ ውስጥም እንዳሉ ተቃዋሚዎች ይናገራሉ፡፡ በዚህ ላይ እርስዎ ምን አስተያየት አለዎት?»... አለቻቸው ጋዜጠኛዋ... በጨዋ ቋንቋ የቀረበ ቆንጆ ጥያቄ... በጨዋ ቋንቋ ለሚቀርቡ ከበድ ከበድ ለሚሉ ጥያቄዎች ጥሩ በር ከፋች....
መለስ ዜናዊ ምላሽ እየሰጧት ነው...
«እኔ ተመሳሳይ ተቃውሞ ይነሳል የሚል ግምት የለኝም...»
...እያሉ ነው መለስ፤ የሚጠበቅ ነው... «ለምን ይነሳል?...»
...እየተሟሟቁ ነው ጠ/ሚ/ራችን... «ህዝቡ የ5 ዓመታት ኮንትራት ከሰጠን ገና 10 ወራት እንኳን በደንብ አላስቆጠሩም...» ...እሺ አቶ መለስ፤ ቀስ ይበሉ...
«በድምፁ፣ በካርዱ ነው ይሄን ኮንትራት የሰጠን...» ... ሳላውቀው ሶፋው ጠርዝ ላይ ደርሻለኹ፤ ምንም ነገር እንዳታመልጠኝ እየተለጠጥኹ ነው... «ለመፈፀም ቃል የገባነውን ዳር ለማድረስ ጠዋት ማታ ደፋ ቀና እያልን ባለንበት ግዜ፣ አሥር ወር ሳይሞላ በመንገድ ላይ ነውጥ ሊያስቆመን የሚወጣው ለምንድን ነው?...» ...አልበቃዎትም አቶ መለስ?... «በዚያ ላይ ደግሞ...» ...ቀጠሉ ጠ/ሚ/ሩ...
«ኢትዮጵያ በህግና በሥርዓት፣ በሰላማዊ መንገድ መንግሥት ለመለወጥ የሚቻልበት ሀገር ናት...» ...አሁን ጆሮዬን እየኮረኮርኹ ነው... የማዳምጠው በትክክል ነው?... «ከ5 ዓመታት በኋላ ህዝቡ ምርጫ ካርዱን ተጠቅሞ ኢሕአዴግን በዝረራ ከሥልጣን ሊያባርረው እንደሚችል ህዝቡ ያውቀዋል...» ...አሁን ከተቀመጥኹበት ፍንጥር ብዬ ተነስቻለሁ!... ህዝቡ ያውቀዋል? ነው ያሉት?... አቤት!... አቤት!... አቤት!... አቤት አለማፈር!... «ኢሕአዴግም ያውቀዋል...» ...አሉ መለስ ...ባለቤቴ ሳቋን ለቀቀችው...
«ይሄን እያወቀ ለምንድን ነው ወደ መንገድ ላይ ነውጥ የሚሄደው?» ...እዚህ ጋር መለስ ተሽከርካሪ ወንበራቸውን ትንሽ ወደኋላ ገፋ አደረጉት... እና... እና... ሁለቱንም እጃቸውን አወናጨፉ!... ለካ በስሜት ከንፈዋል... አይ መለስ! ቃለ-ምልልሱ አበቃ... ጠ/ሚ/ሩ ተነስተው ወጡ...

ታዲያ፣ ለዚህ ምን ምላሽ ነው የሚሰጠው? የት ነው የሚጀመረው? ወደ ሰኔ 1983 እንመለስ? ሁለት አስርት ዓመታት ወደኋላ ተጉዘን፣ ሰፊ ህዝባዊ መሠረት በነበረው ኢዴኃቅ ላይ የሽግግር መንግሥቱ አካል አንዳይሆን በር በመዝጋት የተጀመረው ኢ-ዴሞክሲያዊነት፣ ዘንድሮ ወደ ተዘመገበው 99.6% «የምርጫ ድል» እንዴት እንዳደገ እንዘክር? «ዝክረ ኢ-ዲሞክራሲ ወኢሕአዴግ» ልንለው እንችላለን፡፡ አንድ ትልቅ መፅሃፍ ይወጣዋል፡፡
እዚህ ውስጥ መነከር ግን፣ ወይ የጠ/ሚ/ሩን አባባል እውነት ነው ብሎ የሚያስብ አንድ ሰው ሊኖር ይችላል ብሎ መጠራጠርን ይጠይቃል፣ ወይ ደግሞ፣ ሌላ የሚፃፍለት ቁምነገር ጠፍቶ፣ አንድ ሺህ ግዜ ስለተፃፈለት እውነታ ለአንድ ሺህ አንደኛ ግዜ መፃፍ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ፣ መለዕኮታዊ ትዕግሥትና የተትረፈረፈ ግዜ ያስፈልገዋል፡፡ በእኔ በኩል ሁለቱም የለኝም፡፡
ስለዚህ፣ በአዲሱ ሚሊኒየም በአስገራሚነቱ ቀዳሚ ስፍራ የያዘውን ምላሻቸውን በትዝብትነቱ ብቻ በማስቀመጥ አልፌዋለኹ፡፡
ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ትንሽ ሳልዳስሰው የማላልፈው ጉዳይ ግን አለ፡፡ ከመለስ አስገራሚ «ትንታኔ» ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሰፊ ባሕር ነው፤ በጥልቀት ልሄድበት አልከጅልም፡፡

ቅድመ 66 አብዮት፣ የቤተመንግሥት ስርዓት ነበር፡፡ ይህ ሰፊ አድማስ ያለው ወግ፣ በተራዘመ አዝጋሚ የለውጥ ሂደት (ፈረንጆቹ Evolutionary የሚሉት) ዳብሯል፡፡ ርዕሰ ብሔርነቱንና መንግሥትነቱን አቀናጅተው ለሺህ ዓመታት የዘለቁት የኢትዮጵያ ነገስታትና መኳንቶቻቸው ከአቋቋም፣ ከአቀማመጥ፣ ከአነጋገር፣ ከአለባበስና ከአበላል አንስቶ እስከ ኃይማኖት፣ ግልቢያ፣ ውጊያና ፍርድ አሰጣጥ ድረስ ተምረዋል፡፡ ታላላቆቹ ነገሥታት በአንዱ ወይም በሌላው የላቀ ብቃት አስመዝግበዋል፡፡ ብዙዎቹ በመንፈሳዊነታቸውና በተዋጊነታቸው ልቀው ወጥተዋል፡፡ የአንዳንዶቹ የገዘፈ ክህሎት በታሪክ ማሕደር ላይ ጎላ ብሎ ሰፍሯል – – – አፄ ዘርያዕቆብ በመንፈሳዊነታቸው፣ አፄ አምደፅዮን በወታደራዊ አመራር ሰጪነታቸው ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ነገሥታቱ ሀገር ከመጠበቅና ከመምራት ባሻገር፣ ለሚመሩት ሕዝብ አርአያ ሆኖ መመሰል ይጠበቅባቸዋል፡፡ አበላላቸው፣ አቀማመጣቸው፣ አነጋገራቸው ወዘተ... ጭንቅ ውስጥ የገባው በዚህ ታሳቢ ነበር፡፡
ይህ ግን ለመለስ ዜናዊ ቦታ እንደሌለው ትላንት አብስረውልናል፡፡ «በጠ/ሚ/ርነቴ ኮንትራት የገባሁት ለ8 ሰዓታት ስራ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪRole Model (አርአያ) ለመሆን የገባሁት ውል የለም፡፡ የታመመን በመጠየቅ፣ ትምህርት ቤት በመመረቅ አላምንም» ብለው እቅጩን ነግረውናል፡፡ (ቀጥተኛ ጥቅስ ነው፡፡)
በመለስ ቀመር፣ ከአነጋገራቸው ጋር «ኮንትራት» የለንም፡፡ የእኛ «ኮንትራት» ኢኮኖሚው በምን ያህል አደገ? የዋጋ ግሽበቱ በቁጥጥር ስር ውሏል ወይ? የውጭ ንግድና የመንግሥት ባጀት ጉድለቶች ምን ደረጃ ላይ ናቸው? በሚሉትና በመሳሰሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ብቻ የታጠረ ነው፡፡ ስለዚህም፣ መለስ ዜናዊ እንዳመጣላቸው እየተናገሩ ይኸው ሃያ ዓመታትን አብረን አዝግመናል፡፡ በዘፈቀደ የሚወረውሯቸውን ቃላትና አባባሎች እያደመጠ የተኮተኮተ፣ ያደገና ለአቅመአዳም የደረሰ አንድ ትውልድ በቅሏል ማለት ነው፡፡

ይህ ትውልድ ለእውነትና ለጨዋነት ምን ያህል ዋጋ ይሰጣል? የሚለው ጥያቄ ሁልጊዜ ያሳስበኛል፡፡ መለስ ዜናዊ ተገነዘቡትም አልተገነዘቡትም፣ መሪዎች በሁሉም ሀገራት ትልቁን የአርአያነት ሚና ይጫወታሉ፤ በጥንቷ ኢትዮጵያ ብቻ አይደለም፡፡ አሜሪካዊያን፣ ፕሬዝዳንቶቻቸው ስለትናንሽ የግል ሕይወታቸው ሳይቀር እውነት መናገራቸውና አለመናገራቸው ከልብ የሚያስጨንቃቸው ተቀናጥተው አይደለም፡፡ ለውሸቱ ዋጋ የማይከፍል መሪ፣ መዋሸትን እንደ ነውር የማይቆጥር ትውልድ ያፈራል ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ የእነሱ ስጋት በሀገሬ እውን ሆኖ እንዳላይ የምር እፈራለሁ፤ እድሜ ለመለስ፡፡

ከዚህ ባሻገር፣ ከጠ/ሚ/ሩ የቅዳሜ ጠዋት ቃለምልልስ የሚገኘው ቁም ነገር፤ ጋዳፊ ባለፈው ሰሞን ሰጥተውት ከነበረው ቃለምልልስ ጋር መመሳሰሉ ነው፡፡ ሕዝባቸው ሆ! ብሎ ለዴሞክራሲ ስለመነሳቱ የተጠየቁት ጋዳፊ፣ «የአልቃይዳ ሴራ ነው» ብለው ዓለምን ማስደመማቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡
የእኛው አቶ መለስ ደግሞ፣ «ሕዝባዊ ተቃውሞ የሚነሳ ከሆነ፣ ከበስተጀርባቸው ሻዕቢያ አለበት» ብለው ከወዲሁ ነግረውናል፡፡ እንደ ጋዳፊ እስከሚፈነዳ አልጠበቁም፤ ፈጣኑ መሪያችን!! «አዲስ አበባን በፈንጂ አናውጦ እንደ ባግዳድ ማድረግ የተሳነው ሻዕቢያ፣ በመንገድ ላይ ነውጥ ባግዳድ ሊያደርጋት ምሏል» ብለው አርድተውናል፡፡

በሌላ አነጋገር፣ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲው ጥያቄ ምንጭ ሕዝቡ ሳይሆን ሻዕቢያ ነው ማለታቸው ነው፡፡ ሕዝቡማ «በምርጫ ካርዱ ኢሕአዴግን ከስልጣን ሊያባርረው እንደሚችል ያውቃል» ብለውናል እኮ ጠ/ሚ/ሩ፤ ቀደም ብለው፡፡ እንደ ቱኒዚያ፣ ግብፅ እና ሊቢያ ጎዳና ላይ የሚወጣ ካለ፣ ወይ የሻዕቢያ ሴራ አስፈፃሚ ወይ ሰለባ ከመሆን አያልፍም፤ ለሃያ ዓመታት «ደግመን ደጋግመን በምርጫ ካርዳችን ኮንትራት እንደሰጠናቸው ጠ/ሚ/ራችን» ገለፃ ከሆነ፡፡

ጋዳፊ የቀበጣጠሩት የሞትና የሽረት ትንቅንቅ ላይ ሆነው ነበር፡፡ ድንግርግራቸው በቂ ምክንያት ነበረው፡፡ ለመከላከል እንኳን ፋታ ባጡበት ቅፅበት ነው ከአልቃይዳ ጀርባ ለመደበቅ የተተራመሱት፡፡ በአባባላቸው ዓለም አልተገረመም፤ ሳቀባቸው እንጂ፡፡
መለስ በአካል ምንም አይድረስባቸው እንጂ፣ በመንፈስ ከጋዳፊ የተሻለ ቦታ ላይ አይደሉም፡፡ ተጨንቀዋል፣ ተጠበዋል፡፡ የአእምሮ እረፍት የሚባል ነገር ከራቃቸው ውለው አድረዋል፡፡ «ዛሬ ነገ የጎዳና ላይ ተቃውሞ ቢነሳ ብለን እንቅልፍ ሳይወስደን አናድርም» ብለው ከትንሽ ደቂቃዎች በፊት የፎከሩት መለስ ዜናዊ፣ የሻዕቢያን ስም ያለቦታው ሲያነሱ የተጨነቀው ገፅታቸው ፍንትው ብሎ ለመታየት በቅቷል፡፡
ሻዕቢያን ሙጥኝ ያስባላቸው ጭንቅ ነው፡፡ አይገርምም፤ ያስቃል እንጂ፡፡

ለመለስም ሆነ ለጋዳፊ፣ ከጭንቅ መገላገያው ዘይቤ በጣም ቀላል ነው፡፡ ድፍረትን፣ ቅንነትንና ጀግንነትን ግን ይጠይቃል፡፡
ስልጣንን በፈቃደኝነት መልቀቅ!!!
አሁኑኑ!!!

# ከቀሲስ ታደሰ አጠና ሃይሉ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ (ክፍል ፩)

ውድ አንባቢያን ቀሲስ ታደሰ አጠና በኢተትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የመንግስት ጣልቃ ገብነትን በመቃወም ድምፃቸውን ከሚያሰሙት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ከሚታወቁት አንዱ ናቸው። የፖለቲካና የሃይማኖት መቀያየጥ አጥብቀው ይቃወማሉ። ባሁኑ ጊዜ ቀሲስ ታደሰ ምክንያቱ ባለታወቀ በቶሮንቶ ካናዳ የፖለቲካ ጥገኝነት ጥያቄ በማቅረበ ላይ ናቸው። የሰሜን አሜሪካ ዘጋቢያችን በስልክ ቃለ መጠይቅ አድርጎላቸዋል።

**ልሳነ ህዝብ**:- ጤና ይስጥልኝ ቀሲስ ታደሰ

**ቀሲስ ታደሰ**:- ጤና ይስጥልኝ፡ ሰላም ላንተ ይሁን ልጄ

**ልሳነ ህዝብ**:- ከለሳነ ህዝብ መፅሄት ነው የመጣሁት።

**ቀሲስ ታደሰ**:- አስታውሳለሁ። በቀጠሮአችን መሰረትም ይኸው መጥቻለሁ።

**ልሳነ ህዝብ**:- ወደ ጥያቄዬ በቀጥታ ልግባና፡ የተከበሩት ቀሲስ ታደሰ በመጀመሪያ እራስዎትን እንደ ፖለቲከኛ አሊያም የኢትዮጵያን መንግስት እንደሚቃወም ሰው አድርው ያዩታል ወይ?

**ቀሲስ ታደሰ**:- በጭራሽ፡ ፖለቲካ ውስጥ ገበቼም አላውቅም ለወደፊት የመግባት ዓላማም የለኝም፡፡ እኔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ካህን ነኝ። ሃይማኖታችን ደግሞ እንደኔ ያሉ ሰዎች ፖለቲካ ውስጥ እንዲገቡ አትፈቅድም።

**ልሳነ ህዝብ**:- የኢትዮጵያ መንግስትን ከቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ውጣ በማለት አጥብቀው ይታገሉ እንደነበር ሰምቻለሁ፡፡

**ቀሲስ ታደሰ**:- ይህ ኢንፎርሜሽን በራሱ ትንሽ የተዛባ ይመስለኛል። እኔ መንግስትም ሆነ ሰራተኞቹን ተቃወሜ አላውቅም። የተቃወመኩተ ጣልቃ ገብነታቸውን ነው። መንግስትን መቃወምና የመንግስት ሰራተኞች የሚፈፅምን ድርጊት መቃወም ተለያይተው መታየት ያለባቸው ይመስለኛል። እንደውም እኮ እኔ በቤተክርስቲያናችን ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ይቁም በማለት በቀጥታ ለራሴ አለቆች ነገርኩ እንጂ በቀጥታ ከመንግስት ሰዎች ጋር ተጋጭቼ አላውቅም።

**ልሳነ ህዝብ:-** አሃ፡ አሁን አባባልዎ የገባኝ ይመስለኛል። የመነገስት ተግባራት የሚሉት ምኑን ነው?

**ቀሲስ ታደሰ:-** በመጀመሪያ በማይመለከተኝ ርእስ ላይ የመንግስትን ስራ መተቸት የኔ ሃላፊነት አይደለም።

ወደ ሃይማኖት ጉዳይ ስንመጣ ግን መንግስት ከቤተክርስቲያኒቱ ተግባር እጁን ማንሳት አለበት በማለት አጥበቄ እቃወማለሁ። መንግስት ሊሰራቸው የሚገባ በርካታ ስራዎች አሉት፤ በቤተክርስቲያኑ የቀን ተቀን ተግባር ግን ጣልቃ መግባት የለበትም።

**ልሳነ ህዝብ:-** መንግስት በቤተክርስቲያኒቱ የለት ተዕለት ተግባር ጣልቃ ይገባል ብለው ያምናሉ።

**ቀሲስ ታደሰ:-** መቼም እንግዲህ ጣልቃ መግባት የሚለው የኢትዮጵያ መንግስት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ እያደረገ ያለውን ነገር ለመግለፅ በጣም የለዘበ ቃል ይመስለኛል። ቤተክርሰቲያኒቱ በገዢው ፓርቲ ደጋፊዎችና አባላት ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር ውላለች። ውድ የሆነው የፈጣሪ ቃል የሚሰራጨባት ሳይሆን የፖለቲካ መድረክ ሆናለች። ፓትሪያርኩን ጨምሮ አቡኖችን የሚሾመው መንግስት ነው። የያነዳንዱ ገዳም አስተዳዳሪዎችን ሳይቀር መንግስት እየሾመ የታሪካዊቷ ቤተክርስቲያናችን መጪ ዘመን በማጨለም ላይ ነው።

**ልሳነ ህዝብ:-** እንዲህ ያለው ተግባር መቼ ነው የተጀመረው? እንዴት መንግስት ሰርዖ ወደ ቤተክርስቲያኒቱ ሊገባና በኋላ ግን ቤተክርስቲያኒቱን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር ሊያውላት ቻለ?

## “አቅረብኩ ለከ ማየ ወእሳተ፡ ደዩ እዴከ ሃበ ዘፈቀድከ”

**ቀሲስ ታደሰ:-** ስለእውነት ለመናገር ቤተክርስቲያናችን በነገስታቶች ዘመን ሳይቀር በማንኛውም ጊዜ ከመንግስት ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆና አታወቅም። ያሁኑ ጊዜ ከሌላው ለየት የሚያደርገው ግን ባለፉት ስርዓተፀ ከነበረው የጣልቃ ገብነት መጠን በጣም የተለየ ነው፡፡ ባለፈው ጊዜ የነበረው ኮሚኒስት መንግስትም አንዳንድ ነገሮችን ሲያደርግ ነበር፤ ባሁኑ ጊዜ ግን ተግባራቱ ሁሉ የሚከናወኑት በመንግስት ነው። በመጀመሪያ የፈፀሙት የከፋ ድርጊት የቅዱስ ሲኖዶሱን ቀኖና በሚያፈርስ መልኩ አንደኛው ፓተትሪያርክ ስራ ላይ እና በህይወት እያለ ሌላ ፓትሪያርክ አምጥተው መሾማቸው ነው። እነዚህ ሰዎች ከሽምቅ ተዋጊነት የነበረውን መንግስት አሸንፈው ስልጣን ላይ ሲወጡ፡ በሽምቅ ተዋጊነታቸው ዘመን አሜሪካን አገር ሆኖ ይደግፉቸው የነበረን አቡን አምጥተው ፓትሪያርክ አድርገው ሾሙት፡፡ አቡኑ የትግራይ ሰው ሲሆን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተከርስቲያን ውስጥ ይህ ነው የሚባል አስተዋፅኦ የነበረው አቡን አይደለም። መላው የበረተክርስቲያኒቱ መዋቅር በተመሳሳይ ሰዎች ለሙላት የመጀመሪው ይኸው ነበር።
ልሳነ ህዝብ:- እንደርስዎ ያሉት መንፈሳዊ አባቶች ታዲያ እንዲህ ያሉት የጣልቃ ገብነት ተግባራትን ሲያዩ ምን አሉ?

**ቀሲስ ታደሰ:-** ሁላችሁም እንደምታውቁት እንዲህ ያለውን ተግባር በርካታ አባቶች ለመቃወም ሞክረዋል። ገሚሱ ከሰራቸው ተባረዋል፣ ገሚሱ አገሪቱን ለቀው ሄደዋል ወዴት እንደሄዱ ያልታወቁም አሉ፡፡ በእውነት ማወቁ በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው።

**ልሳነ ህዝብ:-** ችግሩ በቀላሉ ይፈታል ብለው ያምናሉ? እርስዎ ብቻዎትን እውነት በመናገርስ ለውጥ ላመጣ እችላለሁ ብለው ያምናሉ?

**ቀሲስ ታደሰ:-** መቼም እኔ እያደረግኩ ያለሁት የእውነት ቃላትን መዝራት ነው፡፡ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ያስተማረን ሰዎች ተከተሉህ አልተከተሉህም እውነትን ይዞ በመቆም በፅናት መፀለይን ነው። እኔም እያደረገኩት ያለው ነገር ጀብደኝነት አይደለም። ብዙ ነገር ሊያስከፍለኝ የሚችል አደገኛ አቋም መሆኑንም አውቃለሁ። ይሁን እንጂ እውነትን እያወቅክ ምንም እንዳልተፈፀመ ዝም ማለት ደጎ በጣም ከባድ ነገር ነው። ሁልጊዜ ሰፊው ህዝብ ትክክል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከታሪክ እንደምንረዳው አንዳንዴ ህዝብ ባለማወቅ ጨለማ ውስጥ ሊቆይ ይችላል። ይሁን እንጂ ህዝብ ብዥታውን ማጥራት ሲጀምር ችግሮችን ለመፍታት ቀላል ይሆናል። ከጠቅላላ የአማኞቹ ቁጥር አንፃር ሲታይ በዚሁ ግብረ ገብ የጎደለው ተግባር ላይ ተሰምተው የሚገኙት ጥቂት ናቸው፡፡ እኔ ያደረገኩት ዕውነታውን ማሰራጨት ነው፡ ከዚያ በኋላ ፍርዱን የቆየውን ማንነቱን ለመጪው ትውልድ ጠብቆ ማቆየትና ማስተላለፍ ለሚፍልገው ህዝበ ክርስቲያን እተወዋለሁ። የፈጀውን ጊዜ ቢፈጅም ለለውጥ የተጋ ፍላጎት እስካለ ድረስ ቢዘገይም እንኳ ለውጥ መምጣቱ የማይቀር ነው። የንደኔው አይነት ትንሽ አስተዋፅኦ ዳቦውን ለማስጋገር ባይችልም እንኳ ለመብላላቱ ሂደት እንደ እርሾ ሆኖ ማገልገሉ የማይቀር ነው። እኔ እያደረግኩ ያለው ትንሽ ጠብታ ቀለም ኩሬ ላይ የማንጠባጠብ ያህል ነው። እነዚህ ጠብታዎች እየበዙ ሲመጡ ግን ቀለሙ መለወጡ የማይቀር ነው።

**ልሳነ ህዝብ:-** ቀሲስ ታደሰ፡ እርስዎ ስለራስዎ ለናገር ብዙም የማይፈልጉ እራስዎን ዝቅ ማድረግ የማይወዱ መሆነዎትን ሰምቻለሁ። ምናልባት ይህ ባህሪይዎ ከኔ ጋር ያለት ቃለ ምልልስ ፈታ እንዳይል እያደረገ ይሆን እንዴ?

**ቀሲስ ታደሰ:-** አላደረገም። እኔ እንደ ሁሉም ሰው ነኝ። በምድር ላይ እንለው ብዙ ሰው ግብዝና ሃጢአተኛ ነኝ፡፡ የሚለየኝ ነገር ካለ በሁለት የተለያዩ መስኮች ላይ ሊያጫውቱ የሚችሉ ሁለት የተለያዩ ሃሳቦች የሉኝም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ይህ ባህሪዬን እንደ ግትርነት ያዩታል። እኔ እንግዲህ አንድ ህሊና ነው ያለኝ የምለው ነገር በእውነት የማምንበትን ነው። የመንፈስ ልጆቼንም በዚሁ መንገድ ነው የማስተምራቸው። ነገሮችን በቀጥታ የምናገር መሆኔን በርግጠኝነት ይነግሯችኋል። አንደዚያ መሆን መጀመሪያ አከባቢ በጣም አስቸጋሪ ነበር እየለመድከው ስትመጣ ግን ከፍተኛኛ የሆነ የህሊና ሰላም ያለበት አካሄድ ነው። አንተ ጋ ሳወራም በእውነት የተሰማኝን ነው፡ ያሰብኩትን እንዳልናገር ያገደኝ ምንም ምክንያትም የለም።

**ልሳነ ህዝብ:-** በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በጣም ሸርሻሪ የሚሉት ችግር ሊነግሩኝ ይችላሉ?

**ቀሲስ ታደሰ:-** በመጀመሪያ ቤተክርስቲያኒቱ ጥንታዊ ከሚባሉት አንዷ ነች። አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚከተላት እንደሆነም አምናለሁ። ቤተክርስቲያናችን ሌሎችን በመቀበልና በመቻቻል ትታወቃለች። በርካታ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተውጣጡ አዋልድ መጻህፍት ያላትና በመላው ዓለም ከሚገኙ ሌሎች ተመሳሳይ ቤተክርስቲያናት እንኳ ልዩ መሆንዋ ይታወቃል። እንደ ማጋነን ካልተቆጠረብኝ ታሪካዊ ቅርሶቻችንም ጭምር የታቀቡት በዚችው ቤተክርስቲያናችን ነው። ይህም እንደ ክርስቲያንነታችን ብቻ ሳይሆን እንደ ኢትዮጵያዊነታችንም ጭምር ነው። በሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ጭምር እጅግ በጣም የተከበረች ቤተክርስቲያን ነች። ከጎረቤቶቻችንና የሌላ ዕምነት ተከታይ ከሆኑ ወንድሞቻችን ጋር በስምረት ኖረናል። አየህ እንግዲህ እንደዚህ ያሉ ወድ ባህሪያት በፖለቲካ እየተለበጡ ሊጠፉ የሚችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። አንዳንድ ቀሳውስት ከእግዜብሄር ቃል ይልቅ ፖለቲካዊ ዓላማ ያለው ሃሳብ ያራምዳሉ፡፡ በቤተክርስቲያኒቱ ሙስና ሰፍኗል። አንዳንዴ ታሪካዊ ቅርሶች ጠፉ ይባልና በጠፉበት ይቀራሉ። የቤተክርስቲያኒቱ ጥሪት ግለሰቦች ስጋቸውን አንደላቀው ለማኖር ሳይሆን ህዝብን ወደ ትክክለኛ አቅጣጫ የሚመራበት ትምህርት ላይ መዋል ነበረበት። ቤተክርስቲያኒቱ እንዲህ ካለ የተበላሸ አሰራር ውስጥ ከተዘፈቀች፡ መንግስትም ለፖለቲካዊ ጥቅሙ ሲል ብቻ እነዚህ ብልሹ አሰራሮችን በመደበቅ የሚተባበር ከሆነ ማን ነው መጪውን ትውልድ ወደትክክለኛ መንገድ የሚመራው? ሳስበው ብስጩ የሚያደርገኝ ነገር ቢኖር ይኸው ነው። ልጆች እንደ ነጭ ወረቀት ንጹህ ሆነው ነው የሚወለዱት። መልካሙ እረኛ ካጋጠማቸው ወደ መልካም እንደሚጓዙ የታወቀ ነው ተቃራኒው ካጋጠማቸው ደግሞ ጉዳቱ ምን እንደሆነ ታውቀዋለህ።

**ልሳነ ህዝብ:-** ቀሲስ ታደሰ፡ ካነጋገርዎ እንደተረዳሁት ካለው ትውልድ ይልቅ ለመጪው ትውልድ የሚጨነቁ ይመስለኛል።

**ቀሲስ ታደሰ:-** እኔም ይመስለኛል። አየህ ይህ ትውልድ ትክክለኛው ትምህርት ለማግኘት ዕድሉ አለው፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ጊዜ በአፈ ታሪክ መልክ መተላለፍ የሚችለውን ግብረ ገባዊ ዕውቀትና ዕምነትን ማስተላለፍ የሚችሉ ሰዎች በህይወት ይገኛሉ። ተፈጥሮአዊ ስለሆነም እነዚህ በጣም የተማሩና ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ከዚህ ምድር ላይ ያልፋሉ። እነዚህ መልካም ሰዎች ካለፉ በኋላም መጪው ትውልድ ተስፋውን የሚጥለው በቤተክርስቲያኒቱ ላይ ነው። ይሁን እንጂ ታዲያ ቤተክርስቲያኒቱን ሳናጸዳት ካለፍን የመጪው ትውልድ ዕጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን ንገረኝ?

**ልሳነ ህዝብ:-** ስላላዋቂነቴ ይቅርታ ያድርጉልኝና ይህ የእግዜብሄር ቤት ስለሆነ እግዜብሄር ቤቱ እንደዚህ ሲሆን ዝም ብሎ ያያል?

**ቀሲስ ታደሰ:-** ይህ ደስ የሚል ርዕስ ነው። ከመጽሃፈ አበው የተወሰደ አንድ ጥቅስ ልንገርህ “አቅረብኩ ለከ ማይ ወእሳተ፡ ደዩ እዴከ ሃበ ዘፈቀድከ” ይላል። ትርጉሙም እሳትና ውሃ አቅርቤልሃለሁ እጅህን ወዳሻህ መክተት ደግሞ ያንተ ምርጫ ነው፡ ማለት ነው። ለቃላት አጠቃቀሜ ይቅርታ እየጠየቅኩ እግዜብሄር የመጨረሻ ትልቅ ዲሞክራት ነው። እግዜብሄር እያንዳንዷን እርምጃችንን አይቆጥርም። ይሄ የሚመዘገበው በያንዳንዳችን ነፍስ ላይ ሲሆን ለፍርድ የሚቀርበውም በፍርድ ቀን ላይ ነው። የእግዜብሄር ቤት ፈተና ላይ ሲወድቅ ይህ የመጀመሪያው ጊዜ አይደለም። የማምነው ነገር ቢኖር ስንውድቅ በጭራሽ ዝም ብሎ እንደማያየን ነው። ከያንዳንዱ መአዘን ሰዎችን ያስነሳል ይህንን መነስሳሳት በጥበብ ይ ጠቀምበትና ችግሩን ይፈውሳል። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ በእግዜብሄር ፈቃድ ለውጥ ይመጣል። አሁን ራሱ የድህነት (የመዳን) ሂደቱ የመጀምሪያ እርከን ላይ ነን። ሰው ስለሆንኩ የሆነ ኣርከን ላይ ስደርስ ተስፋ የመቁረጥ ባህሪያት ቢታዩም ኣንኳ የእግዜብሄር ፈቃድ በምንም ተአምር አይቋረጥም። ሰዎች ይጸልያሉ፡ የጸሎታቸው መልስ ግን ዘግይቶ ሊመጣ ይችላል፡ ካለፉ በኋላም ቢሆን።

**ልሳነ ህዝብ:-** በካናዳ ስለሚቆዩበት ሁኔታ በዝርዝር መወያየት ኣንደማይፈልጉ ነግረውኛል። እርስዎ በቤተክርስቲያኒቱ ታላላቅ ለሚባሉ ሰዎች ይጽፉና ይናገሩ ነበር፡፡ ስለምን ነበር ለነዚህ ሰዎች የመነግሩትና የሚጽፉላቸው?
ቀሲስ ታደሰ:- እኔ የነገርኳቸው ነገሮች ካንቀላፉበት ኣንዲነቁና ነገሮች ወደነበሩበት ኣንዲመልሱ ነው። ተጠያቂነትን በማስፈን የተስፋፋውን ሙስና እንዲያቆሙ ነግሬያቸዋለሁ። የቤተክርስቲያኒቱ ሃብትን ብቻ ሳይሆን በዚህ ሙስና ውስጥ እየሰመጡ ያሉት ወንድሞቻችን ነፈሰንም እንዲያድኑ ጠይቄይአቸዋለሁ። እንደ እምነቴ ስህተቶች የስጋ ልጆች ስለሆኑ መታረም ለሚፈልጉት እውነቱን በመንገርና ላጠፉትም ይቅርታና ምህረት በማድረግ ሊወገዱ ይችላሉ።

**ልሳነ ህዝብ:-** በዚህ ዓይነቱ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎችን እውነታን በግልቡ መንገር በራሱ አስቸጋሪ አይሆንም?

**ቀሲስ ታደሰ:-** አንዳንዴ ሌሎችን ለመጉዳት ብለህ እስካልተናገርክ ድረስ እግዜብሄር በጥንካሬ ይሞላሃል። ማንንም አልተቃወምኩም። የሰዎችን ስም በምንም ስህትት አንስቼ አላውቅም። በቁጣም ሆነ በተጋነነ ድምጽ ሃሳቤን ሰንዝሬ አላውቅም። ከዚህም በተጨማሪ የእየሱስ ክርስክቶስ አስተምህሮን በመጥቀስ ስለምናገር ማንም ምንም ሊል አልቻለም።

**ልሳነ ህዝብ:-** ክቡራን የልሳነ ህዝብ አንባቢያን ከቀሲስ ታደሰ አጠና ጋር ያካሄድነው ቃለ ምልልስ ክፍል ሁለት በሚቀጥለው እትም ላይ ይዘን እስከምንቀርብ ድረስ በቸር እንሰንብት



# አይ ስብሐት ነጋ!

|ፕ/ር መስፍን ወልደ ማርያም

በኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን ሳይኖረው ባለሙሉ ሥልጣን፤ እውቀት ሳይኖረው ባለሙሉ እውቀት የሆነ ሰው ስብሐት ነጋ ብቻ ነው፤ እንዲያውም ከዚያም አልፎ ራሱን የቻለ ሉዓላዊ ነጻነት ያለው ግለሰብ ነው ለማለት የሚቻል ይመስለኛል፤ በዚህ ግለሰብ ላይ የማደንቃቸው ሁለት ነገሮች ናቸው፤ በሉዓላዊነቱ የተጎናጸፈውን ሥልጣን ሙሉ በሙሉ ይጠቀምበታል፤ ይቆጣኛል ወይም ይቀጣኛል ብሎ የሚፈራው የለም፤ ስብሐት ነጋ የሚፈራው ምንም ነገር የለም፤ ሁለተኛ በሉዓላዊነቱ ያለውን ሙሉ ነጻነት በሙሉ ልብ ይጠቀምበታል፤ ናስ በላይ ከበደ እንዳለው <<የቅብጠት መዘላበድ>> ሊሆን ይችላል፤ ስብሐት ነጋ የተናገረው ነገር ትክክል ይሁን አይሁን ጉዳዩ አይደለም፤ ዋናው ነገር መናገሩ ነው።

በቅርቡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከጋዜጠኛነት ተማሪዎች ጋር ባደረገው ውይይት ላይ ሁለት ሰዎች ጽፈው አይቻለሁ፤ ዶር. በድሉ ዋቅጅራ በ**ፋክት** ላይ፣ ናስ በላይ አበበ በ**ኢትዮ–ምኅዳር** ላይ፤ ሁለቱም ሰዎች አልወደዱለትም ማለት ያንሳል፤ የሚወዱለትና የሚያጨበጭቡለት መኖራቸውም ሳይታለም የተፈታ ነው፤ ነገር ግን ስብሐት ነጋም ሆነ ደጋፊዎቹ አደባባይ ወጥተው ለመከራከር አይችሉም፤ ናስ በላይ አበበ እንደሚነግረን <<አቶ ስብሐት ነጋ የውጭ ሰው እንዳይገባ ከተማሪዎቹ ጋር ተደራድረው ነበር የመጡት፤ ስለሆነም ነበር ከፍተኛ ጥበቃ አልፈን የገባነው፤>> ብቻውን ተናግሮ በጭብጨባ የሚሸኝበት መድረክ በመፈለጉ በከባድ ጥያቄም ቢሆን የሚያጣድፉት ሰዎች እንዳይኖሩ ማረጋገጡ በተማሪዎቹም ቢሆን ውሎ አድሮ ትዝብት ላይ ይጥለዋል። ዶር. በድሉ ዋቅጂራ ስለስብሐት ነጋ ከኢትዮጵያዊነት መውደቅ በሚል በጻፈው ላይ ዶር. ዳኛቸውን



እንደሚከተለው ይጠቅሳል፤ <<ከኢትዮጵያዊነት መውደቅ ማለት፤ በቃ በአጭሩ (ኢትዮጵያዊ ሆኖ) ኢትዮጵያዊ አለመሆን ነው፤>> በቅንፍ ውስጥ ያለው የኔ ነው፤ ልክ ነው፤ አንድ ግለሰብ በማናቸውም ምክንያት ከኢትዮጵያዊነት ቢወድቅ ኢትዮጵያዊነቱ የከሸፈ ነው ለማለት ይቻላል፤ ነገር ግን ከኢትዮጵያዊነት መውደቅንና ኢትዮጵያዊነትን መጣልን ለይተን ማየት ያስፈልጋል፤ አንድ ሰው በማናቸውም ምክንያት ከፍተኛውን የኢትዮጳያዊነት ባሕርይና ግዴታ መሸከም አቅቶት ቢወድቅ ለዚያ ሰው ኢትዮጵያዊነቱ ከሸፈ፤ ለስብሐት ነጋና ለጓደኞቹ ከከሸፈባቸው የቆየ ይመስለኛል፤ ከራሱ አልፎ የሌሎችን ኢትዮጵያዊነት ለማክሸፍ የሚሞክር ደሞ ከመክሸፍ አልፎአል፤ ከኢትዮጵያዊነት መውደቅ ማለት የከሸፈ ኢትዮጵያዊነት ነው ማለት ነው።

ስብሐት ነጋ ዋና ዓላማው በሙሉ ነጻነት የመጣለትን እንደመጣለት መናገር ነው፤ ምሳሌዎችን እንጥቀስ፤– ሀ) <<ከኢትዮጵያ ሕዝብ በላይ የኤርትራ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት አለው፤>> ስብሐት ነጋ ስለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ስለኤርትራ ሕዝብ፣ ስለኢትዮጵያዊነት ያለው እውቀት የሚባል ነገር እንዲህ ያለው መዘባረቅ ነው፤ ስብሐት ነጋ ጨረቃ ከጸሐይ የበለጠ ትሞቃለች ቢልም አይደንቀኝም፤ አልከራከረውም፤ ስብሐት ነጋም ብቻውን መናገር እንጂ መከራከር አይፈልግም፤ ለ) <<የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኤርትራ ሕዝብ የበለጠ የኤርትራን መሬት ይፈልጋል፤>> እንደምሳሌ ያነሣው አሰብን ነው፤ ባድመን አላነሣም! እሱና ጓደኞቹ የኢትዮጵያን ወጣቶች በከሸፈ ጦርነት ውስጥ የማገዱት ባድመ ለሚባል መንደር ነው እንጂ አሰብ ለሚባል ወደብ አልነበረም፤

በዚያን ጊዜ ጦርነቱን በመቃወም ድምጼን ያሰማሁት ኢትዮጵያዊ ወይም ኤርትራዊ ሆኜ አልነበረም፤ ሰው ሆኜ ነው፤ ዛሬ ስብሐት ነጋ ሲዘላብድ ኢትዮጵያዊነት የማይታይበትን ያህል ኤርትራዊነትም አይታይበትም፤ በዚህም ጉዳይ ላይ መከራከር አይፈልግም፤ ሐ) <<ለማንኛውም ሰማያዊ ፓርቲ ሰልፍ መከልከላቸው የማውቀው ብዙ ነገር የለኝም፤ ይከልከሉም አልልም፤ አይከልከሉም አልልም፤ መብታቸው ነው፤>> ይህ መዘላበድ ካልሆነ ምንድን ነው? ምን ቁም-ነገር ይዞ ነው ይህንን የተናገረው? የገለባ ክምር ውስጥ አንድ ፍሬ መፈለግ ይቀላል።

አንድ ሌላ የስብሐት ነጋ ዘዴ (ዘዴ ካልነው!) ጉዳዩን በሚገባ ሳያጣራ እንደመጣለት ይናገርና <<አላውቅም>> ይላል! የማያውቀውን መዘባረቅ ግን ይችላል፤ ሰማያዊ ፓርቲ <<የምን ፓርቲ እንደሆነ አይታወቅም፤ የእስላም ፓርቲ ነው?>> ስብሐት ነጋ እውቀትን የሚሻ ቢሆን ለፓርቲዎች እውቅናን የሚሰጠውን መሥሪያ ቤት ያውቀዋል፤ ለምን ብሎ ይጠይቅ? ለምን ብሎ እውነቱን በማወቅ ይታሰር? ትክክለኛ መረጃ ባለማወቅ እንደልብ የመናገርን ነጻነት ይገድባልና <<አላውቅም>> ማለት ለመዘላበድ ይጠቅማል፤ ምንም እንኳን የሰላዮች ሠራዊት እንዳለው ብናውቅም ስለእስላሞችና ስለሰማያዊ ፓርቲ የተናገረውን እንደፖሊቲካ ከወሰደው ደረጃውን ከማሳየት አያልፍም፤ ሰማያዊ ፓርቲን በሁሉም ዘንድ ለማስጠላት የሚከተለውን ይላል፤ <<እስላሞች ወንድሞቻችን የሚሉት ደግሞ የት ያውቁናል? ሲቀጠቅጡን የነበሩ፤ ተራ ሕዝቡም አይወዳቸውም፤>> የጤፍ ቅንጣት የምታህል የማሰብ ተግባር ቢኖርበት ስብሐት የተናገረው ያልተጠረነፉትን እስላሞች በሙሉ የሰማያዊ ፓርቲ ደጋፊ የሚያደርግ መሆኑን መረዳት ይችል ነበር።

ስብሐት ነጋ አንድ መቶ ሃያ ዓመታት ያህል ወደኋላ ቢሄድ ኤርትራ የሚባል አገር አያገኝም፤ በዚያ መሬት ያሉ ሰዎች ላላቸው ወይም ለሌላቸው የኢትዮጵያዊነት ስሜት የስብሐት ነጋን ምስክርነት እንደማይፈልጉ በጣም እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል፤ ለሌሎቻችን ኢትዮጵያዊነትም ቢሆን የስብሐት ነጋ ምስክርነት አያሻንም፤ አሰብን አንሥቶ ብዙ ወጣቶች ያለቁበትን ባድመን ሳያነሣ መቅረቱ በአንድ በኩል፣ አሰብንም ሆነ ባድመን ከሚፈልጉ ወገኖች መሀል እሱ መውጣቱን በጣም ግልጽ አደረገ፤ ወዴት እንደገባ ግን ገና አልነገረንም!!!

# የኢህኣዴግ ውጥረትና የኣቦይ ስብሓት ጭንቅ

ሰሞኑን ኢህኣዴግ በኣዲስ ኣበባ ስብሰባ ማካሄድ ጀምሮ ነበር።

ስብሰባው ከተጠበቀው በላይ ውጥረት የተሞላበትና የድርጅቶች ሞቧደን የታየበት ነበር። ቡዱኖቹ ህወሓትና ደህዴን በኣንድ በኩል፤ ብኣዴንና ኦህዴድ በሌላ መስመር ተሰልፈው ሲወቃቀሱ ነበር።

ሊቀ መንበሩ ሃይለማርያም ደሳለኝ የቡዱናዊ መንገድ ከተመለከቱ በኋላ የኢህኣዴግ ስብሰባ ኣቁመው የድርጅቶቹ በግላቸው ገምግመው እንዲመለሱ በማለት መላው ቀይረው ጉብኝት ለማድረግ ብለው ወደ ምዕራብ ኣፍሪካ ሄደዋል።

በኢህኣዴግ ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ለመሳተፍ የሞከሩት ኣቦይ ስብሓት ነጋና ኣቶ ኣባይ ፀሃየ "ስብሰባው ለኢህኣዴግ ማእከላዊ ኮሚቴ ኣባላት ብቻ የሚመለከት ስለሆነ ኣዳራሹ ለቃቹ ውጡልን" ተብለው በብኣዴን፣ ኦህዴድ ድርጅቶችና በነ ኣባይ ወልዱ የሚመራው ኣንጃ ተቃውሞ ስለ ደረሰባቸው በብስጭት ሳይወዱ በግድ ከስብሰባው ወጥተዋል።

ኣቦይ ስብሓት ነጋ በራሳቸው የደረሳቸው ጠንካራ ተቃውሞና ህወሓት በኢህኣዴግ የነበረው ተሰሚነት ማሽቆልቆሉ ኣስደንግጧቸዋል።

ለዚህ ጭንቀታቸው መፍትሄ ብለው የመረጡት መንገድ የመከላከያ ኢታማዦር ሹም ፕ/ጀነራል ሳሞራ ዮንስና የብሄራዊ ደህንነት ሃላፊ ኣቶ ጌታቸው ኣሰፋ በሽምግልና እየያዙዋቸው ይገኛሉ።

የኣቦይ ስብሓት ተማፅኖ "መንግስታችን የቆመው በ60 ሺ መስዋእትነት ነው እያልን የመጣነው ለፕሮፖጋንዳ እንዲመቸን ነው(ህዝቡን ዋሽተነዋል) እንጂ በትጥቅ ትግል የተሰዋው ከ200 ሺ በላይ ውድ የሰው ሂወት ነው" ካሉ በኋላ "ይህ ሁሉ መስዋእትነት የተከፈለበት ትግላችን እያየነው ወደ ጠላቶቻችን እጅ እየገባ ነው፣ ድርጅታችን ከዚ ውድቀት ለማውጣትና ስርዓታችን ከውድቀት ለማዳን ኣስፈላጊ እርምጃ ለመውሰድ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ኣለባቹ" የሚል ሓሳብና ተማፅኖ ኣቅርበውላቸዋል።

በኣዲስ ኣበባ ለስብሰባ የተቀመጠው የህወሓት ማእከላዊ ኮሚቴ እየደረሰበት ያለው ተፅእኖ ለማብረድ በማሰብ "በትግራይ እየተካሄደ ያለው ልማት የሚቃወም ማንኛውም ሰው ከኣፍራሽ ተግባሩ እንዲቆጠብ..."የሚል መግለጫ ማውጣታቸው ይታወቃል።

የኣቦይ ስብሓት በትጥቅ ትግል ስለ ተከፈለው የሂወት መስዋእትነት ለ25 ዓመታት 60 ሺ ሲሉን ቆይተው ኣሁን ደርሰው 200 ሺ ነው የተከፈለው በማለት ስርዓቱ ለማቆየት ትልቅ ትኩረት እንዲሰጠው በመፈለግ ነው።

# ወያኔና አውሬው ዝንጀሮ ተመሳሰሉብኝ


ሀብታሙ ጀማል (ጀርመን)

በአለም ታሪክ ውስጥ አንባገነን ገዢዎች ለስልጣናቸው የሚሰጡት ህጋዊ ሽፋን ከሁሉም በላይ አዋቂዎች ፣ ለህዝብ ተቆርቋሪዎች ፣ የድሆችን እንባ ጠባቂና . . . ወዘተ ስለሆነም እራሳቸውን ብቸኛ አማራጭ አድርገው ይስማማሉ ። አንዳንድ በጠመንጃ ኃይል ከስልጣን ኮርቻ ላይ የተፈናጠጡ ቡድኖችና መሪዎች ብዙ ግዛቶችን በጭካኔ አጥቅተው ከያዙ በኋላ ሰው መሆናቸውንም እስከ መርሳት ደርሰው ነበር ። ሆኖም ግን መጨረሻቸው እነሱ እንዳሰቡት ሳይሆን ውጤታቸው ታላቅ ውርደትና በህዝብ ዘንድ መጠላትን ፣ ውድቀትን ፣ የህዝብ እልቂትን ከማስከተል ና የታሪክ አተላ ከመሆን አላመለጡም አላለፉምም ። ዛሬ ኢትዮጵያን የሚገዛው ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ወያኔ) ለይስሙላ እንደሚያናፍሰው ሳይሆን ከመጀመሪያ ሲመሰረት የትግራይን ህዝብ ከወገኑና ከሀገሩ ገንጥሎ በአልባኒያ ተምሳሌት የተዋቀረች ሀገር በመመስረት ለጥቆም ታላቋን የትግራይ ትግሪኝ ሪፐብሊክ ለመመስረት ነበር ። ሆኖም ግን ይህንን ጠባብ ዓላማ የተቃወሙትን የትግራይ ተወላጆችን አሁን በስልጣን ላይ ያሉትም ሆኑ በስልጣን ተጣልተው የተባረሩ ወያኔዎች በግፍ አርደዋቸዋል ። ብዙዎቹ ለትምህርት ሄደዋል እየተባለ ቤተሰብ እንኳን በወጉ ሳይቀብራቸው በሺዎች የሚቆጠሩት በየጥሻው ወድቀው ቀርተዋል ። በዚህ እኩይ አላማ በመነሳትም ኢትዮጵያን ያሉ የትግራይ ልጆችንና ባጠቃላይም በኢትዮጵያውያን ላይ ከሀገሪቱ መደበኛ ጠላቶች ጋር በማበር አጥፊ ሴራዎችንም በመጎንጎን እጅግ የረቀቀ እና ጭካኔ በተሞላበት መንገድ በሀገሪቱ ዋና ዋና የሀይማኖት ተቋማት ፣ በታሪኳ ፣ በግዛት አንድነቷ ፣ በስነ-ልቦናዊና ባህላዊ እሴቶቿ ላይና ባጠቃላይም በኢትዮጵያዊነት ላይ ወደር የማይገኝለት ጭካኔ የተሞላበት ግፍና በደል ፈፅሟል ። ወያኔዎች በብሄር ብሄረሰብ መብት ማስከበር ስም በማጭበርበር ልዩነትን እንደ መሳሪያ በመጠቀም ህዝብን ለመከፋፈልና አንድነቱን ለመበጠስ ጥላቻን በማራገብ ብሄራዊ መረጃና ደህንነት በሚባለው የወያኔ የስለላ ድርጅት አማካይነት የዘርና የጎሳ ፣ የድንበር ፣ የሀይማኖትና ልዩ ልዩ ግጭቶችን በመፍጠር ህዝብን እርስ በርስ እያፋጁ ይሄ ነው የማይባል እልቂትን ፈፅመዋል ። ይህ የስልጣን እድሜአቸውን ለማራዘም የዘረጉት የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲያቸው የዘር ማጥፋትንና የዘር ማፅዳትን ወንጀል ከማስከተሉም በላይ በሀገር ውስጥ ከፍተኛ የሆነ መፈናቀልን አስከትሏል ። ይህ አልበቃ ብሎ የሀገሪቱን ለም መሬቶች ህዝቡን ከአባቶቹ አፅመ ርስት በመንቀልና በማፈናቀል ለውጭ ኩባንያዎች የነፃ ያህል በመሸጥ በፈጠሩት ፖለቲካዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የኢትዮጵያን ህዝብ በሀገሩና በርስቱ ላይ የባዕዳን ባሪያ እንዲሆን በማድረግና በርሀብ እና በችጋር በመግረፍ አፍነውና ረግጠው በመግዛት እነሱና አጋሮቻቸው የሀገሪቱን ሀብት በመዝረፍና በማካበት ከብረዋል ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ላለፉት 23 ዓመታት የወያኔን የግፍና የጭካኔ አገዛዝ በትዕግስት ቢያልፍም እነርሱ ግን ግፉን እና ፀረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አላማቸውን በከፋ መልኩ ቀጥለዋል ። ስለሆነም ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በደደቢት በሻእቢያ ተጠንስሰው የተፈጠሩበት አላማ ግቡን እስካልመታ ማለትም ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንደ ሀገር መኖርን እስካላቆመች ወይም እስካልጠፋች ድረስ የጥፋት ዘመቻቸውን አያቆሙም ። የወያኔ ተግባር የአውሬውን ዝንጀሮ ይመስላል ። ዝንጀሮ የእህል ክምር ውስጥ ገብቶ ሆዱ እስኪጠረቃ ቢበላና ቢጠግብም ቀሪውን ለሌሎች እንዳይተርፍ በማሰብ ክምሩን እንዳልነበረ አድርጎ ያፈራርሰዋል ።ወያኔዎችም ለመርዘኛ እቅዳቸው ተግባራዊነት የኤርትራን ክፍለ ሀገር ደብዳቤ ፅፎ(ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት) በማስገንጠል የጀመሩትን ሀገሪቱን የማጥፋት ዕቅዳቸው መሳካት አገሪቱንና ህዝቧን በዘር በቋንቋ በኃይማኖት በመከፋፈል እያጋጩና እየቆራረሱ ይገኛሉ ። ለዚህም ነው ከሁመራ ጀምሮ በርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለውና ስፋቱ ደግሞ ከ 30-50 ኪሎ ሜትር ለም የጠረፍ መሬት ለሱዳን በስጦታ መልክ ያስረከቡት ። ስለዚህ እያንዳንዳችን እንደዜጋ በተለይም ደግሞ ሀገር ተረካቢው ወጣቱ ትውልድ ያለው ብቸኛ አማራጭ እንድ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ ሀገራችን ከመጥፋቷ በፊት ወያኔን ማጥፋት ታሪክ የጣለብን ግዴታችን መሆኑን መገንዘብ አለብን ። ወያኔ በሰላማዊ ትግልም ሆነ በአቤቱታ አይወገድም ። ወያኔ ሊወገድ የሚችለው በጠንካራና በተባበረ ሀይል ሲደቆስ ብቻ ነው ። ለዚህ ደግሞ የተደራጀ ሀይል ከምን ጊዜውም በላይ አስፈላጊ ነው ። ከተከፋፈልን እና ከተበታተንን እንመታለን ፤ ከተባበርን ከነቃንና ከተደራጀን ደግሞ ካለምንበት ከግባችን እንደርሳለን ስለዚህ ተደራጅተን ይህንን ፀረ ኢትዮጵያ ሀይል እናስወግድ ።

እናቸንፋለን !

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !



# ስነ ግጥም

ልቤ ልቤን ሲሞግተው.... .

"እውነትስ ምንትስ ማነው?"

እያለ ነው፡፡ .... .

ያም ሆኖ ነገሬ ከልብ

ያልወጣነውና ለሕዝብ

ለማንም ያልተገለጠ÷ የራሴ ድብቅ ሰባኤ

ልቤ ከልቤ ጋር ብቻ÷ ያደረገው የዝግ ጉባኤ

ከቶ የናንተን ዳኝነት÷ አልጠይቅምና ስሙኝ

ፋይል ከፋች እንዳትሉኝ፡፡ ......

ያው ብቻ በዘልማድ ሕግ÷ በእንቶ ፈንቶአችሁ ልረታ...... .

እውነቱ ከእውነቱ ተፋጭቶ÷ ሐቅ ሆኗልና ሸውታ

ስለዚህ አንዳንዴ ብቻ÷ አልፎ አልፎ ብቻ ላንዳፍታ

አሳቤም ሥጋዬም አብሮ÷ ትንፋሼም ሲያገኝ እፎይታ

ምንትሶች ለምትሉን÷ የለንምና ጸጥታ

ከዚያ ከሌት ውጣ ውረድ÷ ከቀን መኝታው ድውታ

ላመል ታህል ብቻ ድንገት÷ ለሃሣብ ንቃት ለትዝታ

ገለል ቀለል ሲለኝሽለስንቱ ሆይታና ዋይታ

ከዳር ዋጋው ካንድ ጊዜው÷ ከሂሣብ ዛቻው ቆይታ

ከግራ-ማ-ፎን ቀረርቶው÷ ከድም-ድሙ ካካታ

ከሙዚቃው ሆያ ሆዬ÷ ከናላ-ወቀጣው ፋታ

ከዳንኪራው ውትር ግትር

ከመጠጡ ብዥ ድንብር

ትንሽ የህሊና ሰላም÷ አገኘሁ ስል .... . የሚለኝ ቅር

እንደገና ለብቻዬ÷ ልቤን ቁስል የሚያጭር

አለብኝ የሐቅ ብትር

ነፍሴን ከስሶ እሚከራከር

እንደዛር እሚጎነትል÷ ሐቅ እንድጠይቅ የሚያስጥር÷

ያራቡኝ÷ ያጠሙኝ÷ የነሱኝን የሐቅ ዕድር

እንድጠይቅ÷ እንድጠይቅ÷ የሚያረገኝ እርር ክርር

ነፍሴን ከልቤ እሚያሚግት÷ በሐቅ ራብ እስካጣጥር

መንፈሴ ውስጥ የሚያቃጭል

'እውነትስ ማን ነው ምንትስ?' ÷ እስቲ እንጠያየቅ የሚል.... .

ሕመም አለኝ÷ .... . ይኸም ሆኖ÷ እግዜር ያሳያችሁ ላልል

ለይታችሁ አጥራችሁኝ÷ ከዳኝነታችሁ ባህል

ከፍርድ አደባባይ ከልል÷

ለኔ ከቶ ላታውቁልኝ

ነውር በቀር ላታዩብኝ

ጠር በቀር ላታስቡኝ

የሕሊናችሁን በደል÷ በኔ ለምትወጡብኝ

# ፍቅር እስከ መቃብር

ሰብለ ሰብለ ሰብለ ወዳጀ እመቤቴ
የመአልት ምርኩዜ የሌሊት መብራቴ
ስራብ እንጀራዬ ስጠማ ወተቴ
ሳዝን መጽናኛዬ ስደክም ጉልበቴ
ሳጣ አለኝታዬ ስጠቃ ኩራቴ
የስጋ የመንፈስ ያለሽኝ አንድ ሀብቴ
ቁርጥ ከሆነማ እኔ አንችን ማጣቴ
ምን ዋጋ ሊኖረዉ ከእንግዲህ ሂወቴ
የለም ህይወት በቃኝ ይገላግለኝ ሞቴ
ተቀማሁ ወይኔ ድሃ በመሆኔ
ጥየሽ የሄድኩለት ወንዝ ተሻግሬ
የደም እምባ አልቅሼበድሌአማርሬ
የሁዋሊት ስጎተት በፍቅርሽ ታስሬ
ወደ ፊት መራመድ እያቃተዉ እግሬ
አሁንም አሁንም ቆሜ እያየሁ ዞሬ
ምን ልቤ ቢፈራ ባይቀር መጠርጠሬ
በተስፋ ነበረ የወጣሁ ካገሬ
እስከ ዛሬም ድረስ በህይወት መኖሬ
ተስፋ ሆኖኝ ነበር ፍቅርሽና ፍቅሬ
ግን እዉነት ከሆነ የነገሩኝ ወሬ
ሊያገባሽ ነዉ ብለዉ ባለብዙ በቅሎ ባለብዙበሬ
በፍቅር ለሞተ መታሰቢያ ሆኖ እንዲቀር መቃብሬ
መኖር አልፈልግም ሞቸ ልደር ዛሬ

# የነግርሜ ትውልድ

*የነግርሜ ትውልድ*
*ጠብ አንስቶ ከዘውድ*
*የነ ዋለ፣ ባሮ*
*መደብ ላይ ቸርችሮ*
*የብሔር ቅማሮ*
*የነ ሙሴ፣ ሓየሎ...*
*ደርግን አንከባሎ*
*ድል ቢነሳም ታግሎ*
*አልቀረም ዘንድሮ*
*ያምናው እንጉርጉሮ*

*ሲሰማ ቅሬታ*
*የበደል አቤቱታ*
*ሲስተዋልም ጎልቶ*
*ብሶት ተበራክቶ*
*ጠብ ማንሳቱ የግድ*
*የዛሬውም ትውልድ*

## በሃይለማርያም ደሳለኝ ዕይታ

**የህዝቡ ኑሮ በጣም መሻሻሉን ለማየት**
**ለበግ በተገዛ ገመድ ደሮ ተሰቅሎበታል።**
**ዕድሜ ለወያኔ መርሐ ግብር ገና ገና**
**ደሮዋ ስትጠፋ ደግሞ ፎቶዋ ይንጠለጠል ይሆናል**
**ሃገራችን እንዲህ ካለ ዕድገት ላይ ደርሳ አታውቅም**
**እልልልል።**



# እኔ እወድሻለሁ



/ገብረክርስቶስ ደስታ /
ብዙ ሺህ ዘመናት
እልፍ አእላፍ ሌሊት
ሚሊዮን መሰለኝ
ፍቅሬ አንችን ስወድሽ ቀኑ ረዘመብኝ።
እኔ እወድሻለሁ
የሰማይ መሬቱን
የባህር ስፋቱን
የዓለም ዳርቻ የርቀቱን ያህል
እንደ ፅጌ-ረዳ
እንደ አደይ አበባ
እንደ ሎሚ ሽታ፡፡
እንደ እጣን ጢስ እንጨት፣ እንደ ከርቤ ብርጉድ፣
እኔ እወድሻለሁ፣
አበባ እንዳየ ንብ፡፡
እንደ ቢራቢሮ ጫካ እንደሚያስሰው
ፍቅርሽን በፍቅሬ በፍቅርሽ ልቅመሰው
ማር ወለላዬ ነሽ ከረሜላ ስኩዋር
አማርኛ አይበቃ፤
ወይ ጉድ!
ባለም ቋንቋ ሁሉ ቢወራ ቢነገር፣
እኔ እወድሻለሁ
እንደማታ ጀንበር።
እንደ ጨረቃ ጌጥ፣ እንደ ንጋት ኮከብ፣
እኔ እማልጠግብሽ
ስወድሽ፣ ስወድሽ፣ ስወድሽ፣ ስወድሽ፡፡
ጡት እንዳየ ህፃን ወተት እንዳማረው
ጠጋ በይ ዘመዴ አፍሽ ህይወቴ ነው።
ጣይ እንዳየ ቅቤ
ገላዬ ገላሽን ሲነካ የሚያልቀው፣
አፈር መሬት ትቢያ ውሃ እንደሚበላው፣
ፍቅሬ አንቺን ስወድሽ
ብዙ ሺህ ዘመናት
እልፍ አእላፍ ሌሊት
ውድ እወድሻለሁ፣
ዐይኖችሽን ባይኔ ተዳክሜ እያየሁ
ስወድሽ ስወድሽ እኔ እወድሻለሁ።

ጎረምሳው ልቡን ያሻፈተችውን ቆንጆ ለሚስትነት ለመጠየቅ አባቷ ቤት ይሄዳል።

**አባት**:- ልጄን ለጋብቻ ልትጠይቅ መጥተህ በአጠገቤ ማስቲካ ታኝካለህ ትንሽ እንኳን አታፍርም? ክብረቢስ

**ጎረምሳው**:-ይቅርታ ጌታዬ ስለጠጣው አፌ እንዳይሸት ብዬ ነው

**አባት**:-ጭራሽ መጠጥም ትጠጣለህ?

**ጎረምሳው**:-አዎ ግን አልፎ አልፎ ናይት ክለብ ስሄድ ብቻ ነው ምጠጣው

**አባት**:-ናይት ክለብ ስሄድ ብቻ?!! አታፍርም እንዴ ልጄን ለመጠየቅ ስትመጣ?

**ጎረምሳው**:-ከእስር ቤት ስወጣ ነው መሄድ የጀመርኩት እንጂ በፊት አልሄድም ነበር

**አባት**:-የባሰ አታምጣ!!!!አንተ ሌባ ልጄን ሰርቀህ ልታበላት ነው እንዴ?

**ጎረምሳው**:-ሌባ አይደለሁም ሰው ገድዬ ነው እስር ቤት የገባሁት

**አባት**:-ምን!!!! ነብሰ ገዳይ ነህ?

**ጎረምሳው**:-አይደለሁም የዛን ቀን በጣም ተናድጄ ስለነበር ነው ሰውየው የኛ ጎረቤት ነበር ልጁን ለማግባት ጠይቄው ከለከለኝ ከዛ ገደልኩት።

**አባት**:-ና አስቲ ልጄ! ና እቀፈኝ! ለልጄ እንዳንተ አይነት ጥሩ ባል ነበር ስፈልግ የነበረው !

# እቴ አንቺን ሳስብሽ

እቴ አንቺን ሳስብሽ ልቤን የሚደክመኝ
ዐይንሽ ላይ ሳተኩር እኔ ዐይኔን የሚያመኝ . . .

አይደለም ለፊትሽ፣ ለገጽሽ ከራማ
አይደለም ለድምጽሽ፣ ላንደበትሽ ዜማ
አይደለም ለጸጉርሽ፣ ለዚያ የሃር ነዶ
አይደለም ለጥርስሽ፣ ለሃጫው በረዶ . . .

አይደለም አይደለም፣ ውዴ አበባዬ . . .
ነገሩ ወዲያ ነው፣ ሌላ ነው ጉዳዬ . . .

አየሽ . . .
በኔና አንቺ መንደር፣ በሁለታችን አገር
ወንድ ነው የበላይ፣ ወንድ ነው ‘ሚከበር
ወንድ ነው ‘ሚያነሳ፣ ወንድ ነው የሚጥል
ወንድ ነው በግብሩ ሴትን የሚያጣጥል
አዳፍኖ ‘ሚያቃጥል . . .

(በርግጥ ሴትም ሆነው ሴትን የሚያረክሱ
አይጠፉም ይሆናል በስምሽ የሚያርሱ)

ግን ግን ለምን ሆነ ?!
ልቤ ገነገነ . . .

አዋቂ ታዋቂው፣ አድናቂ አዳማቂው
መሪና ተመሪ፣ ተጨመላላቂው
መንገድ የጀመረ፣ ተረኛ ጠባቂው
ሁሉም እንዳቅሙ፣ ስምሽን አንስቶ
እንደፈቀደለት፣ ድክመትሽን አውስቶ
ውበትሽን አጉልቶ፣ ገላሽን አቡክቶ
ነፍስሽን ዘንግቶ፣ ህልምሽ ላይ ተኝቶ
ሲጽፍ ሲቸከችክ፣ ስንቱን እንቶፈልቶ
ኃይልሽ በየት በኩል፣ በነማን ተሰምቶ
ኸረ እንደምን ታይቶ …

(ይኸው እኔ ራሴ፣ እየጻፍኩ አይደለ
ብዙ ያልጨመረ፣ ብዙም ያልጎደለ)

ጥንባዣም ደራሲ፣
ኮተታም ሃያሲ፣
እንቅልፋም ገጣሚ፣
ሆዳም አሳታሚ . . .
ባንድ አገር፣ ባንድነት ዐይኑ እየፈዘዘ
በንዋይ በዝና፣ ነፍሱ እየነፈዘ
በሆዱ፣ በራቡ፣ እየደነዘዘ፤
የቃላት ቡትቶ እየበዋወዘ
ስንት ቀን ገደለሽ፣ ስንት አንቺን ገነዘ …

አየነው፣ ሰማነው …
ገዝተን አነበብነው …

‘ወሲብ፣ ገድል፣ ሚስጥር
የአዲስ አባ ‘ቂንጥር’
የጭኖች ንቅሳት
የዳሌ ትኩሳት’
መዋደቅ መነሳት የሚል ዝባዝንኪ
ስንት ሰዎች ጻፉ በይ ንገሪንኝ እስኪ ?!

ለምቦጭሽን አትጣዪ፣ ጠበቅ አርገሽ ስሚኝ
ካጠፋሁም ላጥፋ፣ ተይኝ አታርሚኝ
ይልቅ ተማሪና ስታመም አክሚኝ።

አሁን ያ ደራሲ . . .
‘ጭኗ ሲተራመስ፣ ዳሌዋ ሲቆጣ
ጡቷ ሲወጣጠር፣ ቅንዝሯ ሲመጣ
ሲሰራት፣ ሲቆላት፣
እንደ ጉድ ሲያምሳት፣
አብርድላትና ከንቱ ነፍሷን ንሳት፤
መቼም ከዚህ በቀር ሁሉም ነው የሚያንሳት።’

ብሎ እየጻፈ በገላ ቸርቻራ
በሴትነትሽ ጥግ ዝሙት እየዘራ
ከመጣ ከሄደው አንቺን እያዳራ
‘ታላቅ ሰው’ ተብሎ ባገሩ ሲጠራ
ማን ተከላከለ?
ማን ሰው ሃቅ አወራ?

ደግሞ የገረመኝ …
ከሁሉም ከሁሉም ይብሱን ያመመኝ …

‘በጭኖችሽ ሰማይ
ወጥታ ብርቱ ፀሐይ
አቃጥላ ፈጀችሽ አንቺኑ መልሳ
የቁሌት አዝመራ በነፍስሽ ነስንሳ።’

ብሎ የጻፈውን ያንኑ ደራሲ
ሲያንቆለጳጵሰው ያ ብኩን ሃያሲ

“እውነት ነው፣ ሃቅ ነው
እሱማ ታላቅ ነው።”
ብለሽ ስታወሪ፣ ላገር ስትለፍፊ
ስሰማና ሳይሽ ዘውትር ስታናፊ
አ – ቤ – ት… ስታስከፊ !

በእውነት ገረመኝ …
በእውነት አመመኝ …

ጡት ብቻ ነሽ አንቺ ?!
ጭን ብቻ ነሽ አንቺ ?!
ወሲብ ነው ገድልሽ ?!
በቃ እሱ ነው ድልሽ ?!
ህልም የለሽም እንዴ ?!
ኧረግ ወየው ጉዴ . . .

(አትመልሽው ይቅር፣ አታውሪልኝ ለኔ
ኑሪና አሳይው ለብኩን ወገኔ።)

አየሽ አንቺ ለሱ . . .
(ብታምኚም ባታምኚም)
‘አንብበሽ ማይገባሽ፣ ገብቶሽ ማትረጂ
ካገኘሽው ጋራ፣ የትም ‘ምትበ-ጂ’
ትሰሪው ትሆኚው፣ ታልሚው የሌለሽ
በቂጥሽ ከመኩራት ፥
ቂጭ ብሎ ከማውራት ፥
ወንድ ልጅ ከማርካት ፥
የዘለለ ሚና ባለም የጎደለሽ
ሸሌ ነሽ፣ ሸርሙጣ፤
ቀን እየጠበቀ ግብርሽ የሚወጣ።’

ደሞ ይሄን ያልኩሽ፣ እኔ እንዳልመስልሽ
ለስድብ ለቁጣ ፥
ለተቃውሞ ጣጣ ፥
መንገድ አደባባይ፣ ጎዳና እንዳይጠብሽ
ገላልጠሽ መርምሪው፣ ያለውን በቅርብሽ…

አውቃለሁ።

የሚያብብ ቡቃያን ብዙ ነው ረጋጩ
የደረሰ ፍሬን እልፍ ነው አፍራጩ
ብዙ ነው ገናገፉ፣ ብዙ ነው በዝባገፉ
ብዙ ነው በዋገፉ፣ ብዙ ነው አፍዛገፉ
ብዙ ነው ቀጣፊው፣ ብዙ ነው በራገፉ …

መሪዎቹ ገናዥ፣ ካድሬዎቹ ገናዥ
አምራቾቹ ገናዥ፣ ነጋዴውም ገናዥ
ዘፋኞቹ ገናዥ፣ ጸሐፊዎች ገናዥ
በቀልዶች ጋጋታ፣ በፌዞች አደንዛዥ
እኔና አንቺ ደግሞ ባካኝ ተንጠራዋዥ …

“እምቢኝ አልገንዝም !
የሚያብብ ቡቃያን አላደነዝዝም !
የነገዋን ብርሃን አላደበዝዝም !”
ያለው ብርቱ ታጋይ
በነዚያኞች ሃካይ
ተጠልፎ ተጥሎ ተጋድሞበት ሃኔ
አሸልቧል ወዲያ ማንም ሳይል ወይኔ።

አንዳንዱም እስር ቤት
አንዳንዱም መጠጥ ቤት
ገሚሱም ሰው አገር
ገሚሱም ጎዳና ወደናንተ ሰፈር
ወድቋል፣ ይታዘባል
የወጪ ወራጁን ሳቅ ይመዘግባል።

ይገርማል . . . !
“ትውልድን ለማነፅጽ
ወገንን ለመቅረጽ
በሚል አጉል ቅዠት እኔ አልተነሳሁም
ጥበቤን ለማውረድ በርግጥ አልሳሳሁም
እንደመጣ ጻፍኩት
ከዚያም አሳተምኩት
በቃ ተደነቀ
ባገሩ ታወቀ።”

ይሉት መቀባጠር፣ አጉል ፍልስፍና
በአፍሪካ ምድር፣ ተስፋን ላያቀና
የተደፈርሽ አንቺን ክብር ላያፀና
አይገባኝም እኔ አታስረጂኝ እቴ
ይልቅ ነቅተሽ አንቂኝ፣ አድኚኝ ከሞቴ።

አየሽ ባገራችን . . .
ትንሽ ገንዘብና የበዛ ቲፎዞ
በግራና በቀኝ፣ ለጋሻ ተይዞ
ላውሪ ጋዜጠኛ፣ ለጣፊ መናኛ
ኪሱን ሸጉጦለት፣ ነፍቶት እንደፊኛ
ካልሆነ አይጻፍም፣ አይታተም ከቶ
ቢታተምም እንኳ አለልሽ ተረስቶ
በቁም ተዘንግቶ ።

(ይህ ሁሉ መለፍለፍ አሁን ለምንድነው
ዝብዘባ የሚያበዛ ጅላንፎ ሞኝ ነው።)

ብቻ አንቺን ሳስብሽ፣ ለዚህ ነው ‘ሚደክመኝ
እራሴን፣ ወገቤን፣ አይኖቼን የሚያመኝ …

ቢሆንም አምናለሁ!
ከጡቶችሽ ሰማይ
ከጭኖች ሰማይ
ከዳሌ ከባትሽ፣ ከሽንጦችሽ ሰማይ
የራቀ የላቀው የነፍስያሽ ሰማይ
ኃይሉን የተፋ ቀን፣ ወጥተሽ ካደባባይ
ያኔ ነው ያገሬ፣ ብርሃኗ የሚታይ
ያኔ ነው ሚነቀል፣ የሕቦቼ ብካይ።

---

አብዲ ሰዒድ
2006 E.C

## እነሆ ፍቅር ተኮር ግጥም
## ብሰማሽ - ብስምሽ

---------

እንዳልኖረ ልቤ ጨዋታን ተርቦ
የአንደበትሽ ጥፍጥና በለዛ ታጅቦ፤
ብሰማሽ
ብስምሽ
ብሰማሽ
ብስምሽ. . . --
ውዬ ባድር ከቶ፣
በቃኝ አይል ልቤ
ጠገብኩ አይል ስሞ
ጠገብኩ አይል ሰምቶ፡፡
ኄኖክ ስጦታው



አካሉ የደከመ ሃሳቡ የቀደመ
የወያኔ ትክክለኛ ተምሳሌት

# እናት ለምን ትሙት ትሒድ አጎንብሳ ታበላ የለም ወይ በጨለማ ዳብሳ

እሱንዳለ በቀለ



የዛሬ ጽሑፌ የተፀነሰው የእናትነትን ርዕሰ ነገር ከወጣቱ ጓደኛዬ ከእሱእንዳለ በቀለ ጋር እየተጨዋወትን ሳለ ነው። እሱእንዳለ በቀለ በተለይ የሚታወቅበት ጉዳይ ኢትዮጵያዊያን እናቶችን በየዓመቱ ሲያሰባስብ፣ ሲያስደስት እና ሲዘክር በመቆየቱ ነው። ከዚህ በፊት በሂልተን ሆቴል፣ በኢምፔሪያል ሆቴል፣ በጣይቱ ጃዝ አምባ፣ በጋንዲና በዘውዲቱ ሆስፒታሎች፣ በካፒታል ሆቴል ውስጥ የእናቶችን ቀን እያከበረ በጣም ጥሩ የሆነ ማህበራዊና ባሕላዊ ዕሴት እየገነባ የሚገኝ ወጣት ነው። እናም የፊታችን ግንቦት 2 ቀን 2007 ዓ.ም በካፒታል ሆቴል ውስጥ ከ9-12 ድረስ በሚቆይ ዝግጅት ለሰባተኛ ጊዜ የእናቶቻችንን በዓል ሊያከብር መዘጋጀቱን ሲነግረኝ ቀልቤ ተሰረቀ። ከእርሱ ጋርም ቁጭ ብለን ረጅም ሰዓት ወስደን እናትነት በኢትዮጵያ ኪነ-ጥበብ ውስጥ ምንድን ነው? ብለን አወራን። የዛሬ ፅሁፌ የዚሁ ወጋችን ውጤት ነው።

በኢትዮጵያ የኪነ-ጥበብ ዓለም ውስጥ እናትነት ልዩ ስፍራ ሲሰጠው ኖሯል። ኢትዮጵያ እናትነት በሁለት መንገዶች ትገልፃለች። አንደኛዋ እናት እንደ ሰው አርግዛ፣ አምጣ፣ ወልዳና አሳድጋ ለቁም ነገር የምታበቃው እናት ነች። ሁለተኛዋ እናት ሀገር ነች። እናትነትን በሀገር መመሰል፣ መግለፅ በኢትዮጵያ ኪነ-ጥበብ ውስጥ በሰፊው ጎልቶ የምናገኘው ነው።

ጥላሁን ገሠሠ መድረክ ላይ ሆኖ በዓይኑ እንባ እየፈሠሠ እንዲህ ነበር ያዜመው፡-

“ክብሬ እናቴ ሀገሬ የኔ መመኪያዬ፣
አንቺው ነሽ ኢትዮጵያ መከታ ጋሻዬ፣
ጥቃትሽን ከማይ በሕይወት ቆሜ፣
ስለ ክብርሽ እኔ ልሙት ይፍሰስ ደሜ።

የእናትነት መገለጫ ቃሉ፣ ዜማው፣ ቋንቋው ጥልቅ ነው። ኪነ-ጥበባችን ውስጥ ትልቁን ቦታ ይዞ እናገኘዋለን። ዛሬ በሕይወት የሌሉት ድምጻዊያኑ ሻለቃ ወጋየሁ ደግነቱ እና ብዙነሽ በቀለ ሙዚቃ ውስጥ ካገነኗቸው ስራዎቻቸው መካከል ስለ እናት ያዜሟቸው ሙዚቃዎች ናቸው። የናትነትን ርዕሰ ጉዳይ ይዘው ብቅ የሚሉ የጥበብ ውጤቶች የታዳሚን መንፈስና ቀልብ በቀላሉ የመቆጣጠር አቅማቸው ትልቅ ነው።

የአፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል /Chronicle/ ፀሐፊ የነበረውና የልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ የቤት ውስጥ አስጠኚ ሆኖ ሲያገለግል የቆየው ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ደብተራ ዘነብ፣ ከመቶ አርባ ዓመት በፊት በፃፈው የፍልስፍና ፅሁፉ እናትነትን ሀይማኖታዊ ዳራ ሰጥቶት ገልፆታል። ደብተራ ዘነብ “መፅሐፈ ጨዋታ ስጋዊ ወ መንፈሳዊ” በተሰኘው መፅሐፉ የእየሱስ ክርስቶስን ስቅለት ያስታውሰናል። እየሱስ በቀራኒዮ ሲሰቀል ወዳጆቹ መላዕክትና ቅዱሳኑ ራሳቸው አብረውት አልነበሩም። ይህን ሁኔታ ነው ደብተራ ዘነብ በፍልስፍና ጽሁፉ ውስጥ የሚተቸው። ከእናቱ ከማርያምና ከሌሎቹ ሴቶች በስተቀር አጠገቡ ማን አለ? እያለ በሰላ አፃፃፉ ያስታውሰናል። እናት በልጇ ነገር ሁሉ ከፊት እንደምትሰለፍ ዘነብ ኢትዮጵያዊ ውብ በሆነው መፅሐፉ ዘላለማዊ ትርክትን አስቀምጦልን አልፏል።

እናትነት በኪነ-ጥበባችን ውስጥ ምን እንደሚመስል ለመግለፅ ሰፊ የሆነ ፅሑፍ ያስፈልገናል። ስለዚህ በቀላሉ ገብተንበት በቀላሉ የምንወጣበት አይደለም። እናት የአለሙን ፈጣሪ እየሱስ ክርስቶስን ወልዳለች፣ አጥብታለች፣ አሳድጋለች። እናት በሰው ልጆች ውስጥ ወደር ያልተገኘለትን የሳይንስ ምርምርና ግኝት ያደረገውን አልበርት አንስታይንን ያክል ፍጡር አርግዛ፣ ወልዳ፣ አጥብታና አሳድጋ ለዓለም አበርክታለች። እናት ሰር አይሳክ ኒውተንን የሚያክል የምርምር ሰው ለዚህች ምድር አበርክታለች።

እናትነትን ለመግለፅ ቅኔ ቢደረድሩ፣ ቋንቋ ላይ ቢራቀቁ፣ ዜማ ላይ ቢፈላሰፉ. . . ተገልፃ አታልቅም። እናትነት ጥልቅ ነው። ውስብስብ ነው። ምስጢር ነው። ዲስኩረኛው ባለ ወግ፣ በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር በአንድ ወቅት ስለ እናትነት ሲያወጋ፣ እናት ልጇ አድጎ ትልቅ ሰውም ቢሆን ራሱን ቻለ አትልም። ለእሷ አሁንም ልጅ ነው። እንደ ልጅነቱ ሁሉ በጉልምስናው ጊዜም ትጨነቅለታለች ብሏል።

ልጅ መጀመሪያ የሚያውቀው ፈጣሪ እናቱን ነው። ከናቱ ጡት ይጠባል። ይመገባል። ይፀዳዳል፣ ለእሱ እናቱ ናት ፈጣሪው። ከዚህ በፊት አንድ ፅሑፍ አንብቤ ነበር። ፀሐፊው መምህር ሰለሞን ፋንቱ ይባላሉ። እርሳቸው በፃፉት ፅሑፍ “እግዚአብሔር ሁሉም ቦታ ስለማይገኝ እናቶችን ፈጠረ” የሚል ሃሳብ ያለው ነው።

ይህችው ፈጣሪ ነች የምትባለው እናት ኢትዮጵያ ውስጥ ለየት ያለ ትርጓሜ አላት። ለምሳሌ አውሮፓውያን እናቶች ልጆቻቸውን እስከ 18 ዓመት ድረስ ካሳደጉ በኋላ ለመተያየት እንኳን አይችሉም። ልጆች ራሳቸውን ከቻሉ ወደ ወላጆቻቸው ዘነድ እምብዛም አይመጡም። ለአብነት ያህል ኖርዌጂያን /የኖርዌይ/ እናቶች እና የጀርመን የሌሎችም እናቶች በልጆቻቸው ናፍቆት እንደሚሰቃዩ ጥናቶች ያሳያሉ።፡ እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ እናትና ልጅን የሚለያያቸው ሞት ብቻ ነው። ፍቅራቸው እስከ መቃብር ይወርዳል።

ኢትዮጵያዊት እናት ሁሌም ቅኔ ሲደረደርለት ቢኖርም ጥልቅ እና ውስብስብ የአንጀት የደም ምስጢሯ ገና ተገልፆ አላለቀም።

“ቢርቁት የማይርቅ የናት ሆድ ብቻ ነው” ተብሎ ቢዜምላትም፣ ወይም ደግሞ ፋጡማ የተባለች ወጣት እንደገጠመችው፤
“ሆድሽ ቤቴ ልብሽ የኔ፣
ደምሽ ደሜ ፍቅርሽ ለኔ፣
ያነቺ ሁሉ ሆኖ ለኔ፣
ልጇ አትበይ፣ በይኝ እኔ።

ብትልም እናት ገና አልተገለፀችም። አንድ ገጣሚ ደግሞ አየ አየና ቢቸግረው እንዲህ አለ፡-
ቢሰፈር ቢለካ፣
እናትን የመሰለ
አይገኝም ለካ!

ስለ እናት የተገጠሙ ስንኞች አያሌ ናቸው። ስፍር ቁጥር የላቸውም። ሁሉም ታዲያ ፍቅሩን ነው የሚገልፅላት። ሌላ ገጣሚ ደግሞ እንዲህ አለ፡-
የሕይወቴ መብራት የኑሮዬ ፋና
የመኖሬ ምስጢር እናቴ ናትና
አደራ አምላኬ አኑራት በጤና

ይህ ገጣሚ እናቱ በጤና እንድትኖርለት የሚመኝ ነው። ሁሉም የናቱን ዘላለማዊነት ይመኛል። እናቴ ኑሪልኝ ይላል። እሌኒ በየነ የምትባል ሴት ደግሞ ከዚሁ ጋር ተመሳሳሰይነት ያለው ግጥም ስለ እናቷ አቅርባለች።
እማ አትሙቺ ልሙትልሽ እኔ፣
ዘመድና ወገን የለኝ ከጎኔ፣
የለኝም ጓደኛ የኔነው የምለው፣
ያላንቺ እናቴ ሕይወቴ ባዶ ነው።
ባክሽ አትሙችብኝ ኑሪልኝ ዘላለም፣
አመሌን የሚችል ካንቺ ሌላ የለም።

እናት ገመና ሸሻጊ ናት። እናት ቤት ናት፣ መጠለያ ናት። ብዙ ዘመድ ናት፣ ጓደኛ ናት። ለዚህም ነው ገጣሚዋ ከላይ የሰፈሩትን ስንኞቿን የደረደረችው። አንዳንዶች “እውነተኛ ፍቅር የማየው ከናቴ አይን ነው” በማለት ይናገራሉ።
እናት እናት አሏት ስሟን አሳንሰው፣
አለምን ሁሉ የምትበልጠዋን ሰው።

በማለት ትልቅነቷን ለመግለፅ ሁሉ ተሞክሯል። ዓለምን ሁሉ የምትበልጥ ግዙፍ ስብዕና ያላት ናት እያሉ ገጣሚያን ይደረድሩላታል። ይህን ከላይ የፃፍኩትን ግጥም የጎጃም ሰዎች ደግሞ እንዲህ ይሉታል።
እናት እናት አሏት ስሟን አሳንሰው፣
አባይና ጣናን የምትበልጠዋን ሰው።

ጎጃም ውስጥ ላሉ የገጠር ሰዎች የትልቅነት ማሳያቸው አባይና ጣና ነው። እርግጥ ነው፤ አባይ ገና ከፍጥረት አለም ጽንሰት በፊት ጀምሮ ሲፈስ የኖረ ትልቁ ወንዝ ነው።

በኢትዮጵያ የግጥም /የአገጣጠም/ ስልት ውስጥ መንቶ /Couplet/ የሚባል አፃፃፍ አለ። ይህም ሁለት ስንኞችን በመደርደር የሚገጠም ነው። በሁለት ስንኞች የዓለምን ውጣ ውረድ ሁሉ የሚገልፁ ገጣሚያን ያሉባት ሀገር ነች። ሁለት ስንኞች በዚህች ሀገር ውስጥ ብዙ የሆድ ሆድ ጨዋታዎችን ሲያቀባብሉ የኖሩ ናቸው።
እናቴን አሰብኳት በሶስት አማርኛ፣
ሲርበኝ ሲጠማኝ ታምሜ ስተኛ።

እነዚህ በሁለት መስመር የሚገጠሙ ስንኞች የውስጥ ራሮትን የመግለፅ ከፍተኛ አቅም አላቸው። ከላይ የተገጠሙትን እንኳ ብናያቸው ብንመረምራቸው ሰፊ ትንታኔ የሚያሰጡ ናቸው። ግን ዝርዝሩን በሁላችንም ልቦና ውስጥ አስቀምጠነው ወደ ሌሎቹ ሃሳብ እናምራ።

ብዙ ሰዎች በቤታቸው ግድግዳ ላይ ጥቅስ ሲያስቀምጡ የእናት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ለምሳሌ “ያለ እናት አለም ጨለማ ናት” የሚል ጥቅስ አንብቤያለሁ። ይህ ማለት እናት ብርሃን ናት የሚለውን አባባል አንድን ወሰድ ያደርጋል። ለዚህም ነው ቀጣዩ ግጥም እናቴን አደራ የሚለው።
ከማር ጭማቂ ላይ አይወጣም መራራ፣
እባክህ አምላኬ እናቴን አደራ።

በዓለም ላይ ከሚደርሱ ክፉ ነገሮች መካከል የእናት እና የልጅ በሞት መለያየት ነው። ይህ በኢትዮጵያ ውስጥ ሲሆን ደግሞ ይከፋል። ምክንያቱም የናትና የልጅ ቅርብርብ የማያረጅ የማይጠወልግ፣ የማይደበዝዝ በመሆኑ ነው። ሁሌም አዲስ ነው። ለዚህም ነው ቀጣዩ ግጥም ከባለብዕረኞች ብቅ ያለው፡-
እናቴ አትሙቺ ልሙትልሽ እኔ፣
ከጎኔ ሳጣሽ ይባክናል አይኔ።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ማንሳት ይቻላል። በተለይ እኔና እሱእንዳለው በቀለ ስለዚሁ በኢትዮጵያ ውስጥ ለስድስተኛ ጊዜ ግንቦት 2 ቀን 2007 ዓ.ም በካፒታል ሆቴል ስለሚከበረው የናቶች ቀን ስንጨዋወት አንድ ነገር ተነሳ። ነገሩ ቀፋፊ ቢሆንም ብዙ ሃሳቦች በውስጡ አሉት። ይህም “እናት መቼ ትሙት?” የሚል ጥያቄ ነው። ሞት አይቀርምና እናት መች ትሙት?

የኪነ-ጥበብ ባለሙያ የሆነው ፍፁም አስፋው /የማለዳ ኮከቦች የተሰጥኦ የቴሌቭዥን ፕሮግራም አዘጋጅ/ ስለ እናቱ አንድ አስገራሚ ግጥም አቅርቧል። የግጥሙ ሃሳብ የናትን ሞት በውስጡ የያዘ ነው። ፍፁም ሲገልፅ “እናቴ ሞትሽን ከኔ በፊት ያድርገው” እያለ ነው። “ራስ ወዳድ ሆኜ አይደለም፤ አንቺ ለኔ ያለሽን ፍቅር ስለማውቀው እኔ ሞቼ ብታይ እጅግ ትጎጅብኛለሽ ብዬ ነው” እያለ ግጥሙ ትረካ ያቀርባል። ብዙ ጊዜ በባህላችን “ካንቺ/ካንተ በፊት ሞቴን ያድርገው” ነበር የምንለው። ግን በፍፁም አስፋው ግጥም ውስጥ “ሞትሽን ከኔ በፊት ያድረገው” የሚል ሃሳብ የሚያፀባርቅ ነው።

እናት በዚህ ጊዜ ትሙት የሚል ሃሳብ የሚናገር ሰው ማግኘት ከባድ ነው። ግን እናት በአፀደ ስጋም ብትለይ በልጆቿ ነብስ ውስጥ ህያው ናት።
እናት ለምን ትት ትሒድ አጎንብሳ
ታበላ የለም ወይ በጨለማ ዳብሳ

የእናትነትን ርዕሰ ጉዳይ አንስተን መቋጫ የለውም። የእናት ርዕስ አያልቅም። ትውልዶች እየመጡ ሲፅፉት ይኖሩታል እንጂ አያልቅም። ታዲያ ይህን የማያልቅ ርዕሰ ጉዳይ ቢያንስ በዓመት አንዴ እየተሰበሰብን እናቶቻችንን እናመስግን፣ እናስደስት፣ ያጣናቸውንም እናቶች በፍቅራቸው ገፀ-በረከት እንዘክራቸው ብሎ ወጣቱ እሱእንዳለ በቀለ ለሰባተኛ ጊዜ በካፒታል ሆቴል ውስጥ ግንቦት ሁለት ቀን ከ8-12 ሰዓት ክብረ-በዓል አዘጋጅቷል። ሁላችንም እናቶቻችንን ይዘን እንድንመጣ እና የተለዩንንም እናቶች እንድንዘክራቸው ጋብዞናል።

## ቀልድ

ሚስት( ትደውልና) የማትረባ! ደደብ! የት አባክ ነው ያለከው?
-ባል፡- ፒያሳ ነኝ!
-ሚስት፡- እዛ ምን ትሰራለሀ?!
-ባል፡-አንዴ ትዝ ካለሽ የሆነ ወርቅ ቤት አልጎበኘንም?
-ሚስት፡- አስታወስኩት ውዴ
ባል፡- የወርቅ ሀብል አይተሽ ወደድኩት ስትይ ገንዘብ ሳገኝ
እገዛልሻለው አላልኩም?
ሚስት፡-አዎ የኔ ፍቅር.
ባል፡- ወርቅ ቤቱን አወቅሽው?
ሚስት፡-አዎ ወለላዬ
ባል፡-ከእሱ አጠገብ ያለው ግሮሰሪ ነኝ

## ማስተዋል

ሚስት አምሽታ ወደቤት እየገባች ነው ...
ወድያው የመኝታ ቤቷን ከፍታ ስትገባ
አልጋዋ ላይ ሁለት የተኙ ሰዎችን
ትመለከታለች፤ አራት እግሮች ከብርድ ልብሱ
ስር ወተው ይታያሉ
ከዝያም ወድያውኑ አጠገቧ ያለውን ዱላ አንስታ
ከብርድ ልብሱ ውስጥ ያሉትን ሁለቱን ሰዎች
ባላት ኃይል መደብደብ ትጀምራለች ..ወድያው
መደብደቡን ታቆምና ወደ ሳሎን ቤት ስትሄድ
ባሏ ሶፋ ላይ ቁጭ ብሎ ጋዜጣ ያነብ ነበር
ከዝያም ባልየው " hi darling...ቤተሰቦችሽ
መተዋሉ
የኛ መኝታ ቤት ተኝተዋል ሰላም አልሻቸው ..?
ሲላት ሚስት በድንጋጤ እራሷን ስታ ወደቀች ::
"የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል አሉ"

ሰላም እንሰንብት

ሃሳባችሁን በ lisanehizb@mail.com
ላኩልን እናስተናግዳቸዋለን።